የወንጀል ስነ ስርአት ህግ

(Criminal procedure Law)

መስከረም 2006 ዓ/ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

ምዕራፍ አንድ

1. የወንጀል ህግ ሥነሥርዓት ትርጓሜ እና ዓላማ

ምዕራፍ ሁለት

2. የወንጀል ፍትሕ ሂደት አጀማመርና መቋረጥ

2.1. የወንጀል ፍትሕ ሂደት አጀማመር

2.1.1. የወንጀል ክስ(Accusation) እና የግል ተበዳይ አቤቱታ(Complaint)

2.1.2. የእጅ ከፍንጅ ወንጀል አፈፃፀም

2.2. የወንጀል ፍትሕ ሂደት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

ምዕራፍ ሶስት

3. በምርመራ ሥራ የዐቃቤህግና የፍርድቤት ሚና

3.1 የወንጀል ምርመራ አላማና መርሆ

3.2 የማስረጃ አሰባሰብ

3.3 መበርበርና መያዝ (Search and Seizure)

3.3.1. በፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር ና መያዝ

3.3.2. ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር ና መያዝ

3.4 ተጠርጣሪን መያዝና የተከሳሽነት ቃል መቀበል

3.4.1 በፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ

3.4.2 ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ

3.4.2 ቃል መቀበል

3.5. ከተጠርጣሪ አካል ላይ የሚወሰድ ማስረጃ

ምዕራፍ አራት

4. የጊዜ ቀጠሮ

4.1 የጊዜ ቀጠሮ ትርጉምና ዓላማው

4.2 በጊዜ ቀጠሮ የሕጉ አተረጓጎም

4.3 የተጠርጣሪ መብትና የጊዜ ቀጠሮ

4.4 በጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ የሚከሰቱ ተግዳሮቶችና ችግሮቹ ለማስወገድ የዐቃቤ ህግና የፍርድ ቤቶች ሚና

ምዕራፍ አምስት

5. ፍርድቤት ስለመቅረብ እና በዋስ ስለመለቀቅ

5.1 የዋስትና ታሪካዊ እድገት፣ ትርጉምና አላማ

5.2 በዋስ ስለ-መለቀቅ፡ የጣብያ ዋስትና፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ጥያቄና አወሳሰን

5.4የዋስትናው ገንዘብ ልክ መወሰኛ መስፈርቶች

5.4 ዋስ የመሆን ብቃት

5.5 የዋሱ ኃላፊነት ወሰን

5.6 የዋስትና መብት የሚያስገኙና የማያስገኙ ወንጀሎች

5.7 በዋስትና ብይን ላይ ድጋሚ ማየትና የሚቀርብ ይግባኝ

5.8 በዋስትና ጥያቄ የዐቃቤ ሕግና ፍርድ ቤቶች ሚና

ምዕራፍ ስድስት

ክስ ማቅረብ

6.1 ክስ ስለ ማቅረብ

6.2 ክስን ስለ ማሻሻል

6.3 ክስን ስለ ማንሳት

ምዕራፍ ሰባት

ምስክር መፈተን

7.1 ስለ ምስክር አቀራረብና መፈተን በጠቅላላ

7.2 የምስክር አጠያየቅ ቴክኒኮችና አወቃቀር

7.3 መቃወም (Objection)

7.4 ምስክር በመፈተን የፍርድ ቤት ሚና

ዋቢ ጽሁፎችና ጉዳዮች

መግቢያ

ወንጀል የአንድን ማኅበረሰብ ህልውና አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር ነው። ህገ-ወጥነቱና አስቀጭነቱ በህግ የተደነገገውን ድርጊት መፈፀም ወንጀል ነው። ywNjL ድርጊት አሳሳቢ ከሚያደርጉት ብዙ ምክንያቶች እጅግ ውድ የሆነው የሰው ህይወት ይቀጫል፣ አካል ያጎድላል፣ የንብረት ባለቤትነት መብት ይነጥቃል። የወንጀል ድርጊት በአንድ በኩል የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት በማናጋት ህዝብ ከስጋት ነፃ የሆነ አስተማማኝና ሰላማዊ ኑሮ እንዳይኖር ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዜጎችን መብትና ህጋዊ ጥቅሞች የማስከበር ኃላፊነት ባለበት በአንድ አገር መንግስና ህዝብ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ወንጀል ተብለው ተለይተው በሕግ ላይ የተመለከቱ ተግባራት ተፈፅመው ሲገኙ ተጠያቂነት ሊከተል ይገባል። አጥፊውን የመለየት አካሄድ ያለ አግባብ ያላጠፋን ሰው እንዲጠየቅ እንዳያደርግ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ እውን ከሚሆንበት የህግ ማእቀፎች አንዱ የወንጀል ስነስርአት ህግ ነው። የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዋና ዓላማም ይህ ዕውን እንዲሆን ማድረግ ነው።

የዚህ ዕሁፍ ዓላማም ሠልጣኞችን በተግባር ማብቃት በመሆኑ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ፅንሰ-ሃሳባዊ ከመሆን ይልቅ አተገባበር ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል። በተጨባጭም ሕጉ ሥራ ላይ ሲውል የሚያጋጥሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ተካተዋል። ይሁንና ሕጉን ለመረዳት ፅንሰ ሃሳቦችን ማብራራት የግድ አስፈላጊ በመሆኑ በቅድሚያ እንዲታዩ የተደረገ ሲሆን በጽሑፉ ውስጥም አስፈላጊነታቸው እየታየ እንዲገቡ ተደርጓል።

የወንጀል ሕግ በሥራ ላይ የሚውለው ወንጀል ለመከላልና ወንጀል ተብሎ በህግ የተደነገገ ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ ለመቆጣጠር ነው። በዚህ መሠረት የወንጀል ስነ ስርአት ህግ ትረጉምና አላማ፣ የወንጀል ፍትህ ሂደት አጀማመርና መቋረጥ፣ ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ ምርመራ የማከናወን፣ ግዜ ቀጠሮ፣ ዋስትና፣ በዐቃቤ ሕግ ክስ መመሥረትና ምስክር መፈተንን

የመሣሰሉ ወሣኝ ሂደቶ ላይ በማተኮር ሕጉና አተገባበሩ ምን እንደሚመስል በጽሑፉ ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል።

ተጨባጭ ጉዳዮች ላይ በመንተራስ መለማመጃ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ ፅሁፉ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አንድ

የወንጀል ህግ ሥነሥርዓት ትርጓሜ እና ዓላማ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምን እንደሆነ ይተነትናሉ፤
- ሕገ መንግሥቱ እና የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ያላቸውን ግንኙነት አውቀው ለተግባራዊነታቸው በፅናት ይሠራሉ፤
- በሀገራችን ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ህጎች ያብራራሉ፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ ዋና ዋና ፅንሰ ሃሳቦች ምን እንደሆኑ በቅድሚያ መታወቅ ስላለባቸው እንዲብራሩ ይደረጋሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ራሱ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምንድነው የሚለው ይዳሰሳል፡፡ ከዚህ ሌላ ማንኛውም በአንድ አገር ያለ ሕግ የሕጎች ሁሉ የበላይ ከሆነዉ ከሕገ መንግሥት አንፃር መታየት ስላለበት የሥነ ሥርዓት ሕጉና ሕገ መንግሥቱ ያላቸው ትስስርም አብሮ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

በታዋቂው ብላክስ የሕግ መዝገበ ቃላት ትርጓሜ መሠረት የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት የሚከተለው ፍቺ ተሠጥቶታል፡-

Criminal procedure means the rules governing the mechanism under which crimes are investigated, prosecuted, adjucated, and punished. It includes the protection of accused persons constitutional rights.

ሕጎች በአጠቃላይ ከይዘታቸው አንፃር ዋና ሕጎች (substantive laws) **እና ቅፅል ሕጎች** (adjective laws) **ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። መሠረታዊ ሕጎች የሚባሉት መብት፣ ግዴታ እና ተጠያቂነትን ኃላፊነትን**(liability) **የሚመለከቱ ሲሆን፣ ቅፅል ሕጎች ደግሞ እነዚህ በሕግ ላይ የተመለከቱ መብት፣ ግዴታ፣ ተጠያቂነትና ኃላፊነት በአግባቡ በተግባር ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ የሚገዙ ናቸው። ቅፅል ሕጎች እንደገና የሥነ ሥርዓት** (procedural) **እና የማስረጃ** (evidentiary) **በመባል በሁለት ይከፈላሉ። ከላይ ስለ ወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ከተሰጠው ትርጓሜ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ወንጀልን የሚያቋቁሙ መስፈርቶችን የሚደነግገው ዋናው የወንጀል ሕግን በሥራ ላይ የሚያውለው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ነው። ወንጀል ተፈፀመ ከተባለ በዋነኛነት በፖሊስ ወይም በዓቃቤ ህግ ምርመራ ይጣራል፤ በቂ ማስረጃ ከተገኘ በዐቃቤ ሕግ ክስ ይመሠረታል፤ ከዚያም ጉዳዩ በፍ/ቤት ታይቶ ጥፋቱ ከተረጋገጠ ተገቢው ቅጣት እንዲወሰን ይደረጋል።**

ወንጀል የሠራ እንዲጠየቅ ማድረግ የማነበረሰቡን ጥቅም የሚያስጠብቅ ቢሆንምሂደቱ፤ አጠፋ የተባለውን ሰው ሰብዓዊ መብቶች የሚጥስ መሆን የለበትም። የማነበረሰቡን ጥቅምና የግለሰቡን መብት በተቻለ መጠን በሚያስታርቅ መልኩ ሕጉ ሥራ ላይ መዋል አለበት። የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዋና ዓላማም ይህ ዕውን እንዲሆን ማድረግ ነው። ወንጀል ፈፃሚን ለይቶ አጣርቶ የማግኘት ሂደት በእጅጉ ከዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ጋር የተቆራኘ ነው። የሰብዓዊ መብቶች መከበር ደግሞ ዴሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር በሠፈነበት አገር ወሣኝ በመሆኑ በቂ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። ሃገራት የጉዳዩን አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ቸምር ይሰጡታል። ከላይ ስለወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ከተሰጠው ፍቺም ለማረጋጥ እንደሚቻለው በሂደቱ ምንጊዜም ቢሆን የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር አለባቸው።

በሃገራችን ያሉት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች በሁለት ዋና ዋና ክፍል ሊመደቡ ይችላሉ። እነርሱም የሕገ መንግሥት መሠረት ያላቸው የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች

(constitutional criminal procedure rules) እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓትን ጨምሮ በሌሎች ሕጎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች (statutory criminal procedure rules) ናቸው::

ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አንድ ሦስተኛውን ቦታ የሚሰጠውና የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት መሰረታዊ ድንጋጌዎችን ያካተተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት እንደሌሎች ሃገሮች ሁሉ በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙና የታሰሩ ሰዎች ጉዳያቸው ሊስተናገድበት ስለሚገባበት ሁኔታ እና ስለ ሰብዓዊ መብታቸው አጠባበቅ ድንጋጌዎች አካቷል:: በህገ መንግስቱ ለፌዴሬሽን ም/ቤት የተሰጠውን ሰልጣን ማክበር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ሁልጊዜ አግባብነት ያላቸውን የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ተርጉመው ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል:: ለምሳሌ በህገ መንግሰቱ አንቀጽ 19/5 ስር በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው (inadmissible) ነዉ:: በተጨባጭ ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች አንጻር ታይቶ ማሰረጃው በማስገደድ የተገኘ ነው ወይስ አይደለም? ተብሎ በዐ/ህግ ና በዳኞች መወሰን አለበት:: ህገ መንግስቱ የመጠበቅ፣ የማክበር፣ የማስከበርና ተፈፃሚነቱ የማረጋገጥ ድርብ ሃላፊነት የተጣለባቸው በመሆኑ::

በሃገራችን ለግማሽ ምዕት ዓመት ያክል በሥራ ላይ የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተሽሮ በአዲስ የወንጀል ሕግ ተተክቷል:: ነገር ግን የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓቱ የተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን በሥራ ላይ ለማዋል ወጥቶ በሥራ ላይ የነበረ ቢሆንም አሁንም ድረስ ፀንቶ ይገኛል::

ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተጨማሪ ግን ሌሎች የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ሕጎችን ያካተቱ ሕጎችም የሚገኙ ሲሆን ለአብነት ያክል የወንጀል ህጉ፣ አደገኛ ቦዘኔነትን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 384/96 እና የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 ተጠ ቃሾች ናቸው::

በሕገ መንግሥቱ፣ በወንጀል ሕጉ ና በወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕጐቹ ተደንግገው የሚገኙት ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች ብቻ ሣይሆኑ የወንጀል ማስረጃን ጭምር የሚመለከቱ ናቸው::

በዘርፉ ሙህራን ዘንድ የሚንፀባረቀው የሃሳብ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዋናነት ማስረጃን በተመለከተ ሀገራችን የሲቪል ሎው የህግ ሥረዓትን ከሚከተሉት ሃገራት ተርታ ስለምትመደብ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን እንደሚከተሉ ሃገራት ራሱን የቻለ የማስረጃ ሕግ የላትም:: ከማስረጃ ጋር የተየያዙ ድንጋጌዎች የሚገኙት በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተካተው ነው::

የመወያያ ነጥቦች

1. የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምንድነው ?
2. የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ና የአንድ ሃገር ሕገ መንግሥትን ምን ያገናኛቸዋል?
3. በሃገራችን የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን በየትኞቹ ሕጎች ውስጥ እናገኛቸዋለን?
4. የወንጀል ህግ ማስረጃስ በየትኞቹ ሕጎች ውስጥ ይገኛል?
5. ህግ መንግሰታዊ መሰረት ያላቸውን የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ተርጉሞ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ከዐ/ህግ እና ዳኞች ምን ይጠበቃል) በዚህ ረገድ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ህግ መንግስቱን ለመተርጎም ከተሰጠው ስልጣን ጋር እንዴት ያዩታል)

ምዕራፍ ሁለት

2. የወንጀል ፍትሕ ሂደት አጀማመርና መቋረጥ

የሚጠበቁ ውጤቶች፤

ሠልጣኞች ይህንን የሥልጠናውን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የወንጀል ፍትሕ ሂደት እንዲጀመር የሚያስፈልጉ ሕጋዊ ቅድመ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ይረዳሉ፤
- የወንጀል ፍትሕ ሂደቱ አንድ ጊዜ ከተጀመረ በኋላ የሚቋረጥባቸውን ሕጋዊ መንገዶች አውቀው በሥራ ላይ ያዉላሉ፤

የወንጀል ሕግ ሲጣስ የጉዳዩ መታየት እንዴት እንደሚጀመር በዚህ ክፍል ይታያል። የወንጀል ፍትሕ ሂደት አንድ ጉዞ ከተጀመረ በኋላ በሕግ ላይ የተቀመጠውን ሥርዓት ተከትሎ ሊጠ ናቀቅ ሲችል ሊቋረጥ የሚችልባቸውም መንገዶች ተካተዋል።

2.1. የወንጀል ፍትሕ ሂደት አጀማመር

የወንጀል ሕግ የወንጀል ድርጊት ሲፈፀም ጉዳዩ በሚመለከተው የፍትሕ አካል ታውቆ በዋነኛነት የምርመራ ሥራ የሚጀመርበት የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሥርዓት አለው። በሃገራችን ወንጀሎች በሁለት ዋና ዋና መደቦች በዐቃቤ ሕግ የሚቀርቡ /የወንጀል ክስ ተብለው የሚታወቁ/ እና በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ተብለው ይከፈላሉ። ይህ በወንጀል ሕጉ ላይ የተደረገው ክፍፍል ወንጀሎቹ ተፈፀሙ ከተባለ በኋላና ጉዳዮቹ በክስ ሂደት የሚስተናገዱበት ሥርዓት ላይ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል። የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ ማቅረብ እና

የእጅ ከፍንጅ የወንጀል አፈፃፀም ሁኔታ መኖር ናቸው። እነዚህ ሁለት መንገዶች የየራሣቸው የተለያየ ባህሪ ስላላቸው እንደሚከተለው ይዳሰሳሉ።

2.1.1. የወንጀል ክስ(Accusation) እና የግል ተበዳይ አቤቱታ(Complaint)

በመርህ ደረጃ ማንኛውም ሰው ወንጀል ሲፈፀም ካየ ወይም ወንጀሉ ሲሠራ ያልተመለከተም ቢሆን መሠራቱን ካወቀ ለሚመለከተው የፍትሕ አካል የማስታወቅ መብት አለው። በመሠረቱ ሁኔታውን ለፍትሕ አካላት ማስታወቅ ግዴታ አይደለም። ነገር ግን አለማስታወቁ በግለሰብ ና ማኅበረሰብ ህልውና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ከባድ አደጋ በማገናዘብ በልዩ ሁኔታ ማስታወቅ እንደ ግዴታ በሕግ ላይ ሊቀመጥ ይችላል። ከነዚህ ህጎች ውስጥ የወ/ሕ/አንቀፅ 254፣ 335 እና 443፤ የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 60/89 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 81-82 የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 12 መጥቀስ ይቻላል።

ወንጀል የሚባሉ ተግባራት የኅብረተሰብን ሕልውና የሚፈታተኑ ሠላምና መረጋጋትን የሚያደፈርሱ በመሆናቸው በመሠረቱ ተፈፅመው ሲገኙ ጉዳዩ በፖሊስ/ ዓቃቤ ህግ ተጣርቶ አጠፋ የተባለውን ሰው ለማስጠየቅ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ካለ በዐቃቤ ሕግ ለፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ጉዳዩ መታየት አለበት። ይሁንና አንዳንድ ጉዳዮች ከማኅበረሰባዊ ገፅታቸው ይልቅ ግላዊ ባህሪያቸው ይጐላል። ስድብ፣ ዛቻና እጅ ዕልፈት የመሣሠሉ ቀላል ጉዳዮች በቀጥታ የሚጐዱት በደሉ የደረሰበትን ነው። ተበዳይ ወገን ፍትሕ ጠይቆ ሕጋዊ ምላሽ ካላገኘ የራሱን ዕርምጃ ወደ መውሰድ ስለሚያመራ ጉዳቱ ለሁሉም የኅበረተሰቡ አካል ነው። ሌላውም ተመሣሣይ በደል ሲደርስብኝ መፍትሔ አላገኝም ብሎ ካሰበ የበቀል ተግባር ውስጥ ሊገባ ስለሚችል አደጋው የከፋ ነው። እዚህ ጋር መታየት ያለበት በእንደዚህ ዓይነት ቀላል ጉዳዮች የተበደለው ወገን መፋረድ ካልፈለገ አጠፋ የተባለውን ሰው እንዲጠየቅ ማድረግ ምን ዓይነት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ ይኖረዋል? የሚለው ነው። በዚህ ሁኔታ አጠፋ የተባለውን መቅጣቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ለዚህም ይመስላል በወንጀል ሕጋችን በሕግ አውጪው ቀላል ተብለው የተገመቱ የወንጀል ተግባራትን በተመለከተ ተጐዳ የተባለው ሰው ክስ ካላቀረበ በስተቀር በወንጀል አያስጠይቁም ተብሎ የተደነገገው። በዚህ ሃሳብ የሰልጣኞች አምነት ምን ይመስላል?

የተሻረው የወንጀለኛ መቅጫሕግ ላይ የተበደለው ወገን ሲሞት በግል አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮችን በቅርብ ዘመዶች መቅረብ እንደሚችሉ የ1949 ዓ.ም የወነወጀል ህግ በአንቀፅ 218 በግልፅ ተደንግጎ የነበረ ሲሆን ሕጉ ሲሻሻል ግን እነዚህ አጠቃላይ ድንጋጌዎች

እንዲወጡ ተደርገዋል። በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች ተበዳዩ የወንጀሉን ድርጊት ወይም ወንጀል አድራጊውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሦስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ለሕግ አስከባሪ አካላት መቅረብ አለበት። ያለ በቂ ሕጋዊ ምክንያት ከዘገየ አቤቱታውን መቀበል አይቻልም /የወ/ሕ/አ 213/። ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች በወቅቱ ካልቀረቡ ምርመራም ጭምር መጀመር ስለሌለበት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

በመርህ ደረጃ ማንኛውም ወንጀል በሕግ አስከባሪ የሚቀርብ ነው። የተበደለው ወገን ክሱን አልፈልግም ቢልም ጉዳዩ ሕዝብን የሚመለከት በመሆኑ በፍትሕ አካላት መስተናገዱ ይቀጥላል። ነገር ግን በሕግ አውጪው የወንጀሉ ባህሪ እና ክብደት ከግምት ገብቶ በልዩ ሁኔታ በግልፅ ተለይቶ የተበደለው ወገን ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ክስ ማቅረብ መፈለግ እንደ ቅድመ ሁኔታ (condition precedent) ከተቀመጠ ይህ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ሣይሟላ ክስ ማቅረብ አይቻልም። በወንጀል ሕጋችን ውስጥ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች በተለያየ መልክ ተቀምጠው ይገኛሉ። ለመጥቀስ ያክል በቀጥታ ወንጀሉን በሚደነግገው አንቀፅ ሥር /የወ/ሕ/አ 580 እና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ በምዕራፍ ውስጥ በሚገኝ አንድ የሕግ ድንጋጌ ውስጥ /የወ/ሕ/አ 664/ የመሣሰሉትን ማስቀመጥ ይቻላል።

መልመጃ

1. በመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 አንቀጽ 40/2 መሰረት በመገናኛ ብዙሃን የስም ማጥፋት የተፈጸመበት ሰው ካለምንም የምርመራ ሂደት በቀጥታ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል ደንግጓል። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 43/7/ መሰረት ክስ የማቅረብ መብት በቀጥታ ለግል ተበዳዩ ተሰጥቷል ተግባራዊነቱ ምንያህል ነው?
2. ህትመቱ እንዲወረስ ከማድረግ ረገድስ ያለው ሁኔታ?
3. በአንድ በግል አቤቱታ በሚያስቀጣ ወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰዉ በችሎትዎ ፊት እንደቀረበ ያስቡ። ይህ ሰዉ ክሱን ከሰማ በኋላ ተበዳይ አቤቱታ አላቀረበብኝም፣ ይልቁንም በአካባቢያችን አዛዉንት አማካይነት ታርቀናል፣ ክሱ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ሆኖ እያለ ለምን እከሰሳለሁ ፍርድቤቱ መፍትሄ ይስጠኝ ብሎ ጥያቄ አቀረበ። እንዲህ ያለ ጥያቄ ለማንሳት ተከሳሹ ምን የህግ መሰረት አለዉ ምን መፍትሄ ይሰጡታል ክሱን ያሰናብቱታል ወይስ ጥያቄዉን ያሰናብቱታል?

ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስም ሆነ የግል አቤቱታ ከቀረበለት ምርመራ እንዲጣራ ለሚመለከተው የፖሊስ አካል ማስተላለፍ አለበት ወይም በራሱ ማጣራት አለበት። በአዋጅ ቁጥር 691/2003 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 16/5 መሠረት ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ የማዘዝ ሥልጣን ጨምሮ በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ የማካሄድ፣ የመምራት፣ የመቆጣጠር፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረን ምርመራ የማቋረጥ ሙሉ ሥልጣን ተሠጥቶታል። ፖሊስ/ መርማሪው ከየትም ወገን የቀረበን የወንጀል ክስ ተቀብሎ የማጣራት ኃላፊነት ስላለበት ከዐቃቤ ሕግ የቀረበም ቢሆን የተለየ አያደርገውም /የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 22 እና 24/። በተጨማሪም ማንኛውም መርማሪ የተጀመረውን ምርመራ ለበላይ ዓቃቤ-ህጉ የማስታወቅ ግዴታ አለበት። በአዋጅ ቁጥር 691/2003 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 16/5 መሠረት ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ወንጀል ላይ የሚካሄዱ ምርመራዎች የመምራት ስልጣን ብገለጽ ተሰጥቶታል።

መልመጃ

1. ሰልጣኞች ከመጡበት አካባቢ ሁኔታ አንፃር ዐቃቤ ሕግ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ የማዘዝ ሥልጣን ጨምረሮ በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ የማካሄድ፣ የመምራት፣ የመቆጣጠር፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረን ምርመራ የማቋረጥ ሙሉ ሥልጣኑ እንዴት ተግባራዊ ያደርገዋል?
2. የተጠያቂነት ወሰኑ ምን ይመስላል?

የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ የሚቀርበው በቃልም ሊሆን ይችላል። ዋናው ነገር ቃሉን የሚቀበለው ፖሊስ አቤቱታውን መዝግቦ በማንበብ አቤቱታ አቅራቢን ቀኑን ጭምር መዝግቦ ማስፈረሙ ላይ ነው (የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 14)። ሰውን በሀሰት የመወንጀል አሠራርን ለመከላከል ይህ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ጠቋሚው ወይም አቤቱታ አቅራቢው አልፈርምም የሚል ከሆነስ የሚል ጥያቄ ከተግባራዊ ልምድ እነጻር ሲነሳ ይስተዋላል።

መልመጃ

1. አንድ ሰዉ በፖሊስ ጣቢያ ቀርቦ የነፍስ ግድያ ወንጀል የተፈጸመ መሆኑን ሪፖርት ካደረገና መርማሪዉም ይህን ሪፖርት ከመዘገበ፣ ጠቋሚዉንም በዝርዝር ስለወንጀሉና ስለወንጀለኛዉ ጠይቆ ከመዘገበ በኋላ እንዲፈርም ሲጠይቀዉ አልፈርምም፣ ስሜም በምስጢር ይያዝልኝ ወንጀሉ በተደራጀ ቡድን የተፈጸመ

በመሆኑ ለበቀል ያጋልጠኛል በማለት ለመርማሪዉ ነግሮ ከምርመራ ክፍሉ ወጥቶ በመሄዱ መርማሪዉ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነሥርዓቱ መሰረት ለመፈጸም ተቸግሯል፡፡ ምርመራዉን በጋራ የሚያከናዉኑ ወይም የሚመሩ ዐቃቤህግ እንደሆኑ ራስዎን ያስቡና ለመርማዉ መፍትሄ የሚሆን ነገር ይምከሩት፡፡

2. ከምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅና ክንጀሎች ክብደት አኳያ እንዴት ይመለከቱታል

ጠkሚው ማንነቱን ሣይገልፅ የሚያቀርበው ክስ በጥንቃቄ መታየት አለበት፡፡ አንድ ሰው ማንነቱን ደብቆ ክስ የሚያቀርበው የግድ ሌላውን ለመጉዳት ብሎ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ የበቀል ሥጋት ያደረበት ራሱን መደበቅ አማራጭ አድርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በአንድ በኩል ወንጀል ፈፃሚን እንዲጠየቅ የማድረግ የማነበረሰብ ጥቅም ያለ ሲሆን በሌላ በኩል ንፁህ ሰው ያለ ጥፋቱ ክስ ቀርቦበት ሰብዓዊ መብቱ እንዳይጣስ የማድረግ ተነፃፃሪ ጥቅም አለ፡፡ ሕጉ ሁለቱን ጥቅሞች ለማስታረቅ አማካይ የሆነ አማራጭን ነው የሚከተለው፡፡

ጠቋሚው ማንነቱን ካላሣወቀ ምርመራ በመርማሪው የሚጣራው ጥቆማው ከፍ ያለ የሕግ መጣስን የሚመለከት ሆኖ በአካባቢያዊ ሁኔታዎች የተደገፈና የሚታመን መስሎ ከተገኘ ብቻ ነው (የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 12)፡፡ ይህም ሕጉ ኃላፊነቱን የሚወስድ ወገን ከሌለ ለዜጎች መብት ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ያረጋግጣል፡፡ መርማሪው ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ በሚሰጥ መልኩ በመሥራት ጠቋሚው ያልታወቀን ክስ በተመለከተ ምርመራ ከመጀመሩ በፊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ ከፍ ያለ የሕግ ጥሰት ምን እንደሆነ በሕጉ ላይ በግልፅ አልተቀመጠ ም፡፡

የወንጀል የፍትሕ ሂደት በወንጀል ክስ ወይም በግል አቤቱታ ሲጀመር በንፁህ ዜጋ ላይ ያለአግባብ ክስ እንዳይቀርብ ሕጉ ያስቀመጣቸውን አሠራሮች መከተል አስፈላጊ ነው፡፡ በሀሰት ሰውን የወነጀለ እንዲታወቅ ሊያደርግ በሚችል መልኩ የአቤቱታ አቅራቢን ማንነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ሆን ብሎ ሌላውን ለመጉዳት የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ በወ/ሕ/አ 447 መሠረት ያስጠይቃል፡፡ የተከሰሰ ሰው ነፃ በወጣ ጊዜ ሁሉ ክሱን ያቀረበ ወገን ራሱ በወንጀል ይጠየቃል ማለት አይደለም፡፡ መተኮር ያለበት ንፁህ የሆነን ሰው ወንጀል እንዳልፈፀመ እየታወቀ ሆነ ተብሎ የመወንጀል ተግባር መኖሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ ዜጎች ተበረታተው ወንጀልን ለመከታተል ዕገዛ እንዲያደርጉ እና በሌላ በኩል ያለ አግባብ ወንጀል

ያልሠራ ሰው ክስ ቀርቦበት ሰብዓዊ መብቱ እንዳይገፈፍ አተገባበር ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

2.1.2. የእጅ ከፍንጅ ወንጀል አፈፃፀም

የምርመራ ሥራ እንዲጀመር ሁልጊዜ የግድ አቤቱታ መቅረብ የለበትም። ወንጀሉ እጅ ከፍንጅ የሚባለው ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን በመፈጸም ሂደት ላይ እያለ ወይም ለመፈፀም ሲሞክር ወይም ወንጀሉን እንደፈፀመ ከቦታው ሳይርቅ ወዲያውኑ ከተያዘ ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወንጀል መፈፀሙን ና ፈፃሚውን በቀላሉ መለየት ስለሚቻል ንፁህ ሰው ያለ አግባብ ሊወነጀልበት የሚችልበት አጋጣሚ ጠባብ ነው። የወንጀል ፍትሕ ሂደት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወዲያው መቀጠሉ የግድ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን በግል አቤቱታ ብቻ ለሚያስጠይቁ የወንጀል ተግባራት ምንም እንኳን ወንጀሉ እጅ ከፍንጅ የተፈፀመ ቢሆንም መርማሪው የተበዳዩን ይሁንታ ሣያገኝ ጉዳዩን ማስተናገድ መጀመር አይችልም። ተበዳዩ ፈቃዱን ከገለፀ ግን በተመጣጣይ ወዲያው ሂደቱ ሊቀጥል ይችላል።

መልመጃ

1. አንድ ተጠርጣሪ ለጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ ተይዞ በችሎትዎ ቀረበ። የተጠረጠረበት ጉዳይ ከአንድ በመንገድ ዳር ከቆመ የቤት መኪና ላይ መብራትና የኋላ ትዕይንት መመልከቻ መስተዋት ሲፈታ እጅከፍንጅ የተያዘ መሆኑ ሲሆን፣ የራሴ መኪና ነዉ ቢልም ማስረጃ ሊያቀርብ ባለመቻሉ ይህን ጉዳይ ለማጣራት ጊዜ ይፈቀድልኝ በማለት መርማሪዉ ጠይቋል። ተጠርጣሪዉ ደግሞ መኪናዉ የሚች አባቱ መሆኑን፣ ብቸኛ ወራሻቸዉ እርሱ መሆኑን፣ እናቱ ለጊዜዉ በአካባቢዉ የሌሉ መሆኑን፣ በርግጥ መኪናዉ ገና በርሱ ስም ያልተመዘገበ መሆኑን፣ ስለዚህ በአባቱ መኪና ጉዳይ ሰርቀሃል ተብሎ ሊከሰስ እንደማይገባዉና የጊዜ ቀጠሮ ሊሰጥ እንደማይገባዉ ይልቁንም ይህ ነገር በዚሁ ተቋርጦ ያለቅድመሁኔታ እንዲለቀቅ ጠየቀ። ይህን

ጉዳይ እንዴት እነደሚያስተናግዱት ከባልደረባዎ ጋር ይወያዩ፣ ምፍትሄዎቻችሁን ርስበራስ ተተቻቹ?

2. የተፋጠነ የክርክር ሂደት/RTD/ እና የእጅ ከፈንጅ ወንጀሎች ትስስር ግለፁ?

የእጅ ከፍንጅ ወንጀሎች የሚባሉት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 19/1 እና 20 ሥር የተጠቀሱት ብቻ አይደሉም። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 19/2 እና 20 ሥር የተጠቀሱት ሌሎች መሠል ሁኔታዎችም በሕጉ እንደ እጅ ከፍንጅ ወንጀሎች ይቆጠራሉ። እነዚህም ወንጀል አድራጊው የወንጀል ተግባሩን ከፈፀመ በኋላ ወዲያውኑ ሲሸሽ ምስክሮች ወይም ሕዝቡ የተከታተሉት ወይም የሕዝቡ ጩኸትና እሪታ የተሰማ እንደሆነ ወይም ወንጀል ተፈፀመ የተባለበት ቦታ ወዲያውኑ ፖሊስ የተጠራ እንደሆነ ወይም ወንጀሉ ሲፈፀም ወይም እንደተፈፀመ በቦታው የድረሱልኝ እሪታ የተሰማ እንደሆነ ነው። ወንጀለኛው ወዲያው አለመያዙ የእጅ ከፍንጅ ወንጀልነቱን አያስቀረውም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በቀላሉ ወንጀሉንና የወንጀል ፈፃሚውን ማንነት መለየት ስለሚቻል የወንጀል ፍትሕ ሂደትን ያለሌላ ቅድመ ሁኔታ ሊጀመር ይችላል። ንፁህ ሰው ሊወነጀልበት የሚችልበት አጋጣሚም ጠባብ ነው የሚሆነው።

ወንጀል የሌላውን ሰብዓዊ መብት የሚጋፋ ማንበራዊ ጠንቅ ነው። የተበደለው ወገንም ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ያስፈልገዋል። በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ጊዜ በተጨባጭ ወንጀሎች ሲፈፀሙ በአፋጣኝ ያጠፋው ሰው ተይዞ በሕግ አግባብ እንዲጠየቅ መደረግ አለበት። የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት ሰብዓዊ መብቱም ይረጋገጥለታል።

በሌሎች ሀገሮችም የእጅ ከፍንጅ ወንጀሎች በተለየ ሁኔታ ነው የሚስተናገዱት። በእንግሊዝ Next Day Justice በሚባል አሰራር በተፋጠነ ሁኔታ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል። በፈረንሳይ ሂደቱ Real Time Dispatch ተብሎ ይታወቃል። በሀገራችንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በስፋት እየተተገበረ ነው። ቀደም ብሎ ይህ አሰራር በቁልቢ ገብርኤል አመታዊ ሃይማኖታዊ ሥርአት ወቅት ብቻ የተወሰነ ነበር። አሁን ግን ጠቀሜታው በተጨባጭ ተረጋግጦ በመላ ሃገሪቱ በመተግበር ላይ ነው። በዚህ መሰረት

እየተሰራ ወንጀል ተፈጸመ በተባለበት እለት ሁሉ በተፋጠነ ሁኔታ ለፍ/ቤት ጉዳዩ ቀርቦ እልባት እያገኘ ነው፡፡

መለማመጃ

1. በእጅከፍንጅ ክስ ጊዜ የተከሳሽ የመከላከል መብት ምን ያህል ሊጠበቅ ይችላል በዚህ አይነት ጉዳይ ተከሳሹ ጠበቃዬ ጋር ተመካክሬ፣ የመከላከያ ማስረጃ አፈላልጌ ተዘጋጅቼ ለክሱ መልስ እሰጣለሁ ለዚህም ቀጠሮ ይሰጠኝ፣ እስከዚያዉ በዋስ ልቀይ የሚል ጥያቄ ቢያቀርብ ፍርድቤቶች ይህን ጥያቄ ይቀበላሉ?
2. የማታለል፣ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ ቆርጦ መስጠት፣ የአእሙሮአዊ ንብረት ጥበቃ አዋጅ ድንጋጌዎች መተላለፍ የመሳሰሉት ወንጀሎች በተፋጠነ ችሎት ሲዳኙ ይሥተዋላል፡፡ አግባብነቱ እንዴት ይመለከቱታል?
3. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከጳጉሜ 5 ጀምሮ እሰከ ሰኔ 30/2000 የተስተናገዱት የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ጉዳዮች አንደሚያረጋግጡት 91% የሚሆኑት ጉዳዮች እልባት ያገኙት በእለቱ ሲሆን 7% የሚሆኑት ደግሞ በማግሰቱ ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ ሂደቱ በራሱ ተከሳሾች እንዲያምኑ ስለሚገፋፋ እና በዚሁ መልኩ እያመኑ አብዛኛው ጉዳይ ስለሚወሰን የተፋጠነ ፍትህ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ጊዜ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በተፋጠነ ሁኔታ ሂደቱ ተጀምሮ መጠናቀቅ አለበት የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ከተከሳሾች የመከላከል መብት አንጻር እንዴት ይታያል?

2.2. የወንጀል ፍትሕ ሂደት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

የወንጀል ሕግ ጥሰት ካለ ያጠፋ እንዲጠየቅ ሂደቱ ቀደም ብሎ በተገለፁት መንገዶች የሚጀምር ሲሆን፣ ሙሉ ሂደቱ በሕግ አግባብ ሳይጠናቀቅ ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ የወንጀል ሕጉ ሲሻሻል በግል ተበዳይ አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች የሚቋረጡበትን ሁኔታ የሚዘጉበት ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች ሳይካተት ቀርቷል፡፡ የወ/መ/ህ/ አንቀጽ 221 እንደነበረ ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡፡ እንም እንኳ ለትርጉም የተጋለጠ ቢሆንም በወ/ሕ/አ

70/1 መሠረት አድራጊው የፈፀመው ወንጀል በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጣና ተበዳዩ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ የፈቀደው ድርጊት ከሆነ አያስቀጣም፡፡ አንዴ ክስ ከቀረበ አሁን ባለው ሕግ ክስ በተበዳይ አቤቱታ የሚቀርብ ቢሆንም ማቋረጥ አይቻልም የሚለው ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ብሎ መከራከር ይቻላል፡፡ ሌላው ሊነሣ የሚገባው ነጥብ ተበዳይ የተባለው ሰው ክሱን አቅርቦ ከሞተ በኋላ ክሱ ሊቀጥል ይገባል ወይ? የሚለው ነው፡፡ ግለሰቡ ቢሞትም በእርግጥ ክሱ መቀጠል አለበት፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በግል አቤቱታ የሚቀርበው የወንጀል ተግባሮች በሕጉ ይጎዳሉ ተብለው የሚገመቱት የተጐዳውን ወገን ነው፡፡ ይህ ከሆነ የሟቹ ወራሾች ቀርበው ክሱን አንፈልግም ብለው ካረጋገጡ ክሱ መቀጠሉ ጠቀሜታ አይኖረውም፡፡ መንግሥትና ሕዝብ በእንደዚህ ዓይነት ግላዊ ባህሪ ባላቸው የወንጀል ተግባራት ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም፡፡ እራሱ ሕግ አውጪው ጉዳዮችን ለይቶ ግላዊ ናቸው ብሏቸዋል፡፡

መልመጃ

1. አንድ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስከስስን ወንጀል ተከትሎ ፖሊስ ነገሩን ካለመገንዘብ ምርመራ ከጀመረ በኋላ ተበዳይና ተጠርጣሪ ታርቀዉ ቀርበዉ ተበዳዩ እኔ ቀድሞም ክስ አላቀረብኩም ከዚህም በላይ ታርቀናል ስለዚህ የተጀመረዉ ምርመራ እንዲቆም እጠይቃለሁ አለ፡፡ መርማሪዉ በዚህ ሁኔታ ምርመራዉን አቋርጦ መዝጋት አለበት ወይስ ለዉሳኔ ለዐቃቤህግ ዐቃቤህግ ደግሞ ለፍርድቤት ማቅረብ አለባቸዉ?

በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶች ጥያቄዉ በተጐጂው ሲቀርብ በየትኞቹ የፍትሕ አካላት ነው ሊቋረጡ የሚችሉት? የሚለው በሕጋችን ላይ በግልፅ አልተቀመጠም፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት በ 1949 የወንጀለኛ አንቀፅ 221 መሰረት ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ በግል አቤቱታ የቀረበን ክስ ማንሳት እንደሚቻል ተገልጧል፡፡በዚህ እረገድ ክስ ከቀረበ በኋላ ስለሚነሳበት ሁኔታ በ1997 የወንጀል ህግ ላይ የተባለ ነገር የለም፡፡በአዲሱ የወንጀል ህግ ጉዳዩ በዝምታ መታለፉ እነዚህ ድንጋጌዎች የስነስርአት ህግ ድንጋጌዎች በመሆናቸው የስነ ስርአት ህጉ ሲሻሻል እልባት ይሰጣቸዋል የሚል ድምዳሜ መያዙን የወንጀል ህጉ አርቃቂ ቃለ ጉባኤ ያመለክታል፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዮቹ የግል ባህሪ ካላቸው ፖሊስ ምርመራ ማጣራት ከጀመረ በኋላ ክሱን እንደማይፈልግ በተበዳዩ ከተገለፀለት ይህንኑ አረጋግጦ መዝግቦ አስፈርሞ እራሱ ፖሊስ መዝገቡን መዝጋት ይችላል፡፡ የሚከለክለው ሕግ የለም የሚል ክርክር ይቀርባል፡፡ በሌላ በኩል ፖሊስ የሕግ ዕውቀቱ የዐቃቤ ሕግን ያክል ስላልሆነ ያለአግባብ ክሶችን በማቋረጥ ፍትሕ

ሊያዛባ ስለሚችል በምንም ዓይነት ሁኔታ ፖሊስ እራሱ ክስን የማቋረጥ ሥልጣን ሊሰጠው አይገባም። ሕግ አውጪው ይህንን ቢፈልግ በግልፅ ሥልጣኑን ይሰጠው ነበር የሚሉ ክርክሮች ይቀርባሉ።

በግል አቤቱታ የሚቀርብ ክስ በተበደለው ወገን ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ጥያቄ እንዲቀርብ ከተደረገ በyላ ጉዳዩ ፍ/ቤት ደርሶ እንዲkረጥ ከተደረገ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 220/3 መሠረት ተበዳይ ለመንግሥት ወጪ መክፈል አለበት። ጉዳዩ ከዚያም በኋላም እንደ አዲስ ሊታይ አይችልም የመጨረሻ ይሆናል።

ሌላው ክስ ሊቋረጥ የሚችልበት መንገድ በዐቃቤ ሕግ ክሱ እንዲነሣ ሲደረግ ነው። በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ውስጥ የነበሩት ክሱን ዐቃቤ ሕግ እንዲያነሣ የሚፈቅዱ ድንጋጌዎች በሙሉ በአዋጅ ቁ. 39/85 ተሽረዋል። አሁን ዐ/ሕግ ክስን ለማንሣት ያለው የሕግ ድጋፍ አዋጅ ቁ. 691/2003 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 16/5 እና 6 ነው። በዚህ አንቀፅ ዐቃቤ ሕግ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ማድረግ ወይም በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ የማንሣት ሥልጣን ተሠጥቶታል።

መልመጃ

1. በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ የማንሣት ሥልጣን ለዓቃቤህግ መሰጠቱ ፋዳው ምንድን ነው?
2. የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት አለ የሚባለው መቼ ነው?
3. ክስ ለማንሳት የሚረዱ ተጨባጭ የህግ ድንጋጌዎች ካሉ ግለፁ?

በምርመራ ላይ ያለን የወንጀል ጉዳይ ለማስቆም ግልፅ ሥልጣን ለፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተሠጥቶታል። የሚያነጋግረው አንድ ጊዜ ክስ ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ክስ ማንሣት ይችላል ወይ? የሚለው ነው። ሕጉ የሚለው በሕጉ መሠረት ክስ ያነሣል ነው። ክስ ለማንሣት በቀጥታ አይፈቀድም። በሕግ መሠረት ስለሚል ክስን ማንሣት የተመለከቱ ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች መፈለግ አለባቸው የሚሉ ክርክሮች ይቀርባሉ። በሌላ በኩል የዐቃቤ ሕግ ክስ የማንሣት መብት ሕጉ ሠጥቶታል። ክሱን ለማንሣት በቂ ምክንያት ካለ ሊቋረጥ ይችላል የሚሉ ክርክሮችም ይንፀባረቃሉ።

የመወያያ ነጥቦች

1. የወንጀል ፍትሕ ሂደት እንዴት ይጀመራል? ንፁህ ሰው ያለወንጀሉ እንዳይጠየቅ ሕጉ ምን ዓይነት ጥበቃ ያደርጋል?

2. እጅ ከፍንጅ ወንጀልን በተመለከተ በሕጉ ላይ የተጠቀሰው «ወዲያው» የሚለው ቃል እንዴት መተርጐም አለበት?

3. በፖሊስ የመብት ጥሰቶች እንዳይፈፀም በሕገ መንግሥቱ እና በወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ድንጋጌዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ከዐቃቤ ሕግ ምን ይጠበቃል? ከፍ/ቤትስ?

4. በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 12 ሥር የተደነገገው ከፍ ያለ የሕግ መጣስ ተግባር እንዴት መተርጐም አለበት?

5. የወንጀል መፈፀምን ለፍትሕ አካላት ማሣወቅ ግዴታ ነው ወይ?

6. በግል ለሚቀርብ አቤቱታ በወ/ሕ/አ 212 መሠረት ወራሽ ክስ ማቅረብ ይችላል ወይ ?

7. በግል አቤቱታ ብቻ የሚቀርብ ክስ መታየቱ ከቀጠለ በኋላ የተበደለው ወገን ቢሞት ወራሹ ክሱ እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላል ወይ?

8. ፖሊስ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶችን በተመለከተ ለተበደለው ወገን ጥያቄ ከቀረበለት በራሱ ክሱ ቀሪ እንዲሆን ማድረግ ይችላል ወይ?

9. በፌዴራልም ሆነ በክልል ባለው የሕግ ማዕቀፍ ዐቃቤ ሕግ ክስን ለማንሣት ሥልጣን አለው ወይ?

ምዕራፍ ሶስት

3. በምርመራ ሥራ የዐቃቤህግና የፍርድቤት ሚና

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ፡-

- መርማሪው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን ሊይዝባቸው የሚችልባቸው ሕጋዊ ሁኔታዎች አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ::
- መርማሪው ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን ሊይዝባቸው የሚችልባቸውን መንገዶች ይገልፃሉ፤
- በፍ/ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ ሊመስጠን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ተረድተው ይተገበራሉ፤
- ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ መርማሪው በብርበራ የወንጀል ፍሬዎችን ወይም ለወንጀል ማስረጃ የሚሆኑ ነገሮችን ለመያዝ ያለውን ሥልጣን ይዘረዝራሉ፤
- ከሕግ ውጪ የብርበራ ሥራ በመርማሪው መከናወን የሚያስከትለውን ውጤት ይተነትናሉ፤
- በተጠርጣሪ በወንጀል ማስረጃነት ደም መስጠትንና አሻራ ማንሣትን የመሣሰሉ ተግባራት በምን መልኩ በሕግ መሠረት ሊተገበሩ እንደሚችሉ ያስረዳሉ::

መርማሪው ወንጀል መፈፀሙን ካወቀ ምርመራ በማከናወን ማጣራት አለበት:: በምርመራ ሂደት ስለሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀጥለን እንመለከታለን::

3.1 የወንጀል ምርመራ አላማና መርሆ

ወንጀል ምርመራ ገና ወደፊት ሊፈፀም በሚችል፣ ሊፈፀም በዕቅድና በዝግጅት ላይ በሚገኝ፣ አፈፃፀሙ ተጀምሮ ባልተጠናቀቀ ወይም አስቀድሞ በተፈፀመ የወንጀል ጉዳይ ላይ ሊደረግ ይችላል፡፡ የወንጀል ምርመራ ወንጀል ለማወቅ፣ ወንጀል እንዳይፈፀም የማስቆም፣ ወንጀል ከተፈፀመ ጉዳቶችን የመቀነስ፣ የወንጀል ኢላማ የሆኑትን ሰዎች፣ ንብረቶች ወይም ጥቅሞችን የመከላከል፣ ወንጀል ፈፃሚዎችን ወደ ሕግ የማቅረብ ወይም የወንጀል ተጎጂዎችን መብቶችና ጥቅሞችን የማስከበር ዓላማ ሊኖረው ይገባል፡፡ የወንጀል ምርመራ ተግባራት የወንጀል ጉዳዮች ላይ መረጃን ወይም ማስረጃን ማፈላለግን፣ ማግኘትን፣ መተንተንን፣ ማደራጀትን፣ ማኖርን፣ ለሚፈለገው ዓላማ ዝግጁ ማድረግን ወይም አግባብነት ላላቸው አካላት ማስረከብን የሚያጠቃልል ነው፡፡

የወንጀል ምርመራ ሂደት የሕግ የበላይነት፣ የፍትሃዊነት፣ የግልጽነት፣ የተጠያቂነት፣ ለሕዝብ ደህንነትና ሰላም ቅድሚያ የመስጠት፣ ለጉዲዮችና ለሁኔታዎች እንዱሁም ለጥቆማዎች ወቅታዊ ምላሽ የመስጠት እና በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሚዛናዊ ውሣኔ የመስጠት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የወንጀል ምርመራ የሚካሄድባቸው ጉዳዮች፣ የወንጀል ምርመራ ዓላማ፣ ተግባራትና መርሆዎች የወንጀል ምርመራ ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ በነዚህ መርሆዎችና አላማዎች መመስረት አለበት፡፡

በወንጀል ምርመራ ሂደት ውስጥ የሚሰበሰቡ ማስረጃዎች ሕጉን ተከትለው የተገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በሕገ ወጥ መንገድ ወይም በሕግ ከሰፈረው ሥርዓት ውጭ በመሔዴ የተገኙ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት ተቀባይነት የማይኖራቸው ወይም ዋጋ የሌላቸው ስለመሆኑ ህገ-መንግስቱ በከፊል አስፍሮ ይገኛል፡፡

ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይገባ እና መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብት እንዳለው በሕገ መንግሥቱም ሆነ ሀገራችን ተቀብላ ባፀደቀቻቸው የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት እና ስምምነቶች ውስጥ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ይሁንና እነዚህ መብቶች ፍፁም ካለመሆናቸውም በተጨማሪ የሀገርን እና የሕዝብን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም በሰዎች ነፃነትና መብቶች በሚፈፀሙት የወንጀል ድርጊቶች ምክንያት አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ለመከላከል ሲባል በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረን ሰው በሕግ ፊት አቅርቦ ፍትሃዊ ውሣኔ እንዲያገኝ ለማድረግ የሚያስችል ማስረጃ ለመሰብሰብ ሲባል አግባብ ያለው ሕግ በሚደነግገው ሥርዓት መሠረት መያዝ፣ ማሰርና መበርበር ይቻላል፡፡በመሆኑም በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረን ሰው በሕግ ፊት አቅርቦ ፍትሃዊ ውሣኔ እንዲያገኝ የሚያስችል ውጤታማ የወንጀል ምርመራ ለማካሔድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አግባብነት ያላቸው ሕጎች በሚያስቀምጡት ሥርዓት መሠረት እና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ተጠርጣሪውን ለመያዝ፣ ለማሰርና ለመበርበር የሚያስችል አሠራር በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

`A **criminal investigation is an official effort to uncover information about a crime`.**

የወንጀል ምርመራ ማለት በተደራጀ ሁኔታ ከወንጀል ጋር በተያያዘ መረጃ ወይም ማስረጃ ለማግኘትና ለመሰብሰብ የሚደረግ ስራ ነው፡፡ መርማሪው ወንጀል ስለመፈፀሙ መረጃ ከደረሰው ወይም ካወቀ መርማሪው በተጨባጭ ማስረጃ ወንጀሉን ለማረጋገጥ ምርመራ ማከናወን አለበት፡፡ የቀረበው ክስ ወይም መረጃ ቢያጠራጥረውም ምርመራ መደረግ ያለበት ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ጠቋሚው ላልታወቀ ወይም ለታወቀ የወንጀል ክስ ነው፡፡ ሰውን ለመጉዳት ሲባል ሊቀርብ ስለሚችል የዚህ ዓይነት ክስ ላይ የግድ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ በምንም ምክንያት መርማሪው ምርመራ ለማጣራት ወደ ኋላ ማለት አይችልም፡፡ በሕግ አንድ ጊዜ የተጀመረን ምርመራ የማጣራት ሥራ ለማቋረጥ ለፖሊስ በሕግ በግልፅ የተሰጠው ሥልጣንም የለም፡፡ ለዓቃቤ ህግ ሲሆን የተለየ ስልጣን መሰጠቱ ከአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 16/5 መሰረተ መረዳት ይቻላል፡፡

በመርማሪው ምርመራ ሂደት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ማስረጃ ማሰባሰብ እና ተጠርጣሪን መያዝ ናቸው። ከመርማሪው ምርመራ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ከወ/መ/ሕ/ቁ. 22 እስከ 37 እና ከወ/መ/ሕ/ቁ. 49 እስከ 62 የሚገኙት ናቸው። ከጊዜ ቀጠሮ ውጭ የሚገኙት በዚህ ክፍል ይካተታሉ።

3.2. የማስረጃ አሰባሰብ

ተፈፀመ ስለተባለው ወንጀል መርማሪው ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ መፈለግ አለበት። ወንጀል ጠቋሚ ወይም የተበደለ ወገን ወይም ከሌላ ከማናቸውም ሰው ማግኘት የሚገባውን መረጃ መሰብሰብ አለበት። በተለይ ስለ ጉዳዩ ከሚያውቁ ተበዳይ እና ምስክር ላይ ቃል መቀበል አለበት። የምስክር ቃል ሲቀበል ማረጋገጥ ያለበት የሙያ ምስክር ካልሆነ የምስክር የግል አስተያየታቸውን ሣይሆን ወንጀል መፈፀሙን ያወቁበትን መንገድ ነው። በስሜት ሕዋሶቻቸው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ያወቁትን እንዲገልፁ መደረግ አለበት። በደፈናው ወንጀል መፈፀሙን አውቃለሁ የሚል አገላለፅ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። በምን ዓይነት ሁኔታ እንዳወቀ ነው በምስክር መረጋገጥ ያለበት። ምስክሩ ስለጉዳዩ ያውቃል ወይም አያውቅም የሚለው ላይ አጣርቶ መወሰን የሚመለከተው የፍትሕ አካል ኃላፊነት ነው። በዐይኑ ተመለከተ ወይም ከሰው ሰማ ወይስ በሌላ ተዘዋዋሪ መንገድ (ተጠርጣሪዉ ከወንጀሉ ቦታ ሲሄድ አየ?) ወይስ በሌላ ዘዴ ስለጉዳዩ አወቀ። ይህን ለይቶ ካላስቀመጠ ያለአግባብ ሰዎች እንዲወነጀሉ በር ሊከፍት ይችላል። ይህንን ለመከላከል መርማሪው በተጨባጭ ለቀጣዩ ምርመራ በሚረዳ እና ወንጀሉን ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ ቃል መቀበል አለበት።

በመርህ ደረጃ ማንኛውም ሰው በ መርማሪው ጥሪ ሲቀርብለት የመቅረብ፤ ለምስክርነት የቀረበ ሰው የሚሰጠው መልስ እራሱን የሚያስዎንጅለው እስካልሆነ ድረስ፣ ለሚቀርብለት ጥያቄ ሁሉ እውነተኛ መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት።፡ ፖሊስ ለምስክሮች ምንም ዓይነት የተሰፋ ቃል እንዲመሰክሩ መስጠት የለበትም። ምስክር ለመመስከር እየፈለገ ቃሉን ላለመቀበል ወደኋላ ማለት የለበትም።

መልመጃ

1. ምስክርን መደለል፣ የተስፋ ቃል መስጠት፣ ማስፈራራት፣ በኃይል መጠቀም፣ የመሳሰሉት የተከለከሉ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል በሥነምግባርና ጸረሙስና ልዩ የሥነሥርዓትና ማስረጃ ህግ አንድ የወንጀል ግብረአበር በሌሎች ግብረአበሮቹ ላይ እንዲመሰክር ከመከሰስ ነጻ የመሆን ጥቅም ሊሰጠዉ እንደሚችል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የጸረ ሽብርተኝነት አዋጁ ግልጽ ባይሆንም ከተጠርጣሪነት ወደ ምስክርነት የዞሩ ሰዎች በተግባር ያጋጥማሉ፡፡ እነዚህን ሁለት ሁኔታዎች እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? ከትርጉም አንጻር የሚያነሱት ሃሳብ ይኖር ይሆን?

በመርማሪው መሰባሰብ ያለበት ማስረጃ የሰው ብቻ አይደለም፡፡ የሰነድና የቴክኒክ ማስረጃም መሰባሰብ አለበት፡፡ ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ የተለመደዉ ከወንጀል ቦታ አሻራ መዉሰድ የመሳሰለ#ትን ማከናወን ይገባል፡፡ የሥነድ ማስረጃዎችም ከተገኙ ማፈላለግ ተገቢ ነው፡፡ ወንጀሉን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ማናቸውም ማስረጃዎች በመርማሪው መሰብሰብ አለባቸው፡፡

3.3. *መበርበርና መያዝ* (Search and Seizure)

የምርመራ አላማ ተፈፀመ የተባለን ወንጀል በማስረጃ ማረጋገጥ ነው፡፡ ለዚህ ተግባር መርማሪው/ፖሊስ ማስረጃን ፈልጐ ማግኘት አለበት፡፡ ተርጣሪውን በሚይዝበት ጊዜ በሰውነቱ ለወንጀሉ የሚሆን ማስረጃ ይዟል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር አካሉን መፈተሽ የለበትም፡፡ በተግባር ግን ማንኛውም የሚያዝ ሰው ተፈተሾ ነው በቁጥጥር ስር የሚውለው፡፡ ይህ የሚደረገው ተጠርጣሪው ወደ ማረፊያ ቤት በራሱ ወይም በሌላው ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል እቃ ይዞ እንዳይገባ ለመከላከል ይመስላል፡፡ ብርበራው መፈፀም ያለበት በተመሣሣይ ጸታ ነው፡፡ በብርበራ ማስረጃን ፈልጐ መያዝ የሚቻለው በህግ መሰረት በፍ/ቤት ትእዛዝና ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ ነው፡፡ ብርበራን የሚመለከቱት የወ/ወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 32 እና 33 ናቸው፡፡ ሁለቱንም በመቀጠል እንመለከታለን፡፡

3.3.1. በፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር ና መያዝ

በመሰረቱ መርማሪው የብርበራ ተግባር በማከናወን ለማስረጃ የሚሆን ነገር መያዝ የሚችለው በፍ/ቤት ትእዛዝ ብቻ ነው፡፡ የብርበራ ትእዛዝ ለፍ/ቤት ጥያቄ ቀርቦ ሊገኝ ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን የመበርበሪያ ትእዛዙን በዘፈቀደ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ለፍትህ አላማ ወይም ለማናቸውም ምርመራ ወይም ወንጀሉን ለማረጋገጥ የሚያስፈልግ መሆን አለበት፡፡ ፍ/ቤቱ ወንጀል ለመሰራቱ በቂ ማስረጃ ካልቀረበ ለማለት አይችልም፡፡ መበርበሪያ ትእዛዝ የሚያሰፈልገው ራሱ ማስረጃ ለማፈላለግ ነው፡፡ ወንጀል መፈጸሙን የሚያመለክት ነገር ካለ በቂ ነው /Prima Fascia Evidence/፡፡ ለምሣሌ መርማሪው ወይም ግለሰብ የስርቆት ወንጀል ፍሬ የሆነ እቃ ያለበትን ቦታ አረጋግጦ ከገለፀ በቂ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ብዙ ምስክር ለምን አልሆነም ወይም በቂ አይደለም የሚል ክርክር ሊቀርብ አይገባም፡፡ ፍ/ቤቱም ለፍትህ የቆመ አካል በመሆኑ ህግን ተከትሎ መርማሪው ወንጀልን ለማረጋገጥ የሚያደርገውን እንቅሰቃሴ ማገዝ አለበት፡፡

የብርበራ ትእዛዝ አጠቃላይ ሊሆን አይችልም፡፡ በተናጠል የሚበረበረውን ና የሚያዘውን እቃ ለይቶ ማመልከት አለበት፡፡ ከመበርበሪያ ትእዛዝ ውጪ ፖሊስ ሌላ እቃ ለመያዝ አይችልም፡፡ ብርበራ በሚከናወንበት ጊዜ ገለልተኛ ታዛቢ ባለበት ቢሆን ተመራጭ ነው፡፡ የሚያዝ እቃ ዝርዝር በታዘቢ ፊት ተመዝግቦ በገለልተኛ ሰው ሊፈረምበት ይገባል፡፡ የማያስፈልግ እቃ በደረሰኝ ተረጋግጦ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

መልመጃ

1 የብርበራ ትዕዛዝ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ምን መምሰል እንዳለበት በህጉ ዉስጥ አልተመለከተም፡፡ ሆኖም ስለብርበራ ከተደነገገዉ ህግ በመነሳት ምን ሊመስል እንደሚገባዉ መወሰን አይቻም?

2. የብርበራ ትዕዛዝ የሚበረበረዉንና የሚያዘዉን ዕቃ ማመልከት አለበት የሚለዉ የህጉ አነጋገር ፍርድቤት ከየት አምጥቶ ነዉ ዕቃዉን ማመልከት የሚችለዉ የሚል ጥያቄ ይጋብዛል፡፡ ይህ ወደ ማመልከቻዉ አይመራንም?

3. በብርበራ ትዕዛዙ ዉስጥ ከሰፈረዉ ዕቃ ሌላ መያዝ አይቻልም የሚለዉ የህጉ አነጋገር ከወንጀል መከላከልና ከህግ ማስፈጸም ጥቅም አኳያ ጠበቦ ወይስ ሰፍቶ መተርጎም አለበት - ማንኛዉንም ዕቃ እንዳይያዝ ለመከልከል ነዉ? ምን አይነት

ዕቃ እንዳይያዝ ለመከላከል ነዉ? በዚህ ህግ ጥበቃ የሚደረግለት ምን አይነት መብት ነዉ?

4. መርማሪ ዕቃዉን በሚያዝበት ጊዜ የተያዘዉን ዕቃ ዝርዝር መጻፍ አለበት፣ ቢቻል በጉዳዩ ነጻ የሆነ ሰዉ የዕቃዉ ዝርዝር ሊስት ትክክል መሆኑን እንዲያረጋግጥና እነዲፈርምበት ያስፍልጋል... የሚለዉ እና የማያስፈልግዉ ማንኛዉም ዕቃ ግንደረሰኝ በመቀበል ለተወሰደበት ሰዉ ተመላሽ ይሆናል... የሚሉት የሥነሥርዓት ህጉ ትዕዛዛት ካለዉ የብርበራና ኤግዚቢት አያያዝ ልማድ አኳያ ይተንትኗቸዉ፡፡ በልማድ ንብረቱ ሲያዝ በፖሊስ የኤግዚቢት ፎርም ላይ የሚፈርመዉ ማን ነዉ? በተያዘዉ ንብረት ዝርዝር ላይ ሊፈርም የሚገባዉ ንብረቱ የተያዘበት ሰዉ ነዉ? ፖሊስ ንብረት ሲመልስ ደረሰኝ የሚቀበል ከሆነ አስቀድሞ ሲወስድ ራሱ ደረሰኝ ሊሰጥ አይገባም፣ የሚዘጋጀዉን ሊስት ቅጂ ለባለንብረቱ ሊሰጥ አይገባም ?

5. የብርበራ ህግ ትዕዛዛት ወና ዓላማ የንብረት መብትን መንከባከብ ከመሆኑ አኳያ በንብረት መያዝ ጊዜ ያለዉ ባለንብረቱን የማስፈረምና ይህን ሰነድ የመያዝ አዝማሚያ ይህን ዓላማ ማገልገል ነዉ ወይስ ዋና ትኩረቱ ሰነዱም የኤግዚቢቱ ደጋፊ ማስረጃ እንዲሆን የማድረግ፣ ስለዚህ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲፈጥር ባለንብረቱን መገፋፋት ነዉ?

መርማሪው/ ፖሊስ ብርበራውን ለማከናወን ከተፈቀደለት በኋላ ችግር ቢያጋጥመው ተመጣጣኝ ኃይል ሊጠቀም እና መበርበር ወዳለበት ቤት መግባት ቢከለከል ይህንኑ ሃይል ተጠቅሞ ለመግባት ይችላል፡፡ በፍ/ቤት በግልፅ ተለይቶ ካልተፈቀደለት በስተቀር ፖሊስ ብርበራውን ከጠዋቱ 12፡00 እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ማከናወን አለበት፡፡

መልመጃ

1. የብርበራ ማከናወኛ ሰዓት በዚህ አይነት ተለይቶ መመልከቱን ብርበራ በዕማኝ ፊት እንዲከናወንና እንዲረጋገጥ ከሚጠይቀዉ የትዕዛዙ ክፍል ጋር በማገናኘት ያብራሩ?

በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 26 መሰረት የግል ህይወት ምስጢርነት ጥበቃ ተደርጐለታል፡፡ መብቱ ግን ፍጹም አይደለም፡፡ በህግ በተመለከተ ልዩ ሁኔታ የሰው መኖሪያ ቤት፣ ሰውነትና ንብረት ሊበረበር፣ ግንኙነት ሊጠለፍ ይችላል፡፡ ለዚህም የወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉን፣ የጸረሙስና ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅን /ቁ 434/1997/ እና የጸረ ሽብርተኝነት አዋጅን /ቁ652/2001/ መመልከት ይቻላል፡፡ በነዚህ ህግጋት ስለመበርበር በተለያየ መልኩ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ የጸረሽብርተኝነት አዋጅ ከመንደ ላይ ድንገተኛ ፍተሻ በቀር ብርበራም ሆነ የግንኙነት ጠለፋዉ በፌርድቤት ፈቃድ እንዲሆን የሚያዝዝ ነዉ፡፡ ድንገተኛ ፍተሻ በፌዴል ፖሊስ ዳይሬክተር ወይም ወኪሉ ፈቃድ ሊፈጸም ይችላለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የጸረሙስና ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ ስለብርበራ በግልጽ የሚደነግገዉ ነገር ባይኖርም ስለግንኙነት ጠለፋ የፍርድቤት ፈቃድ ማግኘት ሳያስፈልግ በህግ አስፈጻሚዉ ፈቃድ ሊፈጸም አንደሚችል ይደነግጋል፡፡

መልመጃ

1. ሙስናም ሆነ ሽብርተኝነት ወይም በኃይል የሚፈጸሙ ወንጀሎች ለኅብረተሰብ የሚጋርጡት አደጋ የሚተናነስ አይደለም፡፡ ከዚህ አኳያ የሰዎችን ግንኙነት በመጥለፍ ማስረጃ ለማሰባሰብ በህግ የሚፈቀድ ቢሆንም ይህን ለማድረግ በአንድኛዉ ጉዳይ የፍርድቤት ፈቃድ ሲያስፈልግ በሌላኛዉ የማያስፈልግ አድርጎ መለያየቱ ምን ያህል ተገቢነት አለዉ?

ከላይ በተገለጹት ህጎች መሰረት የግል ህይወት ምስጢርነትንና የንብረት መብትን የሚገድቡ የምርመራ ተግባራት ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡ ማለትም በማስገደድ እንደተገኘ ማስረጃ በማያሻማ መልኩ እልባት ያገኘ አይደለም፡፡ በህገ ወጥ መንገድ እንዲገኝ ያስደረገውን ወገን በመቅጣት በህገ ወጥ ብርበራ የተገኘዉን ማስረጃ መቀበል አንድ አማራጭ ነው፡፡ ሌላዉ አማራጭ ህገወጥነትን ላለማበረታታት ማስረጃውን /The Fruits of Poisonous Tree/ ውድቅ ማድረግ ነው ፡፡ ህገወጥ ከተባለ ተቀባይነት ሊያጣ ይገባል፣ Exclusionary Rule ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል የሚል መከራከሪያ አለ፡፡ የትኛውን መከተል አለብን የሚለዉ ያከራክራል፡፡ ህጋዊ የእስር ወይም የመበርበሪያ ትእዛዝ ይዞ ሣለ ፖሊስ ያላሰበውን የሌላ ወንጀል ማስረጃ ቢያገኝና ቢይዝስ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው

በተመሣሣይ ያከራክራል፡፡ መርማሪዉ በዚህ ጊዜ እና ቦታ በህጋዊ ተግባር ላይ ከሆነ በብዙ ሀገራት የተያዘዉ ማስረጃ ተቀባይነትን ያገኛል፡፡ ተቀባይነት(Admissibility) ህግ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ግልጽ ከልካይ ህግ ያስፈልጋል፡፡ ከማስረጃ አግባብነት(Relevance) ጋር ይለያል፡፡ አግባብነት ከሎጂክ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ማስረጃን ፍ/ቤት ሊቀበል አይገባም ስንል ሁልጊዜ የህግ ድንጋጌ ላይ መመስረት አለብን፡፡

መልመጃ

1. እነዚህን ሁለት የብርበራ አጋጣሚዎች ያነጻጽሩ? በአንዱ አጋጣሚ የብርበራ ትዕዛዝ ይዞ በወንጀሉ ቦታ የተገኘ በርባሪ ተግባሩን በሚያከናዉንበት ጊዜ እንዲበረብርና እንዲይዝ በትዕዛዙ ላይ ከተገለጸዉ ዉጪ የሆነ በምርመራ ክፍሉ ተመዝግቦ እየተጣራ ባለ አንድ ወንጀል የተገኘና ለጊዜዉ ከህግ አስከባሪዎች ተሰዉሮ የነበረ ንብረት በመኪና ሊወሰድ ሲጫን ተመልክቶ ይህን ንብረት ያዘ፡፡በሌላኛዉ አጋጣሚ በተመሳሳይ ሁኔታ በቦታዉ የተገኘ በርባሪ በትዕዛዙ ዉስጥ ያልተጠቀሰ ስለአንድ ህገወጥ ድርጅት የሚገልጽ አንድ ገጽ ወረቀት በቦታዉ በማየቱ እና የተለያዩ የጽህፈት መሳሪያዎች ወደመኪና ሲጫኑ በመገኘታቸዉ ይህን ጽሁፍ የሚመለከቱ ነገሮች ከነዚህ መሳሪያዎች ዉስጥ ይገኙ ይሆናል በሚል ግምት ሁሉንም ዕቃዎች ኮምፒዉተሮችና ተያያዥ መሳሪያዎችን በሙሉ ሰብስቦ ያዘ፡፡
2. ከነዚህ ሁለት አጋጣሚዎች በየትኛዉ ብርበራ የተገኘዉ ማስረጃ ተቀባይነት ይኖረዋል ወይም በሁሉም አጋጣሚዎች የተገኘዉ ሁሉ በትዕዛዙ ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረዉም?
3. የማስረጃ ተቀባይነትን አስመልክቶ ከብርበራ ጋር በተያያዘ የተደረገ ክልከላ በህጋችን ዉስጥ አለ?
4. በብርበራ ትዕዛዝ ከተመለከተዉ ዉጪ መያዝ አይቻልም የሚለዉ የማስረጃ ተቀባየነትን የሚመለከት ነዉ?

3.3.2. ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር ና መያዝ

ተጠርጣሪን እንደ መያዝ ሁሉ መበርበርና መያዝ ሁልጊዜ በፍ/ቤት ትእዛዝ ብቻ የሚፈፀም አይደለም፡፡ ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ ህግን ተከትሎ ብርበራ በማከናወን የወንጀል ማስረጃን መያዝ ይችላል፡፡ ያለ ፍ/ቤት የመበርበሪያ ትእዛዝ ብርበራ ማከናወን የሚቻለው ወንጀለኛውን እጅ ከፍንጅ ሲከታተሉ እና ቤት ውስጥ ገብቶ ከተደበቀ ወይም ወንጀል የተሰራበትን ነገር ቤት ውስጥ ያስቀመጠ ከሆነ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ፖሊስ የብርበራ ትእዛዝ ፍለጋ ወደ ፍ/ቤት ሲሄድ ወንጀለኛውን ወይም ማስረጃውን ላያገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ ህጉ በቀጥታ እርምጃ እንዲወሰድ ይፈቅዳል፡፡

ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ የፖሊስ ብርበራ የሚከናወንበት ሌላው መንገድ ከሶስት ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ተፈፀመ ተብሎ ክስ ወይም አቤቱታ ከቀረበ በኋላ ለማስረጃ የሚሆን ወንጀሉ የተፈጸመበት ነገር አንድ ቦታ የተደበቀ ወይም የተቀመጠ ለመሆኑ ለፖሊስ በሚያሣምን መልኩ ከተገለፀና የብርበራው ትእዛዝ እስኪገኝ ድረስ ማስረጃው ይጠፋል ተብሎ በበቂ ምክንያት የታመነ እንደሆነ ነው፡፡ የወንጀሉን አይነት ለመለየት መታየት የለበት መነሻው ቅጣት ሣይሆን መድረሻው ነው፡፡

መልመጃ

1. ከወንጀሉ ቅጣት መጠን ጋር የተያያዘዉ ያለፍርድቤት ፈቃድ የሚደረግ ብርበራ በሁሉም ወንጀሎች ላይ ሊከናወን ይችላል?
2. በመደበኛ ሁኔታ በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከሦስት ዓመት በላይ ሊያስቀጡ አይችሉም፡፡ ስለዚህ በዚህ አይነት ወንጀሎች ጊዜ ያለፍርድቤት ፈቃድ መበርበር አይቻልም ማለት ነዉ?

በመንገድ ላይ ወይም ወደ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለመግባት የሚደረግ ፍተሻ ህጋዊነት ላይ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ እነዚህ ፍተሻዎች ያለፍርድቤት ፈቃድ የሚከናወኑ ናቸዉ፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉ ስለዚህ አይነት ፍተሻ የሚደነግገዉ የለም፡፡ በፍርድቤት ፈቃድ ይሁን አይሁን የሚያነሳዉ ምንም ነገር የለም፡፡ ሆኖም በቅርብ ጊዜ እየወጡ ያሉ ህጎች አዝማሚያ እንዲህ አይነት ጉዳዮችን የሚገዙ ድንጋጌዎችን እያካተቱ

እንደሆነ ይስተዋላል፡፡ የጸረሽብርተኝነት አዋጅ ለዚህ ተጠቃሽ ነዉ፤ በመንገድ ላይ ሰዎችን ወይም አሽከርካሪዎችን አስቁሞ መፈተሽ በግልጽ የተፈቀደ ሲሆን ለዚህም የፌዴራል ፖሊስ ዳይሬክትር ወይም የወኪሉ ፈቃድ ብቻ በቂ ነዉ፡፡

በመንገድ ላይ የሚደረገው ፍተሻ በሚፈተሸው ሰው ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ ሊያወዛግብ ይችላል፡፡ ወደ ተቋም የሚገባ ሰው ግን ካልፈለገ ሊመለስ የሚችልበት ሁኔታ ስላለ ከግል ህይወት ምስጢርነት መብት እና ከአካል ደኅንነት መብት መጣስ ጋር ያለው ግንኙነት አነስተኛ ነው፡፡

መልመጃ

- ለመፈተሽ ያልፈለገ ሰዉ ይሄድ ከነበረበት አቅጣጫ ሊመለስ መቻሉ የግል ነጻነቱ ማለትም ወደፈለገበት ቦታ የመሄድና የመግባት መብቱ አልተገደበም ማለት ያስችላል?

ከፍተሻ ጋር ተቀራራቢ የሆነዉና የግል ህይወት ምስጢርነትን የሚመለከተዉ ሌላዉ የምርመራ ተግባር ግንኙነትን መጥለፍ ሲሆን ይህን በተመለከተ ሁለቱ ቀደም ሲል የተጠቀሱ ህጎች የተለያ አቋም ይከተላሉ፡፡ ቀደም ሲል የወጣዉ የጸረ ሙስና ሥነሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ይህን ጠለፋ ያለፍርድቤት ፈቃድ እንዲከናወን ሲፈቅድ፤ የጸረሽብርተኝነት አዋጅ በቅርብ ጊዜ የወጣ ቢሆንም ግን እንዲህ አይነቱጠለፋ በፍርድቤት ፈቃድ እንዲሆን ያዝዛል፡፡

መታየት የለበት ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የግል ነጻነት መከበሩን የመጠየቅ ሁኔታ/reasonable expectation/ ላይ ነው፡፡ ህገወጥነት ካለ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ቀደም ብሎ የተገለጸው እዚህ ጋርም አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ሰለሆነም የወንጀል ህግ ሥነስርዓቱ ሲሻሻል ያሉት ክፍተቶችን ሁሉ በሚዘጋ መልኩ ሊቀረፅ ይገባል፡፡ ባለውም ህግ ቢሆን ህገ መንግስቱን ተከትሉ መስራት ይገባል፡፡

3.4 ተጠርጣሪን መያዝና የተከሳሽነት ቃል መቀበል

3.4.1 መያዝ

መልመጃ

- በሥነሥርዓት ህጉ በቁ 26/1/ አንድን ተጠርጣሪ ለመያዝ ሊሚሉ ከሚገባቸዉ ቅድመሁኔታዎች አንዱ ...ወንጀሉ በህጉ መሰረት የሚያስይዘዉ... መሆኑ ነዉ፡፡ ይህ ምን ማለት ነዉ በህጉ መሰረት የማያስይዝ ወንጀል አለ ማለት ነዉ?

ወንጀል የተፈጸመ መሆኑን ለማመን ምክንያት <u>ለመፈፀሙ መረጃ</u> ካለው መርማሪው ተጠ ርጣሪውን ማስቀረብ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ማዋል እንደነገሩ ሁኔታ በተለያየ መንገድ ሊፈፀም ይችላል፡፡ ለተጠርጣሪው በመርማሪው መጥሪያ ተልኮለት ከቀረበ መርማሪው በቁጥጥር ስር ያውለዋል፡፡ ከዚህ ውጪ መጥሪያ ተልኮለት ካልቀረበ ወይም ገና ያልተያዘ ሆኖ ወንጀሉ የሚያስይዘዉ ከሆነ መርማሪው ተጠርጣሪውን በሕግ ላይ በተደነገገው መሠረት ሊይዘው ይችላል፡፡

ይህም ማለት ተጠርጣሪው በ መርማሪው ተጠርቶ እራሱ ካልቀረበ ወይም ያለ መርማሪው መጥሪያ መያዝ ያለበት ሆኖ ከተገኘ መርማሪው ተጠርጣሪውን እንዲያዝ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ተጠርጣሪው በሁለት ዓይነት መንገድ ሊያዝ ይችላል፡፡ እነዚህም በፍ/ቤት ትዕዛዝና ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ናቸው፡፡ ያለፍ/ቤት ትዕዛዝ ለመያዝ ሕጉ በሚፈቅድበት ጊዜ ሁሉ ወደ ፍ/ቤት መሄድ ሣያስፈልግ በቀጥታ መርማሪው/ፖሊስ በራሱ ተጠርጣሪውን መያዝ ይችላል፡፡ ሁለቱ የአያያዝ መንገዶች የየራሣቸው የተለየ ባህሪ ስላላቸው ለየብቻ እንመለከታቸዋለን፡፡

3.4.1.1 በፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ

በመርህ ደረጃ ወንጀል ፈፀመ የተባለው ሰው መያዝ የሚችለው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ብቻ ነው፡፡ የመያዣ ትዕዛዝ የፈለገ መርማሪ/ፖሊስ በማናቸውም ቀንና ሰዓት ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡ የመያዣ ትዕዛዝ በመርማሪው በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ በፍ/ቤት መፈቀድ የለበትም፡፡ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 54 መሠረት የመያዣ ትዕዛዝ የሚሰጠው የተጠርጣሪው መቅረብ ፍፁም አስፈላጊ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ፍ/ቤት ጅምር የምርመራ መዝገብን ተመልክቶ በሕግ ወንጀል የተባለ ተግባር ተፈፀመ መባሉንና ወንጀል መፈፀሙን የሚያመለክት ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡ ይህ ማለት ግን ፍ/ቤት ጥፋተኝነትን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ

መኖሩን መመርመር አለበት ማለት አይደለም። በቂ ማስረጃ መኖሩ ወደፊት ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ በዐቃቤ ሕግ የሚመዘን ነው። ፍ/ቤቱ ማረጋገጥ ያለበት በበቂ ምክንያት ጥያቄው መቅረቡን ነው። ይህንን ለማረጋገጥ ወንጀል መፈፀሙን የሚያመለክት ማስረጃ (primafacie evidence) በቂ ነው። እውነቱን ወዲያው ማረጋገጥ አይቻልም፤ ለምሣሌ አንድ ግለሰብ ወይም የፖሊስ አባል በተጠርጣሪው መጋዘን ውስጥ የሚፈነዳ የጦር መሳርያ ወይም ተቀጣጣይ ፈንጅ መኖሩን አረጋግጦ ቃል የሰጠበት ጉዳይ ቢሆን ተጠርጣሪው እንዲያዝ ለማስደረግ በቂ ነው። ፍ/ቤት ማስረጃ ምዘና ውስጥ መግባት የለበትም።

መልመጃ

1. የመያዣርያ ትዕዛዝ ለማግኘት የሚቀርበዉ ጥያቄ ተቀባይነት እንዲኖረዉ የተጠርጣሪዉ *ፍርድቤት መቅረብ ፍጹም አስፈላጊ* መሆኑ እና ይህም *በሌላ መንገድ ያማይቻል* መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል። እነዚህ መመዘኛዎች መርማሪዉ ምን እንዲያሳይ ያስገድዳሉ?
2. ያለመያዣርያ ትዕዛዝ መያዝ አለመቻሉን ማሳየት ይጠበቃል?
3. የተጠርጣሪዉ ፍርድቤት መቅረብ ፍጹም አስፈላጊ መሆኑና ወንጀል የተፈጸመ መሆኑን ለማመን የሚያስችል ማስረጃ የማቅረብ አስፈላጊነት ምን ግንኙነት አላቸዉ?

ተጠርጣሪን መያዝ ጊዜ የማይሰጥ ሊሆን ይችላል። ወንጀሉን ፈፅሞ ከአካባቢው ሊሰወር እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ለፖሊስ መረጃ ሊደርስ ይችላል። በዚህ ጊዜ ፖሊስ ለፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ እስከሚያቀርብ ድረስ ተጠርጣሪው ሊሰወር ይችላል። ሊፈጠሩ የሚችሉ ያልተጠበቁ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ሕጉ መፍትሄ አበጅቶለታል። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 55 መሠረት አጣዳፊ ሁኔታ ሲያጋጥም መርማሪው ፖሊስ በቴሌፎን ወይም በቴሌግራም የመያዣ ትዕዛዝ መጠየቅ ይችላል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የመያዣ ትዕዛዙ ከተፈቀደ በኋላ በ24 ሰዓታት ውስጥ በጽሑፍ ተደርጐ ለፍ/ቤቱ መቅረብ አለበት። ወሣኙ ነገር በተፈለገበት ጊዜ በአስቸኳይ ትዕዛዙ መገኘቱ ነው። ከዚያ በኋላ የተጠያቂነት አሠራር እንዲሰፍን ጥያቄው በጊዜ ተገድቦ በጽሁፍ መቅረቡ ተገቢ ነው።

3.4.1.2 ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ

ተጠርጣሪን ለመያዝ ሁልጊዜ ፍ/ቤትን የመያዣ ትዕዛዝ መጠየቅ አያስፈልግም። በሕጉ ላይ የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መርማሪው/ፖሊስ ፍ/ቤት ድረስ መሄድ ሣያስፈልገው በራሱ በቀጥታ ተጠርጣሪውን ይዞ በቁጥጥር ስር ማዋል ይችላል። ለፖሊስ ይህንን ሥልጣን የሚሰጡት ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ መያዝ ልዩ ሁኔታም አይመስልም። በበርካታ ጉዳዮች ላይ ፖሊስ ያለ መያዣ ትዕዛዝ ተጠርጣሪን መያዝ ይችላል።

ማንኛውም ሰው ወይም የፖሊስ ሠራዊት ተጠርጣሪውን ከ3ወር በማያንስ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ የእጅ ከፈንጅ ወንጀል እየፈጸመ ወይም ፈጽሞ ያገኘዉ እንደሆነ መያዝ ይችላል። ፖሊስ ያልሆነ ሰው ተጠርጣሪውን ከያዘ በኋላ ወዲያው ለሚመለከተው የፖሊስ ክፍል ማስተላለፍ አለበት።

የወንጀሉን ዓይነት ለመለየት መመልከት ያለብን የቅጣቱን መነሻ ሣይሆን መድረሻ ነው። መነሻው ቅጣት ዝቅተኛም ቢሆን መድረሻው ቅጣት 3 ወር ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ሕጉ ይሸፍነዋል።

መልመጃ

1. ያለመያዣ ትዕዛዝ ሰዉን መያዝ የሚቻልበትን የእጅከፍንጅ ወንጀል ለመለየት 3 ወርን ልንመለከት የሚገባን እንደቅጣቱ መነሻ ነዉ ወይስ መድረሻ?
2. እንደመድረሻ ከወሰድነዉ የማያስይዙ ወንጀሎች በሚባሉት /ደንብ መተላለፍ፣ ወይም በተግሳጽና በወቀሳ የሚቀጡት ቀላል ወንጀሎች/ ጊዜ ምን ልናደርግ ነዉ /የሥ/ሥ/ህጉንና የወ/ህ/ቁ 89 አገናዝበዉ ይመርምሩ?

ከዚህ ውጪ ለማንኛውም ሰው ሣይሆን ለፖሊስ ብቻ ተጠርጣሪን ያለመያዣ ትዕዛዝ መያዝ የሚቻልባቸው ጉዳዮች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 51 ስር ተዘርዝረዋል። ከአንድ ዓመት በማያንስ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ለመስራት ዝግጁ የሆነዉን ወይም ሰርቷል ተብሎ በሚገባ የተጠረጠረዉን ሰዉ መያዝ አንዱ ሲሆን መነሻ ቅጣቱ አነስተኛም ቢሆን በዚህ ጊዜም ቤሆን መታየት ያለበት መድረሻው ቅጣት ነው።

መልመጃ

1. ከአንድ ዓመት በማያንስ መባሉ ከላይ ያየነዉን ችግር በተለየ ሁኔታ እንድንፈታ የሚጋብዝ ነዉ ወይስ ችግሩ ተመሳሳይ ነዉ?
2. አንድ ዓመት ተብሎ የተጠቀሰዉ መነሻዉን ካልሆነ ሁሉም ወንጀል ያለፍርድቤት ፈቃድ መያዝ ሊያስችል አይደለም?
3. በማያንስ ካለ መነሻዉ ከዚህ ሊያንስ የሚችልበት አጋጣሚ የሚፈጥር አተረጓጎም ለምን እንከተላለን?
4. የማያስይዙ ወንጀሎችስ እንዴት ይስተናገዳሉ?

የሕዝብን ፀጥታ በማዉላሸት ላይ የሚገኝ ወይም የፖሊስን ስራ የሚያደናቅፍ ወይም ከታሰረበት የሚያመልጥ ወይም ለማምለጥ የሚሞክር ወይም ከፖሊስ ወይም ከመከላከያ ሠራዊት የከዳ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ የቤት መሰርሰሪያ ወይም ቤትን መስበሪያ መሣሪያ የያዘ ወይም የተሠረቀ ዕቃ መያዙ በሚገባ የሚጠረጠርን ወይም የወንጀል ፍሬ የያዘ ወይም በአደገኛ ቦዘኔነት በሚባ የተጠረጠረን ፖሊስ ፍ/ቤት መሄድ ሣያስፈልገው በቀጥታ በራሱ መያዝ ይችላል::

በመሆኑም ፖሊስ ፍ/ቤት መሄድ ሣያስፈልገው በብዙ ጉዳዮች ላይ ተጠርጣሪን በሕግ መሠረት መያዝ ስለሚችል በነዚህ ጉዳዮች የፍ/ቤትን ይሁንታ መጠየቅ የለበትም:: ሕግን ተከትለ በራሱ መሥራት አለበት::

መልመጃ

1. ያለፍርድቤት ፈቃድ መያዝ የሚቻልባቸዉ አጋጣሚዎች ከወንጀሎቹ ባህሪ ባብዛኛዉ ደግሞ ከሚያስከትሉት ቅጣት ጋር የተያያዙ ናቸዉ:: የወንጀሎቹ አይነት እና የቅጣታቸዉ መጠን በህግ የተመለከተ ነዉ:: እነዚህን ለይቶ ለመገንዘብ ደግሞ ሰዎችን ለምርመራ የሚይዘዉ ወገን የህግ ዕዉቀት መጠን ይወስነዋል:: የፖሊስ ባልደረቦች የተፈጸመን ወይም እየተፈጸመ ያን ወንጀል የቅጣት መጠን በምን ለይተዉ ነዉ ባግባቡ እጅከፍንጅ መያዝ የሚችሉት?
2. ወይም ይህ መመዘኛ በመያዝ ጊዜ ሳይሆን መያዝ ከተፈጸመ በኋላ ተገቢነቱን ለመወሰን የሚያገለግል መመዘኛ ነዉ?

3.4.2 ቃል መቀበል

በማናቸውም መንገድ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋለ ተጠርጣሪ ማንነቱና አድራሻው ከተረጋገጠ በኋላ ለቀረበበት ክስ ወይም አቤቱታ ቃሉን እንዲሰጥ ይጠየቃል። ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ግን ለመናገር የማይገደድ መሆኑን፣ ግን ፈቅዶ የሚሰጠው ማናቸውም ቃል ተመዝግቦ በማስረጃነት ወደፊት ሊቀርብበት እንደሚችል ሊነገረው ይገባል። ተጠርጣሪን ቃሉን እንዲሰጥ ማስገደድ ሕገ ወጥ ነው። በማስገደድ የተገኘ የዕምነት ቃል ውጤቱ ምን እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 19/5 ስር ተደንግጉ ይገኛል። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም።

መልመጃ

1. በወንጀል ምርመራ ጊዜ ላለመናገር መብት እንዳለዉና ፈቅዶ የሚሰጠዉ ቃል ተመዝግቦ ማስረጃ እንደሚሆንበት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠዉ ቃሉን እንዲሰጥ የተጠየቀ ተጠርጣሪ ቃል የማስረጃነት ዋጋዉ ምን ያህል ነዉ ተቀባይነቱን ማጣተ አለበት፣ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ሊባል ይችላል?
2. በፖሊስ ጣቢያ የሚሰጥ ቃል ብዙ ጊዜ ፍ/ቤት ሲቀርብ ተቃውሞ ሲቀርብበት ይታያል። ተከሣሹ ተገድጄ ነው ካለ መገደዱን እራሱ ማረጋገጥ አለበት የሚል ክርክር ይቀርባል። በሌላ በኩል እራሱ ዓ/ህግ በተከሣሹ ከተካደ በነጻነት የተሰጠ ቃል ለመሆኑ በደጋፊ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል፣ ተከሣሹ ነጻነቱን አጥቶ በእስር ላይ ስለሚገኝ በፈቃዱ ለመስጠቱ በከሣሽ ነው መረጋገጥ ያለበት፣ በከሣሽ ከተረጋገጠ ነው ተከሣሹ መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ያለበት የሚል ክርክርም ይቀርባል። በተጨማሪ ተከሣሹ የጣቢያ ቃሉ ውድቅ እንዲሆንለት ተገዶ ቃሉን ለመስጠቱ ማስረጃ ማቅረብ ያለበት ተከላከል ተብሎ ሣይነገረው ነው ወይስ ከተነገረው በኋላ መከላከያ ማስረጀ ሲያቀርብ አብሮ ያቀርባል/ በህጉ ላይ በግልፅ የተመለከተ ነገር የለም። አንድ ተጠርጣሪ በወንጀል ምርመራ ጊዜ በሚሰጠዉ ቃል ጽሁፍ ላይ ከፈረመበትና ፊርማዉ የራሱ መሆኑን ካረጋገጠ ለዚህ ቃል

ትክክለኛነት /በተለይም ማስጠንቀቂያዎች የተሰጡት መሆኑ ተጽፎ ከሆነ/ ማረጋገጫ አይሆንም? ለዐቃቤህግ ይህ በቂ ማስረጃ ሆኖ ሊወሰድ አይገባም?

ተጠርጣሪው በፖሊስ ጣቢያ ቃሉን ሲሰጥ በፍቃዱ ለመስጠቱ ውዝግብ ስለሚፈጥር ተመራጩ መንገድ በወ/መ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሰረት ፍ/ቤት ሄዶ ቃሉን እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ቃሉን ከመቀበሉ በፊት በቅድሚያ በነጻነት ቃሉን መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ተጠርጣሪውን በመጠየቅ የሚሰጠው ቃል ወደ ፊት በማስረጃነት ሊቀርብት እንደሚችል ተገለጸለት ፈቃደኛ መሆኑን በማያሻማ መልኩ ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ መደረጉም መዝገቡ ላይ መስፈር አለበት፡፡ ተጠርጣሪው በነጻነት ቃሉን ከሰጠ በኋላ ተነቦለት ቃሉን የተሰጠበትን ቀን ጽፎ መፈረም ይጠበቅበታል፡፡ በመቀጠል ቃሉን የተቀበለው ዳኛ መፈረም አለበት፡፡ ከዚህ በኋለ ለዓ/ህግና ለሚመለከተው ሁሉ ቃሉ ተገልብጦ እንዲሰጥ ትእዛዝ ተሰጥቶ መዝገቡ መዘጋት አለበት፡፡ ምን ጊዜም አስተማማኝ የሆነውን በፍ/ቤት ቃል የማሰጠት አሰራር አላስፈላጊ ክርክርን ስለሚያስወግድ ፖሊስ ሊከተለው ይገባል፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ በፍ/ቤትም ቢሆን በነጻነት ቃሉን ላለመስጠቱ መከላከያ ማስረጃ ካለው ማቅረብ ሊከለከል አይችልም፡፡

መልመጃ

1. በ35 የሚመዘገብ ቃል ምን አይነት ነዉ? የወንጀል ተጠርጣሪ ቃል ብቻ ነዉ ወይስ ሌላም ቃል ሊሆን ይችላል? ይህ ቃል ወደፊት ማስረጃ እንደሚሆንበት የመንገር ሃሳብ በዚህ ድንጋጌ ዉስጥ በግልጽም ሆነ በዉስጠ ታዋቂ ተካትቶ ይገኛል?
2. ይህ ቃል እንዲሰጥ ጥያቄዉ የሚቀርበዉ በመርማሪዉ መሆኑ ተገቢነቱ ከድንጋጌዉ ግብ አንጻር ምን ያህል ተገቢ ነዉ?
3. ይህ ቃል በ27 ከሚመዘገበዉ ቃል በምን ይለያል? በተለይ ተከሳሹ ፍርድቤት ቀርቦ ክሱን ከሰማ በኋላ ወንጀሉን አልፈጸምኩም የሚል ክርክር በሚያቀርብበት አጋጣሚ፡፡
4. በፌደራሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 35763 የተላለፈው ውሳኔ በዚህ ፅሁፍ መጨረሻ ክፍል ተያይዟል ከቃል አቀባበል ጋር የተያያዙት የፍሬ-ነገርና የህግ ክርክሮች፣ ትንታኔዎች ና የፍርድቤቱ ውሳኔ

በመመልከት አግባብነቱ ያብራሩ? ያዕቆብ ሓይለማርያም የተባለው ተከሳሽ ሁለት ግዜ ቃሉ ለፖሊስ ሰጥቷል። በመጀመርያው ሙሉ በሙሉ ሲክድ በሁለተኛው ግን ቃሉ አምኖ ሰጥቷል። ሁለተኛ ጊዜ ቃል መቀበል ለምን አስፈለገ? በምን አይነት ሁኔታ ነው ቃል ለሁለተኛ ጊዜ መቀበል የሚቻለው? ተጨማሪ ቃል ለምን አላማ ያስፈልጋል? ቃል የምንቀበልበት ቅፅ ወይም ፎርም እና ይዘቱ ምን መምሰል አለበት? ቃል የምንቀበልበት ጊዜና ሰዓት እንዴት ከተፅእኖ ጋር ሊያያዝ ይችላል? ለሚሉት መሰረታዊ ጭብጦች ምላሽ ይስጡ?

3.5. ከተጠርጣሪ አካል ላይ የሚወሰድ ማስረጃ

ወንጀል ተፈጸመ ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ማስረጃ የሚሆን ነገር ከሰውነቱ ላይ ለማግኘት ፍቃደኛ ካልሆነ ምን መደረግ አለበት የሚለው በህጋችን ግልፅ ምላሽ አላገኘም። በዚህ ጊዜ ሁለት አማራጭ ነው ያሉት። አንዱ ተጠርጣሪውን በሃይል በማስገደድ የጣት አሻራ ወይም የደም ምርመራ እንዲደረግ ነው። ሌላው አማራጭ በምርመራ የሚገኘው ውጤት ተጠርጣሪው ተመርምሮ ውጤቱ በአግባቡ እንዲረጋገጥ ካልፈለገ ባይመረምር የራሱ ችግር በመሆኑ ኖረበትም አልኖረበትም እንዳለበት ቆጥሮ ማለፍ ነው።

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 34/1 መሰረት በፍ/ብ/ህ/ቁ 20 ሥር የተደነገገው ቢኖርም መረማሪው/ፖሊስ ተከሣሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ተመልክቶ በህኪም መመርመር የሚያስፈልገው መሆኑን ከተረዳ የማከም ፍቃድ ያለው ሐኪም ምርመራውን እንዲያደርግ ና የምርመራውን ውጤት ሐኪሙ በፅሑፍም እንዲያስታውቀው ለማዘዝ ይቻላል። ስልጣኑ የተሰጠው ለፖሊስ ነው። ይህ ግልፅ ድንጋጌ ነው። ሊገደድ ይገባል። ተመርማሪው ባይፈልግም ለወንጀል ጉዳይ ሊገደድ ይገባል ለፍታብሄር ግን እንዳለበት ግምት ነው መወሰ ያለበት በማለት መከራከር ይቻላል።

መልመጃ

1. የወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉ የታወጀበት ጊዜ የአካል ድኅንነት መብት በግልጽ ያልተረጋገጠበት መሆኑን በ1949 ዓም የወ/መ/ህግ ዉስጥ ይታወቅ ከነበረዉ የግርፋት ቅጣት መመልከት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉ ቁ 34 አንድ ሰዉ የህኪም ምርመራን እምቢ የማለት መብቱ ቢኖርም መርማሪ ፖ/ሊስ ይህ ምርመራ እንዲደረግበት ሊያዝዝ ይችላል ብሎ መደንገጉ በማስገደድ ሊከናወን እንደሚችል ያመለክታል?
2. በአሁኑ ጊዜ የአካል ድኅንነትመብት በህገ መንግሥቱ ተረጋግጧል፡፡ የግርፋት ቅጣትም እንዲቀር ተደርጓል፡፡ ከዚህ አኳያ በማስገደድ ምርመራ ማድረግ የሚቻል ይሆናልን?
3. ማስረጃ በህግ ግምት ሊሆን ይችላል፡፡ በአንድ ህግ ዉስጥ የተሰጠን የህግ ግምት የፍትሃብሄር እና የወንጀል ብሎ መለያየት በሌላዉ ህግ በሚነሳ ጉዳየ ዉስጥ ተፈጻሚ እንዳይሆን ማድረግ ከማስረጃ ህግ አኳያ ተገቢነቱ እስከምን ነዉ?

በፍ/ብ/ህ/ቁ 22 መሰረት የዚህን አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም መደረግ ያለበት በምርመራ ሊገኝ የሚችለው ነገር እንዳለበት በመገመት ውሣኔ መስጠት ነው፡፡ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 34/1 የፍታብሔር ህጉ ድንጋጌ ቢኖርም ተብሎ ስለተቀረፀ ተጻሚነት አለው፡፡ ተጠርጣሪው ተገዶ መመርመር አለበት ወይም ተመሣሣይ ለህዝብ ጥቅም ሲባል አሻራ መስጠት አለበት ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ ለምሳሌ የጸረሽብርተኝነትን አዋጅ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ አዋጅ በቁ 21 እንድተመለከተዉ

> ፖ/ሊስ በሽብርተኝነት ወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረ ሰዉ የእጅ ጽሁፉን፣ የጣት አሻራዉን፣ ፎቶግራፉን፣ የጸጉሩን፣ የድምጹን፣ የደሙን፣ የምራቁንና በሰዉነቱ የሚገኙ ፊሰሽ ነገሮችን ናሙናዎች ለምርመራ እንዲሰጥ ሊያዝዝ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የህክምና ምርመራ እንዲያደርግ ሊያዝዝ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪዉ ለምርመራዉ ፈቃደኛ ካልሆነ ፖ/ሊስ አስፈላጊ የሆነ ተመጣጣኝ ኃይል ተጠቅሞ ከተጠርጣሪዉ ናሙና ሊወስድ ይችላል፡

መልመጃ

በሽብርተኝነት ጉዳይ የተፈቀደዉ የኃይል አጠቃቀም እንዴት ሊፈጸም ይችላል ከዚህ ተመሳሳይ የሆኑ የኃይል አጠቃቀም መንገዶች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉ ተደንግገዉ ይገኛሉ፡፡

1. በ አንቀፅ 33/4/፡- መርማሪዉ ፖሊስ ወይም የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ ብርበደራ በሚያደርግበት ጊዜ አስፈላጊ የጅነዉን ኃይል ብቻ ለመፈጸም ይችላል? እንዲሁም ከቤቱ ዉስጥ ለመግባት የተከለከለ እንደሆነ ተገቢ በሆነ ኃይል ለመግባት ይችላል?
2. በ አንቀፅ 56/4/፡- የሚያዘዉም ሰዉ አልያዝም ብሎ በኃይል የተከላከለ ወይም ለማምለጥ የሞከረ እንደሆነ ሁኔታዉ በሚፈቅደዉ ተመዛዛኝ ዘዴ ፖሊሱ ሰዉየዉን ለመያዝ ይችላል?
3. በነዚህ የኃይል አጠቃቀሞችና በሽብርተኝነት አዋጅ በተመለከተዉ የኃይል አጠቃቀም መሃል ተመሳሳይነት ሊኖር ይችላልን?
4. የተለያዩ የምርመራ ናሙናዎችን ለመስጠት የተጠየቀ ሰዉ ላይ የምንጠቀመዉ ኃይል ከምን ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፣ ፈቃደኛ ካለመሆን ጋር ተመጣጣኝ የሚሆነዉ ኃይል ምን አይነት ነዉ?
5. በህገመንግሥቱ የአካል ደኅንነት መብት ከሌሎች መብቶች በተለየ ሁኔታ ምንም ገደብ ያልተቀመጠለት ከመሆኑ አኳያ እንዲህ አይነቱን የኃይል አጠቃቀም ህጋዊ ሆኖ ማከናወን ይቻላልን?

በኤች አይ ቪ ፖሊሲው ላይ ማስገደድ ተከልክሎዋል፡፡ ፖሊሲ በህግ አተረጓጎም ላይ የራሱ እንደምታ አለው፡፡ በአሰሪ ና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14/2/መ ስርም ለኤች አይ ቪ ምርመራ ሰራተኛን ማስገደድ አይቻልም፡፡

በማስገደድ ምርመራ ማድረግ ተገቢ አይደለም የሚለዉ ክርክር በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀፅ 19/5 መሰረት በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም ስለሚል በዚህ አይነት ማስገደድ የምንሰበስበዉ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረዉም በሚል ላይ

የተመሰረተ ነዉ። ሌላዉ መከራከሪያ በአንቀፅ 26 ስርም የግል ነጻነት ተከብሯልየሚለዉ ነዉ። ከዚህ አንጻር የማስገደድን ተግባርን ህገ መንግስታዊነት መመርመር ያስፈልጋል።

መልመጃ

1. የግል ህይወት ምስጢርነት መብት በህገመንግሥቱ የተረጋገጠ ቢሆንም የተለያዩ ገደቦች ሊደረጉበት የሚችል ነዉ። ከዚህ አኳያ ለወንጀል መከላከል ዓላማ በማስገደድ ምርመራ እንዲከናወን ቢደረግ ይህን መብት የመጣስ ተግባር ተፈጸመ ሊያስብል ይችላልን?
2. በህገመንግሥቱ ቁ 19/5/ የተመለከተዉ የማስረጃ ተቀባይነት ድንጋጌ በማስገደድ ናሙናዎችን መዉሰድ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላልን?
3. በማስገደድ የሚገኘዉ ማስረጃ ነዉ ወይስ ማስረጃ ለመፈለግ የሚያስችል ሌላ ነገር፣ የሚወሰደዉ ናሙና ማስረጃ ነዉን?
4. በሚወሰደዉ ናሙና ላይ የማስገደድ ወይም የኃይል ሥራ ቢታከልበት በናሙናዉ ባህሪ ላይ ለዉጥ ያመጣልን?

እንዳለበት ገምቶ ማለፍ ይሻላል ከተባለ ግን ፖሊስ በጥንቃቄ በታዛቢ ወይም በፍ/ቤት የተጠርጣሪውን እምቢተኝነት አረጋግጦ መያዝ አለበት። ሴትን ደፍሮ ወዲያው አልመረመርም ብሎ በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፍ የሚችል/Sexually Transmitted Diseases/ ጨብጥን ለመሣሰለ በሽታ መድሃኒት ከወሰደ በኋላ ዘግይቶ ልመርመር የሚል ጥያቄ እንዲያቀረብ በር መክፈት የለበትም።

በአሜሪካ ፌዴራል ና በብዙ ግዛቶች እንዲሁም በአንዳንድ አውሮፓ ሀገራት ራስን ለመወንጀል ያለ መብደድ መብት/The Privilege Against Self-Incrimination/ ሃሳብን ከመግለፅ ጋር ብቻ የተያያዘ ነዉ። ተገዶ የጣት አሻራ ከመስጠት ጋር እንዲሁም ፎቶግራፍ ከመነሣትና ከመለካት ጋር አይገናኝም ተብሎ ይወሰዳል።

የመወያያ ነጥቦች

1. ተከሣሽ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል በነፃነት አልሠጠሁም ቢል የማስረዳት ሸክሙ በቀጥታ ተከሣሹ ላይ ይወድቃል ወይስ ዐቃቤ ሕግ በቅድሚያ በነፃነት ቃሉ መሰጠቱ በደጋፊ ማስረጃ የደረጃ ምስክርን በመሳሰለ ማረጋገጥ አለበት?

1. ለፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሠረት የተሰጠ ቃል በማስረጃነት ሲቀርብ ተቃውሞና መከላከያ ሊቀርብበት ይችላል ወይ?

2. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 25 መሰረት ፖሊስ ምርመራ አጣርቶ ተጠርጣሪው ወንጀል መፈፀሙን የሚያሣይ ማስረጃ ቢያጣ ተጠርጣሪውን ማስቀረብ ነው ያለበት ወይስ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ማስተላለፍ?

4. በተጠርጣሪው ላይ በፍ/ቤት የመያዝ ትዕዛዝ የሚሰጠው ምን ዓይነት ሁኔታዎች ሲረጋገጡ ነው?

5. ያለፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ፖሊስ ተጠርጣሪን የሚይዝባቸው ሁኔታዎች ምንድናቸው?

6. ፖሊስ ተጠርጣሪውን በጣቢያ ዋስትና የሚለቅባቸው ሕጋዊ መንገዶች ምንድናቸው?

7. በፍ/ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ ለመስጠት ምን መረጋገጥ አለበት?

8. ያለ ፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ብርበራ በፖሊስ ሊካሄድባቸው የሚችልባቸው ሁኔታዎች ምንድናቸው?

9. ለምሳሌ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ለኤችአይቪ ወይም በግበረ ሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፍ በሽታ እንዲመረመር ተጠይቆ ፍቃደኛ ባይሆን ሊገደድ ይገባል ወይ?

10. በወንጀል የተጠረጠረ ሰው አሻራ ለመስጠት ፍቃደኛ ባይሆን ሪኮርድ እንዳለበት ለማጣራት በኃይል እንዲሰጥ ሊደረግ ይገባል ወይ?

11. **በሕጋዊ እስር ለማጣራት ወይም ብርበራ አጋጣሚ ያልታሰበ የወንጀል የሌላ ማስረጃ ቢገኝ ውጤቱ ምን ይሆናል?**

12. **በማስገደድ ወይም በሕገ ወጥ ብርበራ የተገኘ ማስረጃ ቢቀርብ ሕጋዋ ውጤቱ ምን መሆን አለት? በህገ ወጥ መንገድ በብርበራ ስለተገኘ ማስረጃ ውጤት በህገ መንግስቱ በግልጽ የተደነገገ ነገር አለመኖሩን እንዴት ያዩታል?**

13. **መንገድ ላይ ወይም ወደተለያዩ መንግሥታዊ የሆኑ ወይም ያልሆኑ ተቋማት ለመግባት የሚደረግ ፍተሻ ሕገ ወጥ ነው ወይ?**

ምዕራፍ አራት

የጊዜ ቀጠሮ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች፡-

- **የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሰብአዊ መብት ለማረጋገጥ ያለውን ሚና ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡**
- **በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነ ስርዓቶችን አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፡፡**

በመርህ ደረጃ ማስረጃ አሰባስቦና ክስ ለመመስረት በሚያስችል ጊዜ ተጠርጣሪ መያዝ እንዳለበት የሚታመንበት ቢሆንም የወንጀል ድርጊት እስከተፈፀመ ድረስ የጎበረተሰቡን ሕይወት ንብረትና ሰላም ለመጠበቅ ሲባል ወንጀል ፈፃሚዎችንና በወንጀል ድርጊት ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ሥር ማዋል አስፈላጊ ነው፡፡ በሰው ልጆች የሥልጣኔ ማደግ እና በቴክኖሎጂ እድገት በዘመኑ የሚፈፀሙት ወንጀሎች ከአደገኝነት በላይ ውስብስብነት አላቸው፡፡ በመሆኑም ወንጀለኛውንና የወንጀል አደራረጉን ለማወቅ፣ ማስረጃ አሰባስቦ ፍርድ ቤት ለማቅረብ ጊዜን፣ ከፍተኛ ዕውቀትን፣ ብልሀትንና ትዕግስትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ሕግ አውጪው ይህንኑ ከግምት በማስገባት አንድ ወንጀል ፈጽሞ ወይም ተጠርጥሮ በሕጉ መሰረት በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የዋለው ሰው ማስረጃ ተሰባስቦ ምርመራው እስኪጠናቀቅ ድረስ በምን ሁኔታ ሊቆይ እንደሚገባው ደንግጎአል፡፡ በቁጥጥር ሥር መቆየቱ አስፈላጊ ከሆነ አስፈላጊነቱን ማን እንደሚወስን፣ በምን መለኪያ እንደሚወሰን፣ በዚህን ወቅት የታሳሪው መብቶች ምን እንደሆኑና በዚህ ረገድ ከሕጉ አተረጓጎምና ከተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን በዚህ ክፍል ስር እናያለን፡፡

4.1 የጊዜ ቀጠሮ ትርጉምና ዓላማው

የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችም ሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንድ በመርማሪ/ፖ/ሊስ በተያዘ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት እንዳለው ይደነግጋሉ፡፡ በተለይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንድን ሰው የያዘ የፖ/ሊስ ባልደረባ ወይም የህግ አስከባሪ በ48 ሰዓት የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ ቤት በማቅረብ ተከሳሹ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ፤ የተያዙት ሰዎች ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት እንዳላቸው ደንግጎአል (አንቀፅ 19/4)፡፡ ይህ ሕገ መንግስታዊ ዕውቅና ያገኘው መርህ በ48 ሰዓታት ውስጥ ለፍርድ ቤት መቅረብ በዝርዝር ሕጎችም ውስጥ ተገልጿል፡፡ መርማሪው/ ፖ/ሊስ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ዜጉችን ያለአግባብ በመያዝ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተግባር እንዳይፈጽም ለመከላከል ሐገራት በህግ ከሚያደርጉት ጥበቃ አንዱ የተያዘ ሰው በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ማድረግ ነው፡፡ በሀገራችንም ይህ መብት በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 19/3 እና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 29/1 መሰረት በወንጀል ተጠርጥረው ለተያዙ ሰዎች የተረጋገጠ መብት ነው፡፡

ተጠርጣሪው ከተያዘ በኋላ ፍ/ቤት ወዲያውኑ እንዲቀርብ የሚያስፈልገው የእስሩን ህጋዊነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ተጠርጣሪው እንደቀረበ ፍ/ቤቱ ማንነቱን አረጋግጦ ከመዘገበ በኋላ በምን ዓይነት ወንጀል ተጠርጥሮ እንደተያዘ ለተጠርጣሪው ሊገልፅለት ይገባል፡፡ ከዚህ በኋላ ፖ/ሊስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ ምክንያቱን ከፖ/ሊስ ማጣራት አለበት፡፡ የተጠርጣሪውም ሐሳብ መሰማት አለበት፡፡ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈቀድበት በቂ ምክንያት ከሌለ እና የተጠረጠረበት ወንጀል ዋስትና የማያስነፍግ ከሆነ ተጠርጣሪው በዋስትና እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ማዘዝ አለበት፡፡ የጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ፖ/ሊስ ያቀረበው ተጨማሪ ምርመራ የማጣሪያ ጊዜ ላይ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት የተጀመረ የፖ/ሊስ ምርመራ የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ፣ የቀረውን ምርመራ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዜ፣ የተጠርጣሪው በእስር ላይ መቆየት አስፈላጊነት ለማረጋገጥ መርማሪውን በመጠየቅ እና እንደአሰፈላጊነቱ ምርመራ መዝገብን በመመልከት ማጣራት ይጠበቅበታል፡፡

መርማሪው የያዘውን ሰው በ48 ሰዓታት ወይም በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት ደንግጓል፡፡ ይህ ማለት ሁኔታዎች ምቹ ከሆኑ የግድ 48 ሰዓት ፖሊስ መጠበቅ እንደሌለበት የሚገልጽ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ አመቺ ካልሆነ (በተለይም በጉዞ ምክንያት የተነሳ) የተያዘው ሰው ፍርድ ቤት እስኪደርስ 48ቱ ሰዓት ሊያልፍም እንደሚችል ነው፡፡

መርማሪው በአንቀፅ 29 በተገለፀው መሰረት ፍርድ ቤት ሲያቀርበው ግለሰቡን ለምን እንደያዘው ለፍርድ ቤቱ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ መርማሪው በዚህ ደረጃ ተከሳሹ ምን ወንጀል ፈጽሞ ወይም በምን ወንጀል ተጠርጥሮ እንደሆነ፤ ወደ ፍርድቤት እስከቀረበበት ባለው ጊዜ ውስጥ የተወሰዱትን እርምጃዎች በሙሉ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት አለበት፡፡

ፍርድ ቤቱ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ አንቀጽ 59/1 መሰረት ተከሳሹ በሕግ መያዙን ከሕግ ውጪ የሀይልና የማንገላታት ሥራ በተያዘው ሰው ላይ ያልተፈፀመ መሆኑን ካረጋገጠ፤ ተከሳሹ ፈፀመ የተባለው ወንጀል ክብደትና ሁኔታ ከመርማሪው የቀረበውን ሪፖርትና ተከሳሹም የሚለውን በመስማት ተከሳሹ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ወይም በዋስ እንዲለቀቅ ሊወሰን ይችላል፡፡ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 59 (1) የተገለፀው በመርማሪው በተደረገው ምርመራ ተጠናቀቀም አልተጠናቀቀ ተከሳሹ ፈፀመ የተባለው ወንጀል ማረፊያ ቤት የሚያስቆይ ነው? ወይስ በዋስትና የሚያስለቅቅ ነው? ግልፅ ህግ ባይኖረም ተከሳሹ የፈፀመው ወንጀል የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. በሚፈቅደው መሰረት ተጠናቆ እና ራፖር ተዘጋጅቶ ለዐቃቤ ሕግ እስኪላክና መዝገቡን ዘግቶ ለመርማሪው እስኪመልስ ድረስባለው ጊዜ የተከሳሹ በማረፊያ ቤት መቆየት አስፈላጊነት የሚወሰንበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ የወንጀል ሕግ ስነ ስርዓት ለምርመራ እንደሚፈቀድ የጊዜ ቀጠሮ ሊቆጠር አይገባውም፡፡ መርማሪው በራሱ አነሳሽነት የሚጠይቀው ሳይሆን የተከሳሹ ድርጊት የሚወስነው ነው፡፡

መርማሪው ተከሳሹ ወንጀሉን በመፈጸሙ ወይም ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በመጠርጠሩ በቁጥጥር ሥር አውሎት የሚካሄደው ምርመራ በ48 ሰዓት ያልተጠናቀቀ ሲሆንና ይህንንም ምርመራ ለማጠናቀቅ እንዲያስችለው ተከሳሽ ማረፊያ ቤት ይቆይ ዘንድ የሚጠይቀው ተጨማሪ ጊዜ ወይም ምርመራው ተጠናቆም ቢሆን ለዐቃቤ ሕግ ተልኮ ውሳኔ እስኪሰጥበት

ድረስ በመርማሪው አነሳሽነት ፍርድ ቤት ተከሳሹ ማረፊያ ቤት እንዲቆይ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 59 (2) የሚጠየቀው ጊዜ ነው የጊዜ ቀጠሮ የሚባለው፡፡

የዚህ ሕግ ሥርዓት ዓላማው ሁለት ሲሆን አንደኛው የአንድን ተከሳሽ መብት ያለአግባብ በመለጠጥ በሕግ ከለላ ሥር ወንጀል የፈጸመ ሰው እንዳያመልጥና ወንጀሉን ተድበስብሶ እንዳይቀር መረጃ ለማሰባሰብና ጉዳዩን በመረጃ ለማንጠር በቂ ጊዜ እንዲገኝ የማድረግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠርጣሪው ተለቆ መረጃ ለማጥፋትና ለመደበቅ ዕድል እንዳያገኝ ማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው የጊዜ ቀጠሮ አላማ፡- ተከሳሹ በመርማሪው ፍላጎት (discretion) ብቻ መርማሪው በፈለገው ጊዜ ተከሳሽን እስር ቤት ለማቆየት ዕድል እንዳያገኝ የሚጠየቀው የጊዜ ቀጠሮ ለምርመራው ብቻ መሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንዲሆን የተከሳሽ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፍርድ ቤት መቅረብ የተከሳሹ የአካል ደህንነትና አያያዝ በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚያደርግ መሆኑን ማረጋገጥ ፤ ተከሳሹም ፍርድ ቤት ሲቀርብ የመደመጥ ዕድል ስለሚያገኝ የተከሳሹን የአካል ደህንነትና መብት ከመጠበቅና የተከሳሹ የመንቀሳቀስ መብትም ያለ አግባብ ተፅዕኖ እንዳይደረግበት አላማ ያደረገ መሰረታዊ የስነስርአት መርህ ነው፡፡

4.2. በጊዜ ቀጠሮ የሕጉ አተረጓጎም

የጊዜ ቀጠሮን ለመጠየቅም ሆነ የጊዜ ቀጠሮን አስመልክቶ የሚጠቀሰው ሕግ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 59 (1፣ 2፣ 3) ነው፡፡የሕጉ ንዑሳን አንቀፆች ተለያይተው ሲታዩ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ይመስላሉ፡፡ ንዑስ አንቀፅ አንድ በአፈፃፀም ሲታይ ከተከታዮቹ ንዑሳን አንቀፆች ይልቅ ተጣምሮ መታየት ያለበት ከወ.መ.ሕ.ስ.ስ. አንቀፅ 29 ጋር ነው የሚል ድምዳሜ ሊያስከትል ይችላል፡፡ አንቀፅ 29 የተመቻቸ ሁኔታ ካለ ፖሊሱ ተከሳሹን በ48 ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤት የማቅረብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 59 (1) በዚህ ሁኔታ መርማሪ ያቀረበውን ተከሳሽ ፍርድ ቤቱ በምን ሁኔታ ማስተናገድ እንዳለበት ነው፡፡ በመሆኑም የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 29 እና 59 (1) ተደጋጋፊ አንቀጾች መሆናቸው ግልፅና የማያሻማ ነው፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 28 በሚለው መሰረት አንድን ተከሳሽ መርማሪው በፖሊስ ዋስትና ከለቀቀው በአንቀጽ 29 መሰረት ፍርድ ቤት ሲቀርብ ፍ/ቤቱ በዋስ ከለቀቀው የአንቀፅ 29

(2) እና (3) አፈጻጸም በዚያው ላይ ቁሞ ተከሳሹ የሚቀርብበትን ክስ ብቻ ይጠባበቃል ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ብዙውን ጊዜ እንደሚወሳው በአንቀጽ 29 (1) መሰረት መርማሪው ተከሳሹን ፍርድ ቤት የሚያቀርበው ሁልጊዜም ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ እንዲፈቀድለት ብቻ መሆን አይገባውም የሚል ክርክር ሊያስነሳ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 59 (2) እና (3) ተደጋጋፊዎች ናቸው፡፡ የነዚህ ሁለት ንዑስ አንቀጾች ተግባራዊነት የሚነሳው መርማሪው በአንቀጽ 29 (1) መሰረት ለፍርድ ቤቱ ያቀረበውን እስረኛ ሕጉ በደነገገው የ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ምርመራውን አጠናቆ ያለመጨረሱንና ቀሪ የምርመራ ስራውን ለማከናወን ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ሲያመለክት ብቻ ነው፡፡ እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊሰጠው የሚገባው መርማሪው እንዲፈቀድለት የሚጠይቀው ጊዜ ምርመራውን ለማጠናቀቅ እንጂ ለመጀመር እንዳልሆነ ግልጽ መሆን ይገባዋል፡፡ በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሟል ወይም ስለመፈጸሙ ይጠረጠራል ለማለት ግለሰቡን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ከመታቀዱ በፊት ተከሳሹ በእጅ ተፍንጅ የወንጀል ተግባር ላይ መገኘቱ ወይም የተፈፀመ ወንጀልም ከሆነ ግለሰቡ ከመያዙ በፊት ለጥርጣሬ የሚያበቃ በቂ የመጀመሪያ ደረጃ (first hand evidence) ወይም የአካባቢ (circumstantial evidence) መኖር ይገባቸዋል፡፡ ያለበለዚያ በይሆናል ሰውን ይዞ መነሻ ማስረጃ ለመፈለግ የጊዜ ቀጠሮ መጠየቁ በግለሰቡ መብት ላይ ከፍተኛ ጫናን ሊያስከትል ይችላል፡፡

መርማሪው በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 59 (2) መሰረት ምርመራውን ለማጠናቀቅ ፍርድ ቤቱን በቂ ጊዜ ለመጠየቅ መብት ቢኖረውም በንዑስ አንቀፅ 3 በበቂ ጊዜ የሚባለው ገደቡ ለአንድ ጊዜ ከ14 ተከታታይ ቀናት እንደማይበልጥ ተደንግጓል፡፡ የሚሰጠው የጊዜ ቀጠሮ በ48 ሰዓት ውስጥ ላልተጠናቀቀ ለምርመራ መሆኑ አንቀፅ 29 እና 59 (1 ና 2) አጣምሮ በማንበብ መረዳት እየተቻለ በንዑስ አንቀፅ 3 ላይ <u>"ለእያንዳንዱ በማረፊያ ቤት ለማቆየት የሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ..."</u> ተብሎ የተነገረው አባባል የጊዜ ቀጠሮን ጥያቄ በጣም ውስብስብ አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም የሕጉ አፃፃፍ የጊዜ ቀጠሮን በተደጋጋሚ መስጠት እንደሚቻል አፃፃፉ እንደምታ (አማላካች ፍንጭ) በመስጠቱና በጊዜ ቀጠሮውም በጽሑፍ መሰጠቱ ብቻ ነው፡፡

ሕጉ ዳኛው የጊዜ ቀጠሮን ለመፍቀድ መርማሪው ምርመራዬን አላጠናቀቅሁም ከማለቱ በስተቀር ሌላ ምን መስፈርት መከተል እንዳለበት አልደነገገም። ለያንዳንዱ ጊዜ የሚለው የሕጉም አፃፃፍ ሲተረጎም ለእያንዳንዱ ጊዜ ለ14 ቀናት በጽሑፍ በተደጋጋሚ ወደሚለው ስለሚያዘነብል በልምድ በአብዛኛው ለወራት ብሎም ለረጂም ጊዜ አንድ ተከሳሽ በጊዜ ቀጠሮ ብቻ በእስር የሚቆይበት ሁኔታ ይስተዋላል።

ውስብስብና የተያያዙ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ እንደሁኔታው የሚጠናቀቁበትን ጊዜ በቅድሚያ መተንበዩ አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም አንድ የወንጀል ምርመራ መች ተጀምሮ መች እንደሚጠናቀቅም በቅድሚያ መተንበይ አይቻል ይሆናል። እንደ ወንጀሉ ሁኔታ በዳኛውም ሆነ በመርማሪው በጋራ ለሚታመንበት ጊዜ ለምርመራ ቀጠሮ መውሰዱም ባልከፋ፤ ግን የግድ ለመርማሪውም ሆነ ለተመርማሪው ሚዛናዊ በሆነ ጊዜ ማጠናቀቁ ግን ተገቢ ነው። በሕጉ ላይ በነዚህ መመዘኛዎች ባለመኖራቸው በአንዳንድ ሁኔታ መርማሪውን የሚያሳስበው 14 ቀኑ ደረሰ የሚለው እንጂ ምርመራው ምን ያህል ተገፋ የሚለው አይመስልም። በተቃራኒው ሽብርተኝነት በመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 20 (3) ምንም እንኳ ለእያንዳንዱ ጊዜ ቀጠሮ ያስቀመጠው የጊዜ መጠን 28 ቀናት ቢሆንም በአጠቃላይ በምርመራ ወቅት ያለው የጊዜ ወሰን /ገደብ/ ግን ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም ሲል በግልፅ ተደንግጓል።

መልመጃ

1) ውስብስብና ከባድ የሆነው የሽብርተኝነት ወንጀል የተጠረጠረው ሰው በአጠቃላይ ለምርመራ የሚቆይበት ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ እንደሌለበት ሽብርተኝነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 20 (3) ይደነግጋል። በተቃራኒው ሌሎች ከሽብርተኝነት የቀለሉ ወንጀሎች ረጂም ጊዜ ለምርመራ ሲወሰዱ ይታያል። በማረፍያ ቤት ለምርመራ ለመቆየት የጊዜ ወሰኑ (ጣርያው) አግባብነት እንዴት ይታያል? ለምን?

2) ለሌሎች ወንጀሎች በማረፍያ ቤት ለምርመራ ለመቆየት የጊዜ ወሰኑ (ጣርያው) አራት ወራት መሆን አለበት። በስነ-ስርአት ህግ አካሄድ አናሎጂ (analogy)

መከተል ይቻላል የሚል ክርክር ሲነሳ ይስተዋላል፡፡ ክርክሩ እንዴት ይመለከቱታል?

3) የአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 20 (3) አለመከበር ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው? ለምን?

4.3 የተጠርጣሪ መብትና የጊዜ ቀጠሮ

የተያዙ ሰዎች ካሉዋቸው መሰረታዊ መብቶች አንዱ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ለመስጠት ሲወሰን በተቻለ መጠን ምርመራው በፍጥነት የሚጠናቀቅበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት ታሳቢ ተደርጎ መሆን ይኖርበታል፡፡ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 59 (2) ለምርመራ የሚሰጥ ጊዜ መራዘም ማለት በተቃራኒው ተከሳሹ በእስር ቤት የሚቆይበትን ጊዜ ማራዘም ማለት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ሕጉ ለምርመራ የሚሰጠውን ከፍተኛ ጊዜ ስላልተወሰነ እና የጊዜ ቀጠሮን የሚሰጠው ፍርድ ቤት ቀጣይ የጊዜ ቀጠሮዎችን ለመፍቀድ ምን መከተል እንዳለበት እና ምን ካልተሟላ የጊዜ ቀጠሮውን መከልከል እንዳለበት ስላልተወሰነ፤ ብዙ ተከሳሾች በተከሰሱበት ወንጀል ቢፈረድባቸው ሊታሰሩ ከሚገባቸው በላይ በፖሊስ እጅ ይቆያሉ፡፡ በመሰረቱ አንድ በጊዜ ቀጠሮ በእስር እንዲቆይ የተደረገ ሰው ምንም ያህል እንኳ የጊዜ ቀጠሮው በተደጋጋሚነት የተፈቀደ ቢሆንም በፍርድ ቤት ተፈቅዶ የተደረገ እስር ስለሆነ ሕጋዊ ነው፡፡ ግን የዚህ ሁኔታ መራዘም ተከሳሹን ሳይፈረድበት በእስር እንደተቀጣ ያስቆጥረዋል፡፡ በሌላም በኩል ጊዜም ወስዶ በፍርድ ቤት በነፃ ቢለቀቁ የማይመለስ ጉዳት ያስከትልባቸዋል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 20 (3) ሁኔታው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 (1) ላይ የተቀመጠውን የተከሰሰን ሰው ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ መደበኛ ፍርድ ቤት የመሰማት ሕገ መንግስታዊ መርህ ይጋፋል በማለት ሃሳባቸውን የሚያራምዱ የህግ ባለሙያዎች በርካታ ናቸው፡፡

በተከሳሽ ላይ የተጀመረው ምርመራ ተጠናቆ ዐቃቤ ሕጉ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 38 (1) እና 109-122 መሰረት ስልጣኑ ለሚፈቅደው ፍ/ቤት ክስ እስኪመሰርት ወይም በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 42 መሰረት አያስከስስም ብሎ ክሱን መዝጋቱን እስኪያስታውቅ

ድረስ ከተከሳሽ መብት አንፃር ሁለት ችግሮች ይታያሉ፡፡ እነርሱም፣ በምርመራ ሂደት በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 59 (2) መሰረት በመርማሪው ጥያቄ በየ14ቱ ቀናት በፍርድ ቤት የሚሰጡ የጊዜ ቀጠሮዎች መቋጫ ማጣት ነው፡፡ ይህንንም ተገን በማድረግ አንዳንድ የሞያ ስነ-ምግባራቸው ያልጠበቁ መርማሪዎች ምርመራውን ለማጠናቀቅ በቂ ትኩረት መንፈጋቸው ነው፡፡ የወሰደውንም ጊዜ ወስዶ መርማሪው ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀፅ 37 መሰረት ራፖሩን ስልጣኑ ለሚፈቅደው ዐቃቤ ሕግ መላክ ያለበት መሆኑን ህጉ ደንግጓል፡፡ ግልፅ ጎግ ባይኖርም መርማሪው ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ ይህንኑ ለፍርድ ቤቱ ይገልጻል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተከሳሽ የተከሰሰበት ወንጀል ዋስትናን የማያስከለክል ከሆነ ተከሳሹ በዋስ እንዲቆይ፣ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ዋስትናን የሚያስከለክል ከሆነ መኖና ሕክምና በሚገኝበት መደበኛው ማረሚያ ቤት እንዲቆይ ያዛል፡፡ ይህም የሚሆነው ዐቃቤ ሕጉ የምርመራ ራፖሩ ደርሶት በሕግ በራፖሩ ላይ ውሳኔ መስጠት በሚገባው የ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ክስ እንዲያቀርብ ነው፡፡

ዐቃቤ ሕጉ የፖሊስ ራፖሩ በደረሰው በ15 ቀን ውስጥ የሚጠበቅበት ክሱን መክፈት ወይም መዝጋት ብቻ ሳይሆን በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀፅ 38 መሰረት ነገሩ ለቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ወይም ተጨማሪ ምርመራ ማዘዝ እንደሚችል ሕጉ ደንግጎአል፡፡ ምንም እንኳ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ፖሊስና ዓቃቤ ህግ በጋራ ስለሚመረምሩ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀፅ 38 መሰረት ለምርመራ ይመላለስ የነበረው መዝገብ ቁጥር ቀንሷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህጉ ፀንቶ ያለ ከመሆኑ በላይ በአሁኑ ሰአትም በተግባር በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀፅ 38 መሰረት መመርያ መስጠት ያልቀረ በመሆኑ በመዝገቡ ላይ በወቅቱ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት ሲያዳግተው ይታያል፡፡ እነዚህን ነገሮች በጊዜው ለማድረግ ዐቃቤ ሕጉ ብዙውን ጊዜ በሰው ሀይል እጥረት እና በስራ መደራረብ ሲያዳግተው ስለሚታይ ይህ እስኪከናወን ድረስና ክስ እስኪመሰረት ድረስ ተከሳሹ ያለፍርድ በእስር የሚቆይበትን ጊዜ ያራዝመዋል፡፡ በሕጉ በተፈቀደው ጊዜ ዐቃቤ ሕጉ በምርመራ መዝገቡ ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ምን ሊሆን እንደሚችል መልስ ባለማስቀመጡም ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ ለመስጠት የሚተጋበት ሁኔታ የለም፡፡ ዐቃቤ ሕጉ በተለይ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 38 (ሐ) በተደነገገው መሰረት ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ የተሰጠው ሥልጣን ተግባራዊ ሲደረግም ተከሳሽ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በእስር እንዲቆይ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ ይኸውም ዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ምርመራ ሲያዝ በአንዳንድ

መዝገቦች ይህ ተጨማሪ ምርመራ ተሟልቷል ተብሎ መዝገቡ ለዐቃቤ ሕጉ የሚመለሰው ረጂም ጊዜ ሲፈጅ ይታያል፡፡ በተለይ ይህ ጉዳይ የፌዴራል ፖሊስና የፌደራል ዐቃቤ ህግ መዋቅር በየክልሉ በአሁኑ ጊዜ ባለመዘርጋቱ የፌዴራል በሆኑ የወንጀል ጉዳዮች በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ ቁጥር 38 (ሐ) መሠረት የሚሰጠው ተጨማሪ የምርመራ መመሪያ እንደገና ተሟልተው እስኪመለሱ የሚወስደው ጊዜ ይረዝማል፡፡ ይህም ተከሳሹ ከፍርድ በፊት በእስር የሚቆይበትን ጊዜ ያንኑ ያህል ያራዝመዋል፡፡ በተለይ ደግሞ በተጓራባች ክልሎች መህል የተፈጸመ ወንጀል ሲሆን ጉዳዩ ያወሳስበዋል፡፡ ባለቤት የሚጠፋበት ሁኔታም ይከሰታል፡፡

ሌላው በፍርድ ቤት ክስ ከመቅረቡ በፊት የተከሳሹን በእስር መቆየት የሚያራዝመው የዐቃቤ ሕጉ በአንድ ምርመራ መዝገብ ከአንድ ጊዜ በላይ ተደጋጋሚ ተጨማሪ የምርመራ መዝገብ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ዐቃብያነ ሕጎች ስለሚያዩት ተጨማሪ ምርመራ ይሰጥበታል ተብሎ ከመወሰኑ በፊት የማያዳግም የመመሪያ ነጥቦች ስለመሰጠታቸው በአንዳንድ ሁኔታዎች ቁጥጥር ስለማይደረጉ ጭምር ነው፡፡

መልመጃ

1. መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ፖሊስና ዐቃቤ ህግ በጋራ ምርመራ እንዲያካሂዱ ያዛል፡፡ የተጠርጣሪ መብት ከማስከበር አኳያ ፋይዳው ምንድን ነው? ህጋዊ መሰረት አለውን? ተግባራዊ ተፈፃሚነቱ ቤመለከተ ሰልጣኞች ከመጡበት አካባቢ አኳያ እንዲቃኙት ይደርጋል፡፡
2. ምርማራ ሳይጀመር ተጠርጣሪ ተይዞ በ48 ሰዓት ዉስጥ ፍርድቤት ቢቀርብና መርማሪዉ ከዚህ በኋላ ምርመራ ለማካሂድ ተጠርጣሪዉን በቁጥጥር ስር እንደሆነ እንዲቆይ ይፈቀድልኝ የሚል ጥያቄ ቢያቀርብ እንዴት ይወስናሉ?
3. በሌላ በኩል ምርመራዉን ጀምሮ ተጠርጣሪን የያዘ መርማሪ ለ48 ሰዓታት ተጠርጣሪዉን ይዞ ሲቆይ ምርመራዉን ሳይቀጥል አቋርጦ ከቆየ በኋላ ተጠርጣሪዉን ይዞ ፍርድቤት በመቅረብ ምርመራዉን ለማጠናቀቅ ጊዜ ይፈቀድልኝ፣ እስከዚያዉ በቁጥጥሩ ስር እንዲያቆየዉ ፈቃድ ቢጠይቅ ምን ይወስናሉ?በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ

59/2/ *የፖሊሱም ምርመራ ያልተፈጸመ እንደሆነ...* ተብሎና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 24 እና 25 ከተደነገጉት ጋር አገናዝበዉ ይወስኑ

4.4 በጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ የሚከሰቱ ተግዳሮቶችና ችግሮቹ ለማስወገድ የዐቃቤ ህግና የፍርድ ቤቶች ሚና

ከላይ እንደተገለፀው የጊዜ ቀጠሮ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ያልተሟላ ምርመራን ለማሟላት ተከሳሽን ማረፊያ ቤት ማቆየቱ በመርማሪውና በፍርድ ቤት ግድ መሆኑ ሲታመንበት ነው፡፡ መርማሪውም ሆነ ዐቃቤ ህግ የጊዜ ቀጠሮን በሚጠይቅበት ጊዜ የጊዜ ቀጠሮው ያስፈለገበትን ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ሁኔታው መመስረት ያለበት የምርመራ መዝገቡን በተሟላ ሁኔታ ለማጠናቀቅ የተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት መቆየት ቀጣይ ምርመራን ለማጠናቀቅና ከወንጀሉ ጋር የተያያዙትን ሰዎች፣ ቁሶችና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ለሚጠይቀው ጊዜና ብልሀት የግለሰቡ መለቀቅ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያመጣ ነው፡፡ ከዚህ አኳያም በልምድ ችግሮች ሲገጥሙ ይታያል፡፡

የመጀመሪያው ፍርድ ቤቶች መርማሪው ከአንድና ከሁለት ጊዜ የበለጠ የጊዜ ቀጠሮን ሲጠይቅ መርማሪው የጊዜ ቀጠሮው እንደገና እንዲራዘም የጠየቀበትን ምክንያትና በእስካሁኑ ያደረገውን ጥረት ሳያገናዝቡ ግለሰቡን ለመልቀቅ ሲወስኑ ከባድም ሆነ ቀላል ወንጀል ተሰርቶ በጊዜ ቀጠሮ ያለመፈቀድ ምርመራው መና የሚቀርበት ሁኔታ አለ፡፡

ሁለተኛው አንድ መርማሪ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 59 (2) መሰረት ምርመራውን ለመፈፀም በሚጠይቅበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደና መርማሪው የጊዜ ቀጠሮውን መከልከሉ አግባብ መስሎ ካልታየው ይግባኝ የሚልበት ሥርዓት በሕጉ በግልፅ ባለመዘርጋቱ መርማሪው ዳር ሊያደርስ ያሰበው የወንጀል ድርጊት በመሀል የሚስተጓጎልበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ዳኞች የጊዜ ቀጠሮን የሚሰጡበትም ሆነ ሊከለክሉበት የሚችሉበት ግልፅ መስፈርት ባለመኖሩ አንዳንዴ በማያስፈልግም ጉዳይ የጊዜ ቀጠሮን ሲሰጡ ይታያል፡፡ ለምሳሌ አንድ በቂ ስንቅ የሌለው ሰው ቼክ ፈርሞ በመስጠቱ የተከሰሰ ሰውን በተመለከተ መርማሪው የጊዜ ቀጠሮ ሲጠይቅ መፍቀዱ ጠቀሜታ አይታይም፡፡ በአንፃሩም ውስብስብነቱ በግልፅ ለታወቀ ከባድ የውንብድና ወንጀል የጊዜ ቀጠሮን መርማሪው መጠየቁ ወይም በተደጋጋሚ መጠየቁ አላስፈላጊ ነው በማለት መከልከሉ ምርመራውን መና ሊያስቀረው ይችላል፡፡

ይህም የሚያሳየው ሕጉ ለጊዜ ቀጠሮ መስጠትም ሆነ መነፈግ መስፈርት ስላላስቀመጠ ጉዳዩ በዳኞቹ ፈቃደኝነት ብቻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው።

በ3ኛ ደረጃ መርማሪው በተመርማሪው ላይ ሕጉ በሚያዘው መሰረት የጊዜ ቀጠሮ እየጠየቀ እና ፍርድ ቤቱም እየፈቀደ ቆይቶ ምርመራው ሲጠናቀቅ የምርመራ መዝገቡን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርአት አንቀፅ 37 በሚያዘው መሰረት መብቱ ለሚፈቅድለት ዐቃቤ ሕግ ይልካል። ተከሳሹ እስከዚያው ጊዜ ድረስ በማረፊያ ቤት የቆየው የጊዜ ቀጠሮን የሚጠይቅበት ሕጋዊ ሁኔታ የለም። የምርመራው መዝገቡ መብቱ ለሚፈቅድለት ዐቃቤ ሕግ ተልኮ ክስ እስኪመሰረት ለሚወስደው ጊዜ ተከሳሹ በምን ሁኔታ ሊቆይ እንደሚገባው ሕጉ ግልፅ ባይሆንም የዳበረ የአሰራርና ልምምድ አለ። ምንም እንኳ የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ተመስርቶ የዓቃቤ ህግና ፖሊስ በጋራ መመርመር ይህ ችግር ቀንሶታል ቢባልም ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ማለት ግን አይቻልም። አብዛኛውን ጊዜ መርማሪው የምርመራ መዝገቡን መብቱ ወደሚፈቅድለት የዐቃቤ ሕግ ከላከ በኋላ ተከሳሹ ከመጀመሪያው የዋስትና ጥያቄን ያላነሰ በመሆኑ ወይም የዋስ መብት ተፈቅዶለት በቂ ዋስ በማጣቱ ወይም ወንጀሉ የዋስትና መብትን የማያስፈቅድ በመሆኑ በፖሊስ እጅ ያለ እስረኛ ስለሆነ የዐቃቤ ሕግ ውሳኔ እስኪገኝ ተከሳሹ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ ይጠየቃል። ከመሰረቱ ይህ ችግር ሲታይ የፍትህ አካላት ያመጡት ችግር ብቻ ሳይሆን ሕጉም የፈጠረው ክፍተት ነው። ነገር ግን ከፍትህ አካላት የሚመነጩት ችግሮች በፍትህ አካላቱ የራሳቸው አቅም ሊፈትዋቸው ይገባል። አቃቤ ህጎች በተወሰነላቸው የ15 ቀናት የጊዜ ገደብ መዘገባቸው መወሰን ከቻሉ ችግሩ ከሚገባ በላይ ያቃልለዋል።

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/አንቀፅ 60 እስከ 62 የተመለከተው በማረፊያ ቤት የመቆየት ሁኔታ የሚመለከተው ለምርመራ በማረፊያ ቤት የሚቆይን ሰው ነው። ማረፊያ ቤት የሚቆየው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/አንቀፅ 59 (3) መሰረት በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ ቢሆንም የሚቆየው ለምርመራ ሲባል ነውና የሚያርፈውም በፖሊስ ጣቢያ ነው። ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ ግን ለዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገቡ ላይ እስኪወሰን ድረስ ተከሳሹ ስለሚቆይበት ሁኔታ ሕጉ ግልጽ አይደለም። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/አንቀፅ 203-205 የተገለፀውና በሥ/ሥ/ሕ 3ኛ ሰንጠረዥ 13ኛ እና 14ኛ ፎርም የተደገፈው የተፈረደበትን ሰው የሚመለከት ነው።

ከዚህ በላይ በተገለፀው መሰረት አንድ ሰው በዐቃቤ ሕግ ተከሶ ፍርድ ቤት እስካልቀረበ ድረስ ማረሚያ ቤት እንዲቆይ ለማድረግ የሚቻልበት የሕግ ሁኔታ የሌለ ይመስላል፡፡

ሆኖም ግን አንድ ተከሳሽ በዋስ የሚፈታበት ሕጋዊ ሁኔታ እስከሌለ ድረስ በጥፋቱ በፍርድ ቤት እስኪፈረድበት ድረስ በማረሚያ ቤት ሊቆይ የሚችልበት የሕግ ሁኔታዎች እስካሉ ድረስ ዐቃቤ ሕጉ ክሱን ፍርድ ቤት እስኪያቀርብ ወይም በምርመራ መዝገቡ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተከሳሹ በዋስ መብቱ መጠቀም ካልቻለ ወይም ወንጀሉ በሕግ ዋስትናን የሚያስከለክል ከሆነ ተከሳሹን በፍርድ ቤት ቁጥጥር መደበኛው ማረሚያ ቤቱ ማቆየቱ ተመራጭነቱ ለተከሳሹም ጭምር ይመስላል፡፡

ስለሆነም ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ ባንድ በኩል ፍርድ ቤቱ በሌላ በኩል በመሆን ተከሳሹ ተከሶ ፍርድ ቤት እስኪቀርብ ድረስ ማረሚያ ቤት ይቆይ ወይም በፖሊስ እጅ ይቆይ በሚለው ነጥብ ተመሳሳይ አቋም የላቸውም፡፡ ምርመራው በተጠናቀቀ መዝገብ ለፌዴራል ዐቃቤ ሕግ መላኩ ከተገለፀ ተከሳሹ በዋስትና መብቱ ያለመጠቀሙ ከተረጋገጠ ወይም ወንጀሉ ዋስትናን የሚያስከለክል ከሆነ በምርመራ መዝገቡ ላይ ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ እስኪሰጥ ጠርጣሪው ማረሚያ ቤት ቢቆይ ምን ችግር አለው? ጠቃሚም ሆነ ጎጂ ጎኖች አሉት?

አንድ በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ሰው እንዴት ፖሊስ ሊይዘው ይገባል? የተያዙ ሰዎች መብቶች ምንድን ናቸው? ሕጋዊ እስር ከሕገ ወጥ እስር የሚለየው እንዴት ነው? በፖሊስ የሚደረገው ምርመራ ሥነ ሥርዓት በምን መመራት እንዳለበት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስትን ጨምሮ በሌሎች ሕጎችም መወሰኑ ለሰው ልጆች መብት ያለመጣስና መከበር የመሰረት ድንጋይ ነው፡፡ በተይም የፍትህ አካላት ሚና የላቀ ነው፡፡ ህገመንግስቱ በአንቀጽ 9 ከህገመንግስቱ ጋር ተቃራኒ የሆነ ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ ወዘተ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው ይደነግጋል፡፡ እንዲህ አይነት ህጎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ከማድረግ አንፃር የዓቃቤ ህግና ዳኞች ሚና ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፣ ጠንካራ፣ የሕግ የበላይነትን ያከበረና ያስከበረ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ፍትህ የሚሰጥ የፍትህ አካል መኖሩ ለሰባአዊ መብቶች መከበር፣ ልእልናና ዘላቂነት መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ ሊረዱ ይገባል፡፡ የፍትህ አካላት ሀላፊነታቸውን በአግባቡ ተወጡ ማለት የሰባአዊ መብቶች መከበር ስር እንዲሰድ

አደረጉ ማለት ሲሆን፣ ሚናቸውን በአግባቡ አለመወጣት ደግሞ የፍትህ ስርዓቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ከአንቀጽ 14-23 በወንጀልና ከወንጀል ጋር በተያያዙ ጉዳዮች የግለሰቦችን መብቶች አስፍቶ መደንገጉ ለዚህ ጉዳይ የተሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ነው። በበፊቶቹም ሕገ መንግስታትና ዝርዝር ሕጎች መሰረተ ሃሳቦች ቢኖሩም እነዚህ ሕጎች በጊዜ ሂደትና በልምድ ከገጠሙአቸው የአሰራር ችግር በመነሳት ለማሻሻልና ለውጥ ለማድረግ ትኩረት ያለመስጠቱ ችግሩን አባብሶታል።

ሌላው በተግባር ጥያቄ የሚያስነሣው የጊዜ ቀጠሮ የሚያስተናግድ ችሎት /የጊዜ ቀጠሮ ችሎት/ ስልጣን ወሰን ነው። ችሎቱ ተጠርጣሪው ያለ አግባብ የተያዘ መሆኑን ቢያረጋግጥ ያለ ዋስትና ሊለቅው ይችላል ወይ? የሚለው ያከራክራል። በህጉ ላይ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከመፍቀድ እና በዋስትና ከማሰናበት ውጪ የተቀመጠ ሌላ ሶስተኛ አማራጭ የሚባል ነገር የለም። ከዚህ አንጻር ችሎቱ ተጠርጣሪውን በዋስትና ብቻ ነው መልቀቅ ያለበት ሊባል የችላል። ነገር ግን በስህተት መያዙን ፖሊስ ቁምር እያረጋገጠ ዋስትና አቅርብ ማለት ምን ትርጉም ይኖረዋል?

በወንጀል ጉዳይ የፍትሕ አስተዳደር ረገድ ለውጥ ከሚያስፈልጋቸው ክፍሎች አንዱ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 59 ነው። ችግሮቹም፣

1) የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 59 ርዕሱ ራሱ <u>በማረፊያ ቤት ስለማቆየት</u> የሚል ሲሆን ንዑስ ቁጥር አንድ የተፃፈው በአንቀጽ 29 መሰረት ስለተያዘው ሰው ነው። የርዕሱ አፃፃፍ በአንቀጹ ውስጥ የተጠቀሱትን ፍሬ ሃሳቦች ያለማካተቱ፤

2) በ59 (3) የተጠቀሰው በፍርድ ቤት ለምርመራ ተብሎ የሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ወሰኑ አለመታወቁና ጊዜው ለምርመራ እንደመሰጠቱ መጠን ፍርድ ቤት ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከመፍቀዱ በፊት በተሰጠው ጊዜ ስለተወሰዱት እርምጃዎች በግልጽ በሕጉ ያለመቀመጡ ናቸው።

ፍ/ቤት ለምን ያህል ጊዜ የጊዜ ቀጠሮ ሊፈቅድ እንደሚችልም በህጉ ላይ በግልጽ ያልተመለከተ ቢሆንም ያለበቂ ምክንያት ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ አይገባም። የሰብዓዊ

መብት ጥሰት እንዳይኖር የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በጥንቃቄ እያንዳንዱን ጉዳይ እያጣራ መፍቀድ አለበት፡፡ በአግባቡ ይህ ከተተገበረ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ አያስፈልግም፡፡ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ጠቀሜታ ቢኖረውም የራሱ የሆነ ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ተጠርጣሪው ከህግ ውጪ ከሌሎች የወንጀል ተሳታፊዎች ጋር በመሆን ሴትን ጠልፎ የደበቀ ቢሆን እና የተጠለፈችው እንዳትለቀቅ የተያዘው ተጠርጣሪ ለመተባበር ባይፈልግ ወይም የተለዩ የተወሳሰቡ ጉዳይዮች ቢያጋጥሙ እና ምርመራውን በህግ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ ባይቻል ሊፈጠር የሚችለውን አስቸጋሪ ሁኔታ አስቀድሞ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

መልመጃ

በጊዜ ቀጠሮ ችሎት ሲታይ በነበረ የከባድ ነፍስግድያ ጉዳይ ምርመራዉ ተጠናቆ ለዐቃቤህግ ዉሳኔ ስለቀረበ ፍርድቤቱ ክስ እስኪቀርብ ተጠርጣሪዉ ማረፊያቤት ይቆይ በማለት ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ መዝግቡን ዘግቶ ወደመዝገብ ቤት መለሰዉ፡፡

1. በቅድሚያ እንዲህ አይነቱ አሰራር ምን ያህል ተገቢ ነዉ ?
2. ፍርድቤቱ መዝገቡን ከመዝጋት ይልቅ ክስ ለማቅረብ ለሚበቃ ጊዜ ቀጠሮ ይዞ ሂደቱን ሊቆጣጠር አይገባም?
3. ዐቃቤህግ ክስ ሳይመሰርት ወይም ሌላ ዉሳኔ ሳይሰጥ ለበርካታ ሳምንታት ወይም ወራት በመቆየቱ ተጠርጣሪዉ መፍትሄ ይሰጠኝ በማለት ቢያመለክት ፍርድቤቱ ምን ሊወስን ይገባል ?
4. ፍርድቤቱ ኃላፊነቱን በምርመራ ክፍሉ ላይ በመተዉ ተጠርጣሪዉ ተይዞ ከነበረበት ማረፊያቤት በተለምዶ ማረሚያቤት ወደ ምርመራ ክፍሉ ወደፖሊስ ጣቢያ እንዲዛወር ቢወስን ምን ያህል ተገቢ ነዉ?
5. የጊዜ ቀጠሮ የሚፈቀድበትን ድግግሞሽ ፍርድቤት በጥብቅ እንዲቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህ እንዲሆን ያስፈለገበት ህገመንግሥታዊ የሰብዓዊ መብት መርህ ምንድን ነዉ ?
6. ከህገመንግሥት ድንጋጌዎች ቁ.19/4/ እና 20/1/ አኳያ ይተንትኑት በየጊዜዉ የሚፈቀደዉ እስከ 14 ቀን የሚደርሰዉ ተጨማሪ የምርመራ ማጣሪያ ጊዜ የእረፍትና የበዓል ቀናትን ያካትታል ወይ?

7. ከጊዜቀጠሮ ጋር ተያይዞ የሚነሳዉ ነገር የዋስትና ነገር ነዉ፡፡ ተጠርጣሪው መደበኛ ክስ ከተመሰረተበት በኋላ ባይቀርብ በጊዜ ቀጠሮ ሂደት በተገባው ዋስትና መሰረት ተከሣሹን የማስቀረብ ነገር ከክሱ መሰማት በኋላ በተገባዉ ዋስትና መሰረት እንዲቀርብ ከሚደረግበት አሰራር የተለየ ሊሆን ይገባል? ተከሣሹ ከጠፋና የጊዜ ቀጠሮ ዋሱ ሊያቀርበው ባይችል የዋስትናው ገንዘብ ገቢ እንዲሆን መታዘዝ ያለበት በጊዜ ቀጠሮው መዝገብ ላይ ነው ወይስ በመደበኛው መዝገብ ላይ? ይህ ዉሳኔ በማን ጠያቂነት ሊሰጥ ይገባል፣ በፖሊስ ወይስ በዐቃቤህግ?

የመወያያ ነጥቦች

1. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል ተጠርጥሮ የተየዘ ሰው እንደቀረበ ለተጨማሪ ጊዜ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ከማዘዙ በፊት ወይም በዋስትና እንዲለቀቅ ከማድረጉ በፊት ምን ማድረግ አለበት?

2. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 59/3 መሰረት የሚሰጠው ተጨማሪ የፖሊስ ምርመራ ማጣሪያ የ14 ቀን ጊዜ ከመንግሥት የስራ ቀናት ውጪ የሆኑትን የእረፍት ቀናትና የበአላት ቀን ያካታታል ወይ?

3. ዋስትና በህግ በሚያስነፍግ ጉዳይ ላይ ፖሊስ ያለ በቂ ምክንያት ምርመራውን ሳያጠናቅቅ ወይም ምርመራው ተጠናቆ የምርመራ መዝገቡ ለዐ/ህግ ከተላከ በኋላ በአፋጣኝ ውሣኔ ሣይሰጥበት ቢቀር የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ምን ማድረግ አለበት?

4. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ዋስትና የሚያስነፍግ የወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረን ግለሰብ ያለ አግባብ መያዙን ቢያረጋግጥ ሊለቀው ይችላል ወይ?

5. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ፖሊስ ያለ በቂ ምክንያት ለተጨማሪ ጊዜ ተጠርጣሪውን በእስር ለማቆየት ጥያቄ በማቅረቡ ምክንያት መዝገቡን ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ሳያዝ ወይም ዋስትና ሳይፈቅድ ቢዘጋው በተጠርጣሪው መብት ላይ ምን ዓይነት ተፅእኖ ያሣድራል? የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ተጠርጣሪው በምን መልኩ ህጋዊ መብቱን ማስከበር ይችላል?

6. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል ተጠርጥሮ የተየዘ ሰውን ያለአግባብ መያዙን ቢያረጋግጥ ያለዋስትና ሊለቅቀው ይችላል ወይ?

7. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ተጨማሪ የምርመራ ማጣሪያ የሚፈቅድበትን ጊዜ በህግ ገድቦ መስቀመጥ ምን አይነት ጥቅምና ጉዳት ይኖረዋል፡፡

8. በጊዜ ቀጠሮ ችሎት አንድ ጊዜ ዋስትና ከተገባ በኋላ ምርመራው ተጠናቆ በዓ/ህግ ለፍ/ቤቱ የወንጀል ክስ ሲቀርብለት ሌላ አዲስ የዋስትና ተከሣሹ እንዲያቀርብ ማደረግ ተቀባይነት ያለው አሰራር ነው ወይ?

8. ለዓ/ህግ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ በኋላ የተከሰሰ ሰው በጊዜ ቀጠሮ ችሎት ዋስትና ግዴታ ከገባ በኋላ ቢሰወር መደበኛ ችሎቱ በጊዜ ቀጠሮ ዋስትና ግዴታ ላይ ትእዛዝ ማስተላለፍ ይችላል ወይ?

ምዕራፍ አምስት

ፍርድቤት ስለመቅረብ እና በዋስ ስለመለቀቅ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ፡-

- የዋስትና መብት ታሪካዊ እድገት፣ ትርጉምና አላማ፣ ዋስትና በመፍቀድና በመከልከል እንደመነሻ የሚወሰዱ የህግና ፍሬ ነገር ሁኔታዎች ይገነዘባሉ፡፡
- የዋስትና መብት በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሰብአዊ መብት ለማረጋገጥ ያለውን ሚና ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡
- በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ከዋስትና ጥያቄ ጋር በተየያዘ ችሎት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነ ስርዓቶችን አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፡፡

በመሆኑም ከዋስትና መብት ጋር ስለሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

5.1 የዋስትና ታሪካዊ እድገት፣ ትርጉምና አላማ

የዋስትና ታሪካዊ እድገት መሰረት ተደርጎ የሚቆጠረው እ.ኤ.አ. ከ1066 በፊት የነበረው የእንግሊዛውያን አስተዳደራዊ ዘውግ ነው፡፡ በወቅቱ የነበሩት የአከባቢ መኳንንት (ሸርፍ) ለዋስትና መብት እውቅና በመስጠት ተግባራዊ ያደርጉት እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1275 የአከባቢ መኳንንት (ሸርፍ) በዋስትና አፈቃቀድ ረገድ ለመጀመርያ ጊዜ ስልጣናቸው በመገደብ የዌስት ሚኒስቴር ገደብ ማበጀቱ፣ እ.ኤ.አ.

በ1689 የወጣው The English Bill of Right ለዋስትና ንድፈሃሳባዊና ተግባራዊ እድገት የላቀ ሚና ማበርከታቸው በዘርፉ የተጻፉ ሰነዶች ያትታሉ፡፡

ዋስትና የፍትሐብሔር ሕጎችና የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት አካል የሆነ ሕግ ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ዋናው ባለዕዳ ወይም የግዴታ ተጠያቂ የሆነ ሰው ለባለገንዘቡ በውል ግዴታ የገባ ሰው ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ዋሱ ባለዕዳውን ተክቶ ለባለገንዘቡ በዕዳው ልክ ገንዘቡን ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት የሕግ ስርዓት ነው (አንቀጽ 1920)፡፡ ይህ አንቀጽ ዋስትና ማለት ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ባይደነግግም ውል ሰጪና ውል ተቀባይ ተባብለው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ባደረጉት ውል ወይም በእነርሱ መካከል ባለ የባለገንዘብና የባለዕዳነት መብትና ግዴታ ውስጥ ከእነርሱ ውጪ የሆነ ሶስተኛ ሰው ባለዕዳው ዕዳውን በሙሉ ወይም በከፊል ያልከፈለ እንደሆነ ወይም ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት ያልቻለ ከሆነ እኔ በእርሱ ምትክ ሆኜ ገንዘቡን እከፍላለሁ ወይም ግዴታውን እወጣለሁ በማለት ለባለገንዘቡ የሚገባለት ውል ነው፡፡ ይህ የዋስትና ትርጉም አቶ ጥላሁን ተሾመ የኢትዮጵያ የውል ሕግ መሰረተ ሃሳቦች በሚል በዓፉት መጽሐፍ ውስጥ ፕላንዩል የተባለ የፈረንሳይ ሕግ ምሁርን ዋቢ በማድረግ ለዋስትና የሰጡት ትርጉም ነው፡፡

በ1952ቱ የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1920 እስከ 1950 ስለዋስትና የተገለፀው አነጋገር የዋስትና ውል ግልጽና የማያሻማ ሆኖ ባለዕዳውን ዕዳውን በውሉ መሰረት ካልተወጣ ለባለገንዘቡ ባለዕዳው ሊከፍለው በሚገባው መጠን ልክ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት በችሮታ ላይ የተመሰረተ ውል ነው ይላል፡፡

በወንጀልና በወንጀል ነክ ጉዳይም አንድ ሰው ወንጀልን በመፈፀሙ ወይም በወንጀል ድርጊት ተጠርጣሪ በመሆኑ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በመታሰሩ ወይም ሊታሰር የሚገባው ከሆነ ወንጀል ፈፃሚነቱ በፍርድ እስኪወሰን ድረስ በዋስ እንዲቆይ የሚደረግበት ስርዓት ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ የዋስትና ዓላማው የወንጀል ድርጊትን የፈፀመ ወይም በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረ ሰው በአንድ በኩል ወንጀሉን ፈጽሞአል ተብሎ በሕግ ሳይወሰንበት እንዳይታሰር ሲሆን፣ በሌላ በኩል ለተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት ለፍትሕ አካላት ይቀርብ ዘንድ ዋስ የሚጠራበት ሥርዓት ነው፡፡ በወንጀል ሕግ መታሰር ለተፈፀመ

ወንጀል ቅጣት ነው፡፡ አንድ ወንጀለኛን ለመቅጣት የሚችለው ደግሞ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው፡፡ አንድ ሰው በፍርድ ሳይወሰንበት የሚታሰር ከሆነና ምናልልባት በፍርድ ቤት ከተከሰሰበት ወንጀል ነፃ ከተባለ የማይመለስ ጉዳት እንደደረሰበት ይቆጠራል፡፡ ከዚህም አኳያ አንድ በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረ ሰው በአንድ በኩል በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት እንዳይቀጣና በሌላ በኩል በቁጥጥር ስር ባለመዋሉ ምክንያት ከፍርድ እንዳያመልጥ የሚደረግበት ዘዴ ዋስትና ነው፡፡ ይህ ዘዴም በብዙ አገሮች በተግባር ላይ የዋለ የወንጀል ሕግ ስርዓት ሲሆን አለም አቀፋዊ ተቀባይነትንም ያገኘ መርህ ነው፡፡

የ1966 (እ.ኤ.አ) የተባበሩት መንግስታት የሲቪል የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 9 (3)፡-

> *It shall not be the general rule that person awaiting trial shall be detained in custody, but realease may be subject to guarantees to appear for trial at any other stage of judicial proceeding and should accastion arise for execution of judgment.*

በዚህ ዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት በወንጀል የተጠረጠረ ማንኛውም ግለሰብ የግድ መታሰር የለበትም፡፡ በማንኛውም ደረጃ ለፍርድ ስለመቅረቡ ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ በእስር መቆየት የለበትም ከሚል መርህ ነው ዋስትና የሚመነጨው፡፡ የዋስትና መብት ሌላው መንስኤ በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችና አገራችን ጨምሮ በብዙ ሀገሮች ሕገ መንግስታት ተቀባይነት ያገኘው በወንጀል የተከሰሰ ሰው ጥፋተኝነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ እንደ ንፁህ መገመት አለበት (presumption of innocence) እና ተከሳሽ ከፍርድ በፊት መቀጣት የለበትም የሚሉ መሰረተ ሃሳቦች ናቸው፡፡

ይህ አለም አቀፋዊ መርህ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 9 (4) መሰረት የአገሪቱ ህግ አካል ነው ማለቱ በቂ ሳይሆን፤ እነዚህ አለም አቀፍ መርሆዎች መነሻ በማድረግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በህግ በሌላ አኳኋን እስካልተወሰነ ድረስ የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው በአንቀጽ 19 (6) ተደንግጎአል፡፡

5.2 በዋስ ስለ-መለቀቅ፣ የጣብያ ዋስትና፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ጥያቄና አወሳሰን

የሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 19 (3) የተያዘ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት እና ለመታሠር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ሊገለጽለት እንደሚገባ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የወ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 29ም በተመሳሳይ መልኩ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ፍ/ቤት ያልቀረበ ተጠርጣሪ በ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/4 መሰረት ፍ/ቤት የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሕገ መንግሥት አንቀጽ 19(6) የተያዘ ሰው በዋስ የመለቀቅ መብት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህ በመርህ ደረጃ የተቀመጠ በዋስ የመፈታት መብት ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 17 ጋር ተገናዝቦ ካልታየ የተሳሳተ ድምዳሜ ሊያደርስ ይችላል፡፡ ምክንያቱም በዋስ የመፈታት መብት በሕግ በተቀመጡ ምክንያቶች ሊገደብ ይችላልና ነው፡፡

ዋስትናን የሚፈቅዱ አካላት የዋስትና ወረቀቱን የፈረመው ግለሰብ የዋስትና ግዴታውን ካልተወጣ ዋሱን በገባው ግዴታ (በዋስትናው ወረቀት) መሰረት ግዴታ የገባበትን ገንዘብ እንዲከፍል ለማድረግ የሚችሉና በዋስ የተለቀቀውንም አስገድዶ ለሕግ ለማቅረብ ስልጣን የተሰጣቸው ፖሊሶችና ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 28 እና 63 የተገለፀውም ይኸው ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 19 (6) አኳያ የተያዘ ሰው የዋስ መብቱ እንዲከበርለት መጠየቅ ሕገ መንግስታዊ መብቱ ሲሆን፣ የግለሰቡ በዋስ መለቀቅ ወይም ያለመለቀቅ በዝርዝር ሕጎች ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ነው፡፡

በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ ቁጥር 28 (1) መሰረት የተሰራው ወይም አቤቱታ የቀረበበት ወንጀል በጽኑ እስራት ወይም ይህንን በመሰለ ተለዋጭ ቅጣት የማያስቀጣ ሲሆን ወይም ወንጀል የተሰራ ለመሆኑ ወይም እንዲቀርብ የተጠራው ወይም የተያዘው ተከሳሽ አቤት የተባለበትን ወንጀል መስራቱ የሚያጠራጥር ሲሆን በአፈፃፀም ረገድ ክፍተቶች ቢኖሩትም ተከሳሹ ዋስትናው ካላከበረ የገንዘብ መቀጫ እንዲከፍል የራስ ዋስትና ወረቀት በማስፈረም ወይም ለዚሁ ገንዘብ ዋስ የሆነውን ሰው የዋስትና ወረቀት በማስፈረም ፖሊስ ተከሳሹን ሊለቀው ይችላል፡፡

ይህ አንቀጽ አንድን ተከሳሽ ወይም ተጠራጣሪ ፖሊስ በዋስ ለመልቀቅ ስላለው ስልጣን የሚናገር ነው፡፡ <u>ተከሳሹን ወይም ተጠርጣሪውን ፖሊስ ሊለቀው ይችላል</u> የሚለው የሕጉ

አነጋገር አስገዳጅ ሳይሆን ፈቃጅ ነው፡፡ በመሰረቱ በሕጉ በፖሊስ ደረጃ በዋስ የሚያስለቅቁ ወንጀሎችም ቢሆኑ ማንም ሰው በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀጽ 11 በተሰጠው የወንጀል መፈጸምን ለማስታወቅ ባለው መብት መሰረት የወንጀልን መፈጸምና ወንጀል አድራጊውን ሲያመለክት ፖሊስ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 25 እና 26 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የተከሰሰውን ወይም የተጠረጠረውን ሰው የመጥራት መብት አለው፡፡ ፖሊስ ግለሰቡን ከጠራው በኋላ ማተኮር የሚገባው በሚከተሉት መሰረተ ሃሳቦች ላይ ነው፡፡

- የተባለው ወንጀል ተፈጽሟልን? ወይም ስለመፈጸሙ ጥርጣሬ አለኝ ወይ?
- የተከሳሹ ወንጀል ፈጽሟል መባል እውነት ነው? ወይስ በበቂ ጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን የነገሩ የመሰረት ድንጋይ የሆኑትን ሊያስረዱ የሚችሉ ሁለት ዋና ነገሮች ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

ጠቋሚው ወይም ከሳሹ ወንጀል መፈጸሙንና አድራጊው የተጠቆመው ሰው መሆኑን አስመልክቶ የሚሰጠው የከሳሽነት ቃል፤ ተከሳሹ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ ቁጥር 27 መሰረት የሚሰጠው የተከሳሽነት ቃል ናቸው፡፡ ፖሊሱ እነዚህን ሁለት ሁኔታዎች አስመልክቶ የሚደርስበት ግንዛቤ ተከሳሹን በቁጥጥር ሥር ለማቆየት ወይም ላለማቆየት ፍንጭ ይሰጠዋል፡፡ ከዋስትና አኳያ መርማሪው የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባል፡፡

ሀ. ተከሳሹ የቀረበበት ክስ (ቀላልም ሆነ ከባድ) የሚያጠራጥርና ድርጊቱ ያልተፈጸመ ወይም ይህ የተጠራው ተከሳሽ ያልፈጸመው መሆኑን፣

ለ. ተከሳሹ የተከሰሰበት ክስ ቀላልና በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 28 መሰረት በራሱ ዋስትና ወይም በሌላ ሰው ዋስትና ሊያስለቅቀው የሚችል መሆኑን፣

ሐ. ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ከባድና ከፖሊስ የዋስትና ስልጣን በላይ መሆኑን፣

መ. ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 28 መሰረት በዋስ ሊያስለቅቀው ቢችልም ለማስረጃ ከሚደረገው ጥንቃቄ አኳያና ራሱም ተመልሶ ፍትሕ ፊት መቅረቡ አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል የሚሉ ናቸው፡፡

መርማሪው በፊደል “ሀ” እና “ለ” በተጠቀሱት መደምደሚያዎች ላይ ከደረሰ ተከሳሹን በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. በ3ኛ ሠንጠረዥ በ1ኛ ፎርም ላይ በተገለፀው መልክ የራስ ዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ሊለቀው ይችላል፡፡ በ3ኛ ሰንጠረዥ በ1ኛ ፎርም ላይ የተገለፀው ለአንድ አላማ የሚውሉ ሁሉ ፎርሞች ሲሆኑ 1ኛው ተጠርጣሪ ራሱ ግዴታውን ካላከበረ በዋስትና ወረቀቱ ላይ የተገለፀውን የተወሰነ ገንዘብ ገቢ ለማድረግ በራሱ ግዴታ የሚገባበት ሲሆን፣ ሌላው ሁለተኛው ሌላ ሰው ለተከሳሹ ግዴታ የሚገባበት ነው፡፡

ፖሊስ ተከሳሹን ወይም ተጠርጣሪውን ግዴታ የሚያስገባውና እንደነገሩ ሁኔታ ዋስም የሚያስጠራው ለሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው፡፡ 1ኛው ምርምራው ባለመጠናቀቁ ወይም ለተጨማሪ ምርመራ ተከሳሹን የሚፈልገው ከሆነ ለአንዴም ሆነ በተደጋጋሚ እንዲቀርብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ተከሳሹ ዋስ ከጠራ ወይም በራሱ ዋስትና ከተለቀቀ በኋላ በገባው ወይም በተገባለት ግዴታ መሰረት በፖሊስ መፈለጉን በምን ያውቀዋል? የሚል ነው፡፡ ሕጉ ይህንን አስመልክቶ የተለየ ፎርም አልደነገገም፡፡ ስለዚህ መርማሪው ግለሰቡ ወይም ዋሱ በሰጠው የቤት፣ የመስሪያ ቤት ወይም የስልክ አድራሻ ምቹ በመሰለው መልኩ ሊጠራው ይችላል፡፡ ግን ተከሳሹ ወይም ዋሱ የዋስትናውን ገንዘብ እንዲከፍል ከመጠየቁ በፊት በፖሊስ መፈለጉንና ለመቅረብ ፈቃደና ያለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 28 መሰረት የሚፈቀድ ዋስትናን አስመልክቶ ብዙ ጊዜ የሚነሳ ጥያቄ ተከሳሹ ግዴታውን አለማክበሩ ከተረጋገጠ የዋስትናውን ገንዘብ የሚከፍልበት ስርዓት ነው፡፡ መርማሪው ነው የሚያስከፍለው? ለፍርድ ቀርቦ ነው የሚከፍለው? ተከሶ ነው የሚከፍለው? የሚሉ ነጥቦች አጠያያቂዎች ናቸው፡፡ ለዋስትና የተባለው ገንዘብ በፖሊስ እጅ ተይዞ ከሆነ ተከሳሹ ወይም ዋሱ ግዴታውን ካላከበረ ገንዘቡን ለመንግስት ገቢ ማድረጉ አያስቸግርም፡፡ ገቢ ካልተደረገና የተፈረመ የገንዘብ ግዴታ ከሆነ ግን ዋስትና የፍትሐብሔር ኃላፊነት ስለሆነ የፍትሐብሔር ክርክር በሚመራበት መልኩ መመራት አለበት የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ መርማሪው ተከሳሽን ወይም ዋሱን ለዋስትና ገንዘብ ፍርድ ቤት የሚያቀርብበት ስርዓት ባይኖርም የፖሊስ መስሪያ ቤቶች በፍትሐብሔር ሕግ መሰረት ከመጠየቅ የሚያግዳቸው ነገር የለም፡፡

ፖሊስ በ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ አንቀፅ 28 መሰረት የያዘውን ተጠርጣሪ በዋስ ሊለቀው ይችላል፡፡ ይህን ለማድረግ ወንጀሉ በጽኑ እሥራት የማያስቀጣ ሊሆን ወይም ደግሞ ተጠርጣሪው ወንጀሉን ለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡፡ ፖሊስ በወንጀል ጠርጥሮ በመያዝ ለፍ/ቤት ያቀረበውን ተጠርጣሪ ፍ/ቤቱ በ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ አንቀፅ 59 (1) መሰረት በዋስትና ወረቀት ሊለቀው ይችላል ፡፡ ህጉ በግልፅ ፍ/ቤት የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ሊለቀው እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህን የሚያደርገው ተጠርጣሪው የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የማያስከለክለው፣ ምርመራ እየተካሄደበት ከሆነ መለቀቁ በማስረጃ ማሰባሰቡ ሂደት ላይ እንቅፋት የማይፈጥር፣ ቢለቀቅ ግዴታውን አክብሮ የሚቀርብ መሆኑን፣ መለቀቁ ለሕዝብ ፀጥታና ሠላም አስጊ አለመሆኑና ሌላ ወንጀል የማይፈጽም መሆኑን በማገናዘብ ሊሆን ይገባል፡፡

ከወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 28 አኳያ መርማሪው የተከሳሹን የዋስትና ጥያቄ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል በእርግጥ ተከሳሽ የተከሰሰበት ወንጀል ከባድ ወንጀል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ በመሰረቱ አንድን ወንጀል ፈፀመ የተባለ ሰው በየትኛው ሕግ አንቀጽ ሊከሰስ እንደሚችል የሚወስነውና ከስም የሚያቀርብበት ዐቃቤ ሕግ ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ራሱ እዚህ መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የሚችለው ማስረጃ ተሰብስቦ ምርመራ ተጣርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል ፖሊሶች ብዙውን ጊዜ በጣም ቀላልና ግልጽ ካልሆነ ሁኔታ በስተቀር ተጠርጣሪን ለመልቀቅ የማይደፍሩት፡፡

ተከሳሹን በራሱ ዋስትና ወይም በዋስትና ወረቀት ፖሊስ ከመልቀቁ በፊት ተከሳሹ በዋስትና ወረቀቱ ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች አይፈጽምም ካለ ወይም ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽማል ብሎ ካመነ ወይም ቢለቀቅ ማስረጃ ያጣፋል ወይም ይሰወራል ብሎ ካመነ ከበፊቱም ቢሆን ዋስትናውን ሊነፍገው ይችላል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተከሳሽን በዋስትና ወረቀት የመልቀቅ ሥልጣን ያለው አንዱ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ. ቁጥር 63 (1) በማንኛውም ደረጃ በክስ ላይ ያለ ግለሰብ ፍርድ ቤት በዋስ እንዲለቀው የመጠየቅ መብት አለው፡፡ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 64 (3) ማንኛውም ፍርድ ቤት በዋስትና ወረቀት ለመልቀቅ የሚቀርብን ማመልከቻ ሊቀበል

ይችላል፡፡ ማንኛውም ፍርድ ቤት የሚለው ሐረግ ግን የመደበኛ ፍ/ቤት መዋቅርን ለመግለጽ እንጂ ዋስትና ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ውጪ ሊቀርብ አይችልም፡፡

መልመጃ

ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ዓ.ም እና ከክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆች አንፃር በአሁኑ ጊዜ በአገራችን በወንጀል አይነት ላይ ተመስርተው የተቋቋሙ እኩል ስልጣን ያላቸው ሁለት ዓይነት ፍርድ ቤቶች ስላሉ ከዋስትና አንፃር ይህም ሁኔታ መታየት ያለበት እንዴት ነው? የዋስትና ማመልከቻ የክልል ፍ//ቤትን የሚመለከት ጉዳይ ፌዴራል ፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል ወይ? ወይም የፌዴራል ጉዳይ የፌዴራል ሥልጣን በሌለው ክልል ፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል ወይ? የክልል ወረዳ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ሥልጣን በሆኑ ጉዳዮች የዋስትና ጥያቄን ማስተናገድ ይችላሉ ወይ?

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የዋስትና ጥያቄ ፍርድ ቤት የሚቀርበው በሁለት መልኩ ነው፡፡ አንደኛው የተከሳሹ የዋስትና ጥያቄ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 28 መሰረት ቀርቦ በፖሊስ ተቀባይነት በማጣቱ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ተከሳሹ ተከሶ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ በጉዳዩ የፍርድ ቤት ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የሚቆይበትን ሁኔታ ለመወሰን ነው፡፡

ወንጀሉ ምንም ይሁን ምን አንድ ሰው በቁጥጥር ስር ውሎ ፖሊስ በተገቢው ጊዜ ካልለቀቀው የዋስትና ጥያቄ ለፍርድ ቤት ማቅረቡ አይቀርም፡፡ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 64 (1) በማንኛውም ጊዜ ቢሆን በተያዘው ሰው በዋስትና እንዲለቀቅ ለመጠየቅ ይችላል ቢልም ይህ ምናልባት ፖሊስ ግለሰቡን ፍርድ ቤት ለማቅረብ ካለው የ48 ሰዓት ጊዜ በፊት ሊሆን ይችላል ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 19 (3) እና በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 29 (1) መሰረት ተከሳሹ ከተያዘ ከ48 ሰዓት በፊት በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 28 መሰረት በዋስ ካልተለቀቀ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት ስላለውና መርማሪውም ተከሳሹን ፍርድ ቤት የማቅረብ ግዴታ ስላለበት የዋስትና ጥያቄውን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

የዋስትና ጥያቄው የቀረበለት ፍርድ ቤት የዋስትና መጠየቂያ ማመልከቻውን በሕጉ መሰረት ከተቀበለ በኋላ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 66 መሰረት ዐቃቤ ሕጉ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡ እርሱም ከሌለ ምርመራውን ያካሄደው ፖሊስ አስተያየት እንዲሰጥበት ይጠይቃል፡፡ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግን ወይም የፖሊስን አስተያየት ሳይጠይቅ ዋስትና ጠያቂውን በዋስ የሚለቅበት የሕግ ሁኔታ የለም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ዐቃቤ ሕጉ አስተያየት ተጠይቆ መልስ ስላልሰጠ ተጠያቂነቱን በርሱ ላይ ጥለን ተከሳሹን በዋስ ወይም ያለ ዋስ ለቀናል የሚል ውሳኔ በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች ሲሰጡ ይታያሉ፡፡

በዋስትና ለመለቀቅ በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ፍ/ቤት ቶሎ ውሣኔ መሰጠት እንዳለበት የሚደነግገው ደግሞ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 66 ነው፡፡ በዚህ ሕግ መሠረት ፍ/ቤቱ ማመልከቻው በደረሰው 48 ሰዓት ውስጥ ውሣኔ መስጠት ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን ከውሣኔው በፊት የዓ/ሕጉን ወይም የመርማሪውን ሃሳብና ትችት እንደሚጠይቅ ያስቀምጣል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ግን ይህ ሕግ ብዙ ጊዜ ሲተገበር አይታይም፡፡ በዋስትና ማመልከቻው ላይ ሃሳብ እንዲሰጥ የሚጠየቅ ዓ/ሕግ የምርመራ መዝገቡ በእጁ ስለሌለ የምርመራ መዝገቡን ከፖሊስ ወስጄና ተመልክቼ አስተያየቴን ለማቅረብ ጊዜ ያስፈልገኛል ይላል፡፡ ፍ/ቤቱም ማመልከቻውን ከዓ/ሕግ አስተያየትና ከምርመራ መዝገቡ ጋር መርምሮ በተሰጠው የ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ለመስጠት በተግባር ችግር አለ ይላል የዋስትና ጉዳዮችን ለብቻው የሚያዩ ችሎቶች ባለመኖራቸው ዳኞች የጊዜ ገደቡን አክብረው ውሣኔ ለመስጠት ሲቸገሩ ይታያል፡፡

የዋስትና መብት ጥያቄ መሠረታዊ ከመሆኑ አንፃር በሕጉ መሰረት ሊተገበር ይገባል፡፡ ክስ ለፍ/ቤት በቀረበበት ጉዳይ ከሆነ ዓ/ሕግ የምርመራ መዝገቡን አይቶ ክስ የሚያዘጋጅ እንደመሆኑ ከሕጉ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ ጉዳዩን የሚያራዝም የተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቅና ሊፈቀድለት የሚገባ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ውስብስብ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ዳኞችና ዓ/ሕጐች ፍትህ እንዳይጓደል በጥንቃቄ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ክስ በፍ/ቤት

ያልተመሠረተበት ጉዳይ ከሆነም መርማሪው ምርመራ መዝገቡ በእጁ ያለ/ የነበረ እንደመሆኑ ወዲያውኑ አስተያየቱን ለመስጠት ይቸገራል ሊባል አይችልም፡፡ ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ የዋስትና ማመልከቻ ከሌሎች ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ በአጭር ጊዜ እንዲወስኑ ሕግ የሚጠይቅ በመሆኑ ቅድሚያ ሰጥተው ሊወስኑ ይገባል፡፡

ፍርድ ቤቱ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 63 (1) በሚቀርብ የዋስትና ጥያቄ ወንጀሉ በሕጉ መሰረት ዋስትናን የሚያስከለክል ነው ወይስ አይደለም ብሎ ለመወሰን በዐቃቤ ሕግ የሚቀርበውን ክስ የግድ ማየት ይኖርበታል ወይ የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ነው፡፡ የተወሰኑ ወገኖች ሕጉ “የተያዘ ሰው የተከሰሰበት ወንጀል” ስለሚል ፍርድ ቤቱ የግድ የዐቃቤ ሕግን ክስ ማየት አለበት ሲሉ ሌሎቹ ግን ዐቃቤ ሕግ አመልካቹ ሊከሰስ የሚችልበትን አንቀጽ ብቻ ማመልከቱ በቂ ነው ይላሉ፡፡ የመጀመሪያው አመለካከት ከተቻለ ጥሩ ነው የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 66 ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄን በአፋጣኝ ማየት እንዳለበት ሲደነግግ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 19 (3) ላይ ማንኛውም የተያዘ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አንድን በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ቶሎ ለመክሰስ የሚያግዱ እንደ ወንጀሉ ውስብስብነት የማስረጃ ቶሎ ያለማሰባሰብ፣ በምርምራ ማጣራት ላይ የሚደርሱ ጉድለቶችን ለማስተካከል የሚወሰደው ጊዜ ክስን በአፋጣኝ ለመመስረት የማያስችሉ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙት ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የምርመራ መዛግብቱ እንኳን ተመዝችተው ቢቀርቡለት በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 109 መሰረት ክስ ለማቅረብ ከተሰጠው ከ15 ቀናት በፊት ክስ ካላቀረብክ ማለት በሕግ ለዐቃቤ ሕግ የተሰጠውን መብት ከመቃረኑ ትክክል አይመስልም፡፡

5.3 ዋስ የመሆን ብቃት

ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.አንቀፅ 28 እና 63 (1) በዋስትና እንዲለቀቅ በፖሊስ ወይም በፍርድ ቤት ለተፈቀደለት ሰው ለዋስትናው ብቁ እስከሆነ ድረስ ዋስ ሊሆን ይችላል፡፡ ተከሳሹ ራሱ በራሱ ዋስትና ሊቆይ የሚችልበት ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ተከሳሹ በራሱ ዋስትና ወይም በሌላ ሰው ዋስትና እንዲለቀቅ ለዋስትናው ብቁ መሆን ግን አስፈላጊ ነው፡፡

አንድ ሰው ለዋስትና ብቁ መሆኑን የሚወስነው የዋስትና ጥያቄው የቀረበለት ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ለመወሰን ግምት ውስጥ ሊያስገባቸው ከሚያስፈልጉት ነገሮች ዋሱ ለዋስትና ግዴታ የገባበትን ገንዘብ ለመክፈል መቻሉ፣ የራሱ የዋሱ ባሕርይ፣ ተከሳሹን ተከታትሎ ለማቅረብ መቻሉ እና የተከሳሹ ታማኝነት ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ናቸው፡፡

የዋሱ ግዴታ መለኪያዎች ከሆኑት አንድ በዋስትና ወረቀቱ ግዴታ የገባበትን የገንዘብ ልክ መክፈል መቻል ያለመቻሉ ነው፡፡ ይህ በአንፃሩ የሚወሰነው በወር ወይም በአመት በሚያገኘው ገቢ ይህ ሊታወቅ የማይችል ከሆነ ባለው ቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ ንብረት ልክ ነው፡፡

ይህ የሆነበት ምክንያት ምንም እንኳ የዋሱ ዋና ግዴታ ተከሳሹ በፖሊስ ወይም በፍርድ ቤት ለአንድ ጊዜም ሆነ በተከታታይ ሲፈለግ ስለመቅረቡ ሲሆን፣ ካልቻለ በዋስትና ወረቀቱ ላይ የገባውን ግዴታ ለመወጣት ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ዋሱ ቢያንስ ለዋስትና ግዴታ ለመወጣት ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ዋሱ ቢያንስ ለዋስትና ግዴታ የገባበትን ጥሬ ገንዘብ እንዲያስይዝ ባይገደድም ለሀብቱ ማረጋገጫ ማቅረብና የዋስትና ግዴታውን በፍርድ ቤት ወይም በዋሱ አመልካችነት እስካወረደ ድረስ ተከብሮ እንዲቆይ መደረጉን ፍ/ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡ በወር በሚገኝ ገቢ የሚተዳደር ዋስም ከሆነ ገቢው ከተገቢው ዋስትና ጋር ሊመጣጠን የሚችልና ከተፈለገ ግዴታውን ሊወጣ የሚያስችለው መሆን ይኖርበታል፡፡

ዋስ ለመሆን ለዋስትናው የሚመጥን በቂ ገቢ መኖር ብቻውን የሚቆም አይደለም፡፡ የዋሱም ባሕርይ ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡ በተለምዶ አሰራር ዋሱ ራሱ በከባድ ወንጀል የተከሰሰ፣ በአጭበርባሪነት የሚታወቅ መሆን የሌለበትና ቋሚ መኖሪያና የሥራ ቦታ ሊኖው የሚገባ ሲሆን የአገሪቱ ዜጋ መሆኑ ወይም በአገሪቱ በቋሚነት የሚኖርና ታማኝ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

5.4 የዋስትናው ገንዘብ ልክ መወሰኛ መስፈርቶች

የዋስትና ልክ የሚለካው በገንዘብ መጠን ቢሆንም በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.አንቀፅ 69 መሰረት ፍርድ ቤቱ የዋስትናውን ገንዘብ ልክ የሚወስነው በመሰለው ነው፡፡ ይህ ሲወሰን ግን የወንጀሉን ክብደት፣ የተከሳሹን ባሕርይ፣ የተከሳሹና የዋሱ ሀብት መጠን መመዘን እንደሚገባው ነው፡፡ ይህ ማለት ወንጀሉ ከባድ (ዋስትናን የማያስከለክል) ከሆነ፣ የተከሳሹ የሥራ፣ የኑሮና የባሕርይ ሁኔታ በግልጽ የማይታወቅ ከሆነና ዳኛው ተከሳሹ በዚህ ምክንያት ዋስትና ሊከለከል አይገባውም ብሎ ካመነ በአንፃሩ የዋስትና ገንዘቡን ከበድ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ፍረድ ቤት ዋስትናን ሲወስን በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 69(2) የተዘረዘሩትን ምክነያቶች መመልከት አለበት፡፡ በዚህ አንቀፅ (መ) አንድተገለፀው ፍረድ ቤቱ የተከሳሹን ወይንም የዋሱን የሀብት መጠን ግምት ዉስጥ ማስገባት አለበት፡፡ምክንያቱም የገንዘቡ መጠን ከአቅም በላይ ከሆን ውጤቱ ዋስትናን መከልከል ነው የሚሆነው፡፡ እንደ አሜሪካ በመሳሰሉት ሀገሮች ከፍተኛ የዋስትና መጠን (excessive bail) ክልክል ነው፡፡ በእኛም ህግ የወ/መ/ስ/ስ/ህገ ቁጥር 69(2)(መ) ድንጋጌ የሽንን ሀሳብ የያዘ ይመስላል፡፡ በአንዳንድ ብይኖች ወንጀሉና ለዋስትና የሚያዘው ገንዘብ ተመጣጣኝነት የለውም፡፡ በአብዛኛው ቀለል ላለ ወንጀልም ቢሆን የዋስትናው ገንዘብ ከበድ የሚልበት ሁኔታዎች አሉ፡፡

የዋስትና ግዴታ ገንዘብ ሲታሰብ ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይኸውም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀፅ 20 (3) የተከበረውን ከፍርድ በፊት ነፃ ሆኖ የመታየት መብት እና አንድ ወንጀል በመፈፀም የተጠረጠረ ሰው ትክክለኛ ፍርዱን የማግኘት ሁኔታ ጎን ለጎን መታየት አለባቸው፡፡

መልመጃ

1. በአንድ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በመሰረተው የኮነትሮባንድ ክስ፡፡ ግምታቸው ለአንዱ 600 ብር የሆኑ 34 የሞባይል ቀፎዎች ይዞ የተገኘ ተጠርጣሪ ያቀረበው የዋስትና ጥያቄ ይመለከት የነበረው ፍርድ ቤት የ300 መቶ ሺ ብር ዋስትና እንዲያቀርብ ካላቀረበ ጉዳዩ ማረምያ ቤት ሆኖ እንዲ ከታተል አዘዘ፡፡ ፍትሃዊነቱ እንዴት ይመለከቱታል?

2. ለቀላል ወንጀል የዋስትናው ገንዘብ ከባድ በሚሆንበት ጊዜ ተከሳሹ ግዴታውን አክብሮ ከመቅረቡም በተጨማሪ ወንጀል እንዳይበረታታ ያደርጋል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እርሶስ?

5.5 የዋሱ ኃላፊነት ወሰን

በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀፅ 70 (1) መሰረት ዋነኛው የዋሱ ግዴታ የክሱ መታየት ሥነ ሥርዓት ተጀምሮ የክሱ መሰማት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚቋረጥም ቢሆን በማንኛውም ጊዜና ቦታ በቀጠሮው ቀን በርሱ ዋስትና የተለቀቀውን ተከሳሽ ፍርድ ቤት ማቅረብ ነው፡፡ ተከሳሹ ግዴታውን አክብሮ ፍርድ ቤት እስከቀረበ ድረስ ፍ/ቤቱ ዋሱን የሚፈልግበት ሁኔታ የለም፡፡ የዋሱ ግዴታውን የማክበር ጥያቄ የሚነሳው ተከሳሽ በመጀመሪያ ወይም በተከታታይ ቀጠሮዎች ከፍርድ ቤት ሲቀር ወይም ከመቅረብ ሲያቋርጥ ነው፡፡ ስለዚህ ዋሱ የዋስትና ግዴታውን ለማቃለል ተከሳሽ በየጊዜው ፍርድ ቤት መቅረቡን መከታተሉ ይጠቅመዋል፡፡

ተከሳሹ ግዴታውን ካላከበረ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀፅ 76 (2) መሰረት ዐቃቤ ሕጉ በሚያቀርበው ማሳሰቢያ ዋሶቹ ፍርድ ቤት ተጠርተው ቀርበው ሊከፍሉ የገቡትን ግዴታ እንዲያስገቡ፣ በቂ ምክንያትም ካላቸው ለምን እንደማያስገቡ ይጠየቁ ዘንድ ለፍርድ ቤት ማመልከት ነው፡፡ ዋሶቹ ፍርድ ቤት ቀርበው የዋስትና ገንዘቡን ላለማስገባት የማያስችላቸውን በቂ ምክንያት ካለ ለፍርድ ቤት ማስረዳት ነው፡፡ ሊያቀርቡት የሚገባው ምክንያት ተከሳሹን በሚመለከት እንጂ የራሳቸውን አይደለም፡፡ ተከሳሹ ከራሱ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ፍርድ ቤት ያለመቅረብ መቻሉን ማስረዳት አለባቸው፡፡ ለምሳሌም ተከሳሹ በሕመም ምክንያት፣ በትራንስፖርት እጦት፣ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች መቅረቱን ማስረዳት ከቻሉ ፍርድ ቤቱ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 70 (3) መሰረት በተከታዩ ቀጠሮ የመሰለውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተከሳሹ ሞቶ ከሆነ በሚያቀርበው ማስረጃ መሰረት ክሱ የሚቋረጥ ሲሆን፣ ዋሱም ራሱ ከሞተ ዋስትናው ቀሪ ሆኖ ማያገኟቸው ለሕጋዊ ወራሾቹ ይመለሳሉ፡፡ ተከሳሹ ተደብቆ ወይም ለመቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ከሆነ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 70 (1) ላይ በተደነገገው መሰረት ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ተፈልጎ እንዲያዝ ዋሱም በግዴታ የገባበትን ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርግ ያዛል፡፡

የዋሱ ግዴታዎች የሚቋረጡት በዋስትና ወረቀቱ ላይ የተጠቀሰው ጊዜ ሲያበቃ፣ ክሱ ውሳኔ ሲያገኝ፣ ዋሱ ሲሞት፣ ዋሱ ዋስትናው ይውረድልኝ ብሎ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ሲያገኝ (የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 77 እና 78)፣ ፍርድ ቤቱ ዋስትናው በቂ አይደለም ብሎ ሲያምንና ክሱ ሲነሳ (ቁጥር 71/3) ዋሱ ከግዴታው ነፃ ሊሆን ይችላል፡፡

መልመጃ

አቶ "ሀ" የአንድ የግል ድርጅት ሰራተኛ ናቸው፡፡ አቶ "ሀ" ከመስሪያ ቤታቸው የደመወዝ መጠን በመግለፅ አቶ "ለ"ን በዋስትና ከእስር እንዲለቀቁ አደረጉ፡፡ አቶ "ለ" ከተፈቱ ሁለት ሳምንታት በኋላ አቶ "ሀ" ይሰሩበት ከነበረው መስሪያ ቤት ለቀቁ፡፡ በቀጣዩ የፍርድ ቤት ቀጠሮ አቶ "ሀ"ና አቶ "ለ" ግዴታቸውን አክብረው ሳይቀርቡ ቀሩ፡፡

ሀ- እንደዚህ አይነት ሁኔታ ገጥሟችሁ ያውቃል? ካልገጠማች ቢገጥማችሁ ታሳቢ አድርጉና ተጠያቂው ማን ሊሆን እንደሚችል ተወያዩበት፡፡

ለ. የመስሪያ ቤት የዋስትናና ደመወዝ መግለጫ ደብዳቤ አስይዞ ዋስ እንዲሆን ማድረግ ያሉት ክፍተቶች ምንድን ናቸው? ለክፍቶቶቹ የጥንቃቄ እርምጃ ይኖር ይሆን?

5.6 የዋስትና መብት የሚያስገኙና የማያስገኙ ወንጀሎች

በወንጀል ተጠርጥረው በተያዙ ሰዎች የሚቀርቡ የዋስትና ጥያቄዎች ላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሚሰጡበት ወቅት ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮች በወንጀል ሥነ ሥርዓት እና በሌሎች ተዛማጅ ህጎች ውስጥ በግልጽ ተዘርዝረው የሚገኙ እና ከፊለቹ የህግ ከፊሎቹ ደግሞ የፍሬ ነገር ግንዛቤ የሚወሰድባቸው መሰረታዊ መርሆዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል የዋስትና ጥያቄ የቀረበበት የወንጀል ጉዳይ ከባድነት፣ የተጠርጣሪው ያለፊ የወንጀል ሪከርድ እና የግል ፀባይ፣ በዋስትና ጥያቄው ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በሕዝብ ጥቅም ሊይ የሚኖረው ተፅዕኖ፣ ተጠርጣሪው በዋስትና ቢለቀቅ በተፈለገ ጊዜ ፌርድ ቤት ተመልሶ ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑ ወይም ሌላ ወንጀል ሊፈጽም የሚችል ስለመሆኑ ወይም ምስክሮችን በማስፈራራትና ማስረጃን በማጥፋት በፍትሕ አሰጣጡ ላይ እክል ሊፈጥር የሚችል ስለመሆኑ እና የመሳሰለት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአለም አቀፍ ሕጎችም ሆነ በአብዛኛው አገሮች የወንጀል ሕጎች፣ ዋስትና ለማንኛውም በወንጀል ለተጠረጠረ ሰው ፍፁማዊ (absolute) መብት አይደለም፡፡ ከዋስትና መብት አንፃር ወንጀሎች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፣ ዋስትና የሚያሰጡና ዋስትና የማያሰጡ ወንጀሎች ተብለው ነው፡፡ ለፍርድ የመቅረብ ተአማኒነት የለውም ብሎ ፍርድ ቤት ካመነ ዋስትናን የሚከለክልበት ሁኔታ አለ፡፡ በአብዛኛው አገሮች ዋስትናን የሚያስከለክሉ ወንጀሎች ከባድ ወንጀሎች የተባለ ሲሆኑ በተለይም የግድያ ወንጀል እንደዋና ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ ወይም የተፈፀመው ወንጀል በአገሩ ሕግ መሰረት የሞት ቅጣትን ሊያስከትል የሚችል ከሆነም ነው፡፡

በአሜሪካና በእንግሊዝ ሕግጋት መሰረት ዋስትናን ለማስከልከል ወንጀሎቹ ከፍተኛ ወይም ከባድ ወንጀሎች መሆን አለባቸው፡፡ በተለይ ከአሜሪካ ሕግ የሞት ቅጣትን የሚያስከትል ወንጀል የዋስትና መብትን ያስከለክላል፡፡ በ1788 የወጣው የፌዴራሉ ሕግ ምናልባት ወንጀሉ የሞት ቅጣትን የሚያስወስን ካልሆነ በስተቀር ዋስትና አይከለክልም ይላል፡፡ የ1966 (እ.ኤ.አ) የፌደራሉ ሕግ ግን ዳኞች ተከሳሹ ሌላ ወንጀል ይፈጽማል ወይም በሕብረተሰቡ ውስጥ ተጠርጣሪው ቢለቀቅ አደጋን ያስከትላል ብለው ካመኑ ዋስትናን ከልክለው አስርን ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡ ይህም የሽብር ወንጀልን፣ አደገኛ ዕፅ የማዘዋወርና የመሳሰሉት ወንጀሎችን በተመለከተ ነው፡፡

በኢትዮጲያ ዋስትና በመርህ ደረጃ የተፈቀደ ነው፡፡ ህገ-መንግስታዊ መሰረት ያለው መርህ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሕግ የዋስትና አሰጣጥ ስርዓት ወንጀሎች ዋስትና የሚያሰጡ እና ዋስትና የማያሰጡ ወንሎች ተብለው ይከፋፈላሉ፡፡ ዋስትና በማያሰጡ ወንጀሎች ፍርድ ቤት ዋስትና የመስጠት መብት የለውም፡፡ ዋስትና ያሰጣሉ በተባሉ ወንጀሎችም ቢሆን ፍ/ቤቱ ዋስትናውን ከመስጠቱ በፊት ዐቃቤ ሕጉ የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 66 መሰረት የሰጠውን አስተያየት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ ይህ አስተያየት በቁጥር 67 ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመፍቀድም ሆነ ላለመፍቀድ ይህንን አስተያየት መነሻ አድርጎ መሆን አለበት፡፡

ዋስትና የማይፈቀ-ድባቸውን ወንጀሎች በልዩ ሁኔታ በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ተግባራዊ ሊሆኖ ይችላሉ፡፡ የመጀመርያው በህግ የተደረገ ክልከላ ሲሆን፣ የህግ ግንዛቤ

በመውሰድና ዋስትና የሚከለክለ ድንጋጌዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው የክልከላ ዓይነት በፍርድ ቤቶች የሚደረግና በፍሬ-ነገር ላይ የተመሰረተ ክልከላ ነው፡፡

5.6.1 በህግ የሚደረግ ክልከላ

በህግ የሚደረግ ክልከላ የህገ- መንግስቱ አንቀፅ 19 (6) መሰረት ያደረጉ መሰረታዊ ገደቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ገደቦች ወይም ክልከላዎች ተግባራዊ የሚሆኑት ህጎቹ በግልፅ በአዋጅ የተደነገጉና ፀንተው የህግ ግንዛቤ የሚወሰድባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ፍፁማዊ ክልካይ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ የሚከተሉት ህጎች በዋስትና መብት ላይ ክልከላ የሚያስከትሉ ከመሆናቸው አንፃር እንደሚከተለው እንመልከታቸው፡፡

5.6.1.1. በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ መሰረት የተደረገ ክልከላ

ለጊዜውም ሆነ ለዘለቄታው ዋስትና የሚያስከለክሉ ወንጀሎች በጽኑ እስራት ወይም የተያዘው ሰው የተከሰሰበት ወንጀል የሞት ቅጣትን ወይም 15 ዓመት ወይም በላይ የሆኑ ጽኑ እስራትን የሚያስቀጣ ከሆነና ወንጀል የተፈጸመበት ሰው በደረሰበት ጉዳት የሚሞት ከሆነ ፖሊስም ሆነ ፍርድ ቤት ተከሳሹን በዋስትና ወረቀት ሊለቀው አይችልም፡፡ ለዚህም የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ አንቀፅ 63 (1) መሰረታዊ ክልከላ ይዟል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 63 ለትርጉም አሻሚ ስለሆነና አንዳንድ በተጨባጭ ዋስትና ሊያስከለክሉ የሚችሉ እንደ ከባድ ዝርፊያ ወይም ውንብድና (የወ.ሕ. አንቀጽ 671) እና በቸልተኝነት ሰው መግደል (የወ.ሕ. አንቀጽ 543 (3)) በግልጽ በሚሸፍን መልኩ ስላልተደነገገ በሕግ ሰዎች ዘንድ አጨቃጫቂ ነው፡፡ አንድ ሰው የተጠረጠረበት ወንጀል ከ15 ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ ወይም የሞት ቅጣትን የሚያስከትል ከሆነ ፍርድ ቤት ግለሰቡን በዋስ ለመልቀቅ ስልጣን አይኖረውም፡፡ በአንድ ባልታተመ ጽሑፍ በአንቀጽ 63 ትርጉም ሲገለጽ ዋስትና የሚከለከለው፣

1. ወንጀሉ 15 ዓመት በጽኑ እስራት የሚያስቀጣና ተበዳዩ የሚሞት ከሆነ
2. ወንጀሉ ከ15 ዓመት **በላይ** ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆንና ተበዳዩ የሚሞት ከሆነ

3. ወንጀሉ በሞት የሚያስቀጣ ሲሆንና ተበዳዩ **የሚሞት** ከሆነ
4. ወንጀሉ በ15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣና ተበዳዩ **የሞተ** ከሆነ
5. ወንጀሉ ከ15 ዓመት ጽኑ እስራት **በላይ** የሚያስቀጣ ከሆነና ተበዳዩ የሞተ ከሆነ
6. ወንጀሉ በሞት የሚያስቀጣና ተበዳዩ **የሞተ** ከሆነ ነው ዋስትና የሚከለከለው በማለት አስፍሮአል፡፡

አንቀጹ በቀጥታ ሲነበብ አንድ ሰው በሕግ ዋስትናን ለመከልከል ሁለት ጣምራ መስፈርቶች ማሟላት ያለባቸው ይመስላል፡፡ ይኸውም፣ የተበዳዩ መሞት ወይም በሞት አፋፍ መገኘት እና የወንጀሉ 15 ዓመት ጽኑ እስራት ወይም ከ15 ዓመታት ጽኑ እስራት በላይ ማሳሰር ናቸው፡፡ ከዚህም አኳያ የአንድ ተበዳይ መሞት ብቻ የዋስትና መብት ጠያቂውን ዋስትና አያስነፍገውም፡፡ ገዳዩን 15 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ሊያስቀጣው እስካልቻለ ድረስ ዋስትናን አያስከለክልም ወደሚል ሃሳብ ይወስዳል፡፡ ለዚህም ሊጠቀስ የሚችለው በወ.መ.ሕ አንቀፅ 543 (1)ና(2)፣ ስር የተጠቀሰው በቸልተኝነት ሰውን መግደል እና 541 መተላለፍን ነው፡፡ በወ.መ.ሕ ቁጥር 540 የተጠቀሰው ተራ የሆነ አገዳደልንም በተመለከተ በድርጊቱ ግድያ ቢፈፀምም ቅጣቱ የሚጀምረው ከ5 ዓመት ስለሆነ ተከሳሹ በሕግ ተከሶ ቢፈረድበትም (በተለይ ማክበጃ ምክንያት ከሌለ) ከ15 ዓመት በላይ ይቀጣል የሚል መደምደሚያ ላይ አያደርስም፡፡ ከዚህ አኳያ የአንቀጽ 63 (1) ዋና ችግር የሚመነጨው የአንቀጹ አቀራረጽ ዋስትና የሚከለክልበትን ሁኔታ በጠባቡ እንድናየው ከማድረጉም ሌላ አንድ የግድያ ወንጀል አስራ አምስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሚያሳስር መሆኑን ለዋስትና ጉዳይ ለመወሰን ማስረጃንም ወደ ማየት የሚገፋፋ በመሆኑ ነው፡፡ ብዙ ግዜ የዓቃቤ ህግ ሲሻሻል ወይም ፍርድ ቤቶች በብይን አንቀፁ በሚቀይሩበት ጊዜ የዋስትና ጉዳይ እንደአዲስ ሲነሳ ይስተዋላል፡፡ የዚህ ትርጉምና የአመለካከት ችግር የአንቀጽ 63 (1) በአለታዊ መልክ መፃፍ ሲሆን የሕጉ በዋስትና ረገድ የከባድ ወንሎችንና የቀላል ወንጀሎችን ሁኔታ አለመለየት ነው፡፡

ሆኖም ግን ይህንን በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ ቁጥር 66 ዐቃቤ ሕጉ በዋስትናው በሚሰጠው አስተያየትና በፍርድ ቤቶች አቋም መካከል ልዩነት ይስተዋላል፡፡

ይኸውም ዐቃቤ ሕጉ ፍርድ ቤት ዋስትናን ሲወስን መከተል ያለበት በአንቀጹ የተጠቀሰውን ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ መሆን አለበት ሲል በዚህ አቋም ግን ብዙ ፍርድ ቤቶች አይስማሙም፡፡ ይህም ማለት ከፍሬ ጉዳይና ከማስረጃም አኳያ ቢሆን በዚህ ደረጃ ዐቃቤ ሕግ በፖሊስ ምርመራ በመዝገቡ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው ማስረጃ በአጠቃላይ የተሟለ ናቸው ተብሎ ስለማይገመት የዋስትና ውሳኔም ከፍርድ በፊት ያለ ውሳኔ እንጂ በማስረጃና በመከላከያ ነጥሮ ያልተወሰነ በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ እጅ ያለው ቀዳሚ ማስረጃ (primary evidence) ዐቃቤ ሕጉን ተከሳሽ ሊከሰስበት የሚችለውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ ሊለይ የሚያስችለው ከሆነ ፍርድ ቤቱ ይህንን ቢከተል መልካም ነው የሚሉ ወገኖችም ይስተዋላሉ፡፡

ይህ ማለት ከዚህ ውጪ ያሉ ወንጀሎች በሙሉ የዋስ መብት ያስፈቅዳሉ ማለት አይደለም፡፡ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 63 (1) ሥር የተጠቀሰው የሞት ወይም ለመሞት መቃረብ ሁኔታና ወንጀሉ 15 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የማያስቀጣ ከሆነ ፍርድ ቤት የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ማመልከቻ አቅራቢውን ሊለቀው ይችላል ይላል፡፡ በዚህ አነጋገር ፍርድ ቤት ላይለቀውም ይችላል ማለት ነው፡፡ በመሰረቱ ከዚህ በላይ የተነገረው ካልተከሰተ ግለሰቡ በዋስትና ላለመለቀቅ አስተዋጽኦ ካላደረገ በስተቀር ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ይፈቅዳል የሚል እምነት አለ፡፡ በአጠቃላይ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀጽ 63 (1) መሰረት የተፈፀመው ወንጀል ግድያ ከሆነ ወይም ወንጀል የተፈፀመበት ሰው የሚሞት ከሆነ እና ወንጀሉ አስራ አምስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ፍርድ ቤት አመልካቹን በዋስ የመልቀቅ ሥልጣን የለውም፡፡

5.6.1.2 የአደገኛ ቦዘኔ መቆጣጠርያ አዋጅ

በአደገኛ ቦዘኔነት የተጠረጠረ ሰው የዋስትና መብት አይከበርለትም፡፡ ቢጠይቅም አይፈቀድለትም፡፡ የአደገኛ ቦዘኔ መቆጣጠርያ አዋጅ ቁጥር 384/ 1994 አንቀፅ 6(3) መሰረት በአደገኛ ቦዘኔ የተጠረጠረ ሰው በዋስትና መለቀቅ እንደሌለበት ህጉ በግልፅ ደንግጓል፡፡

5.6.1.3 የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ ስነ-ስርአትና የማስረጃ ህግ

ይህ ህግ ሙሉ-በሙሉ ከልካይ ሳይሆን በቅድመ ሁኔታ የተመሰረተ ክልከላ ደንግጓል። የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ ስነ-ስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/ 1997 አንቀፅ 4 (1) ሁለት የተለያዩ ፅንሰ-ሃሳቦች በአንድነት አካቶ ይዟል። በዚህ አንቀፅ መሰረት በሙስና የተጠረጠረ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍርድ ቤት ማመልከት እንደሚችል ቢገልፅም ይህ አንቀፅ ራሱ የተጠረጠረበት ወንጀል ከ አስር አመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ፍርድ ቤቶች በዋስትና መልቀቅ እንደማይችሉ በግልጽ አስቀምጧል።

5.6.1.4 የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ

በሽብርተኝነት የተጠረጠረ ሰው የዋስትና መብት አይከበርለትም። ቢጠይቅም አይፈቀድለትም። ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ አዋጅ ቁጥር 652/2001 በአንቀፅ 20 (5) በግልፅ እንዳስቀመጠው በሽብርተኝነት የተጠረጠረ ሰው ክስ የቀረበበት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ክሱ ሰምቶ ውሳኔ እስኪ ሰጥ ድረስ ተከሳሽ በማረፍያ ቤት እንዲቆይ ማድረግ እንዳለበት በግልፅ ደንግጓል። በዚህ አንቀፅ 20 (1) እና (4) በጣምራ በማንበብ በምርመራ ሂደት ባለ ጉዳይ ዋስትና ሊፈቀድ ይችላል የሚል ተቃራኒ ሃሳብ መኖሩ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

እነዚህ ግልፅ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ናቸው። የህብረተሰቡ ሰላም፣ ደህንነት፣ ነፃነት ከማስጠበቅና አደጋን ከመከላከል አኳያ የተደነገጉ ድንጋጌዎች መሆናቸው ከአዋጆቹ አላማ፣ የመግቢያቸው ይዘትና የመወያያ ሃሳቦቻቸው መረዳት ይቻላል። ፍርድቤቶችም የህግ ግንዛቤ ወስደው ክልከላውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይጠበቃል።

5.6.2 በፍርድ ቤቶች የሚደረግ ክልከላ

በፍርድቤቶች የሚደረግ የዋስትና መብት ክልከላ ከፍሬ-ነገር የሚመነጭ ሲሆን፤ ፈቃጅ በሆነ ህግ ነገር ግን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ የሚከለከልበት አግባብ ነው። በዋስትና ወረቀት ላለመለቀቅ የተከሳሽ ሁኔታ የሚባለውም በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 67 የተገለፀው ነው። ይኸውም ግለሰቡ በዋስትናው ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች የሚፈጽም የማይመስል ከሆነ ወይም አመልካቹ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ

የሚገመት ሲሆን፣ ምስክሮች በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጂ የሚሆንበትን ያጠፋል ተብሎ የሚገመት ሲሆን ነው።።

እነዚህ መስፈርቶች በተናጠልም ሆነ በጥቅል የሚሟሉ ከሆነ አመልካቹን በዋስትና ላለመልቀቅ በቂ ምክንያቶች ናቸው።። ዳኞች የዋስትናውን ጉዳይ በሚያዩበት ወቅት አመልካቹን በዋስትና ወረቀት ለመልቀቅም ሆነ ላለመልቀቅ በግምት ውስጥ ከሚያስገቡት ነገሮች ስለወንጀሉና ስለወንጀል አፈፃፀሙ ያለውን ግርድፍ መረጃ፣ የቀረበውን የማስረጃ ሚዛን፣ የተከሳሹን የቤተሰብ ሁኔታ፣ የሥራ ሁኔታውን፣ የገቢ አቋምና ምንጩን፣ ፀባዩንና የአእምሮውን ሁኔታ፣ በአካባቢው የኅብረተሰቡ ውስጥ የቆየበትን ጊዜ ርቀት፣ ከዚያ በፊት ለምን ያህል ጊዜ እንደተከሰሰና ፍርድ ቤት እንደቀረበ፣ የፍርድ ቤት ቀጠሮ አክባሪነቱን ይመለከታሉ።። እነዚህ ነጥቦች ከሞላ ጎደል በአለታ የሚመለሱ ከሆነ ዋስትናው ሊከለከል ይችላል።።

በአገራችን የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 67 ዋስትናን ለመከልከል ከፊደል “ሀ” እስከ “ሐ” የተጠቀሱት “የማይመስል” “የሚገመት” “የሚገመት ሲሆን” የሚሉት ቃላት በአንቀጹ ውስጥ ተጠቅሰዋል።። ዳኛው የዋስትና ጥያቄውን ለመከልከል በምናልባትና በይሆናል ላይ ተመስርቶ ከመሰለው የዋስትና ጥያቄውን መከልከል እንዳለበት ተገልጿል።። አብዛኛውን ጊዜ ዳኞች በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 66 ሥር ዐቃቤ ሕግ ለሚያቀርበው ተቃውሞ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይጠይቃሉ።። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች መጤን አለባቸው።። አንደኛ ዳኞች ዋስትናን ለመከልከል ሕጉን በጠባቡ መተርጎሙ አግባብ ቢመስልም ሕጉ በዐቃቤ ሕጉ ላይ ያልጣለውን የማስረዳት ሸክም ግን እንዲወጣ ማድረጉ በአግባቡ አይመስልም የሚሉ ወገኖች ሲኖሩ።። በተቃራኒው የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 67 ህገ-መንግስቱ ከመውጣቱ በፊት የነበረ፣ ከህገ-መንግስቱ የዋስትና መርህ ጋር አብሮ የማይሄድ ከመሆኑም በላይ ሰብአዊ መብቶች በማክበርና ማስከበር ካላቸው ከፍተኛ ሃላፊነት አንፃር ህጉ በጠባቡ በመተርጎም አቃቤ ህጉም ዋስትና ለማስከልከል ባነሳባቸው ፍሬ-ነገሮች ትይዩ የማስረዳት ሸክም አለበት የሚሉ ወገኖች አሉ።።

ይህም ማለት አመልካቹ በዋስ ይለቀቅ ወይም አይለቀቅ የሚለውን ለመወሰን ዳኛው ይረዳው ዘንድ ግልጽ የወንጀል ሪኮርድ በቅርብ የሚቀርብ ከሆነ መጠቀሙ በአግባቡ ነው።።

ምንም እንኳ ከወ/መ/ስ/ስ/ህ/ አንቀፅ 138 ተያይዞ የሚነሳ ሃሳብ ቢኖርም በአንዳንድ ፍርድ ቤት በሚቀርቡ ጉዳዮች ዋስትና ጠያቂዎቹ ለጠየቁት ዋስትና ዐቃቤ ሕግ የሚቀርበው ተቃውሞ ባለሁለት ፈርጅ ነው፡፡ በተለይም ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን መሰረት ያደረጉ ወንጀሎች ከሆኑ 1ኛው) ግለሰቦቹ በከባድ አንቀፅ የተከሰሱ ስለሆነና ምናልባት ቢፈረድባቸው እስከ 15 ዓመት ሊሆን ስለሚችል፣ 2ኛ) ግለሰቦቹ የተያዙት በጦርነትና በተኩስ ስለሆነና በመከላከያ ሠራዊትም ተማርከው ስለሆነ በዋስ ቢለቀቁ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ አንቀጽ 67 (1 እና 2) መሰረት ሌላ ወንጀል ይፈጽማሉ ወይም ግዴታቸውን አክብረው ተመልሰው ፍርድ ቤት አይቀርቡም በማለት ተቃውሞ ቀርቧል፡፡ ከወንጀሉ ክብደትና ከሚጠብቀው የቅጣት ክብደት አንፃር የዋስትና ግዴታውን አለማክበሩ የሚገመት (presumed) ስለሚሆን ዋስትናን ለመከልከል ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ያስፈልጋል መባሉን ብቻ በቂ ነው፡፡ የማረጋገጫ ማስረጃ መመልከት አያስፈልግም፤ ዐቃቤ ሕጉ በዚህ ጉዳይ ማስረጃ የሚጠየቅማ ከሆነ በሕጉ የተደነገገው “ግምት” እና “ምናልባት” ሳይሆን እውነትና እርግጥ ይሆናል ማለት ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች በርካታ ናቸው፡፡

የሆነ ሆኖ ፍርድ ቤቶች የወ/መ/ስ/ስ/ ህግ አንቀፅ 67 መሰረት አድርገው የሚከለክሉት ክልከላ ፍሬ-ነገር መሰረት ያደረገ ክልከላ መሆኑ ነው፡፡

5.7 በዋስትና ብይን ላይ ድጋሚ ማየትና የሚቀርብ ይግባኝ

ፍ/ቤት በዋስ የለቀቀውን ሰው መልሶ ማሰር ወይም ሌላ ዋስ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ የሚከሰተው በበርካታ ምክንያቶች ነው፡፡ ዋሱ ቢሞት፣ ከሀገር ቢጠፋ፣ ወይም ግዴታውን ሊወጣ የማይችል መሆኑ ሲታወቅ ወ.ዘ.ተ...ነው፡፡ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ አንቀፅ 73 እና 74 ላይ እንደተደነገገው በስህተት ወይም በማታለል የተገኘ የዋስትና ወይም በዋስትና እንዲለቀቅ ውሳኔ በተሰጠ ጊዜ ያልተገለፀ አዲስ ነገር የተገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በስልጣኑ ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት የተለቀቀበትን ሁኔታዎች ወይም ግዴታዎች እንደገና ተመልክቶ የተለቀቀው ተከሳሽ አዲስ ዋሶች እንዲጠራ ወይም በማረፍያ ቤት ሆኖ ጉዳዩ እንዲከታተል ማዘዝ ይችላል፡፡

የዋስትና ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ ተጠርጣሪ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሀያ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማመልከቻውን ማቅረብ እንደሚችል በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ አንቀፅ 75 የተደነገገ ሲሆን፣ ይህን አንቀጽ አስመልክቶ የሚነሳው ጥያቄ ይግባኝ ለማለት የተፈቀደው ለተከሳሽ/ተጠሪጣሪ ብቻ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ የዋስ መብት ጠይቆ ሊከለከል የሚችል ተከሳሽ/ተጠርጣሪ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተከሳሽ ያለውን መብት ለማሳየት ሕጉ በዚህ መልክ የተቀረፀ እንጂ የዋስ መብት በማይፈቅድ ወንጀል የተከሰሰን ሰው በፍ/ቤት በዋስ ቢለቀቅ ዓ/ሕግ ይግባኝ እንዳይጠይቅ የሚከለክለው አይደለም፡፡

ከዋስትና ጋር የተያያዘ የሚከተሉት የፍ/ቤት ውሳኔዎች እንመለከት፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የ ሰበር ይ/መ/ቁ/ 31734፣ 34077፣ 35611 እና 35695 በእነዚህ መዝገቦች ዋስትና ለመከልከል የሚወሰደው ግምት በቂ መንደርደርያ የሚያስፈልገው መሆኑ የገለፀበት፣ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 (3) የተከሰሰ ሰው በ ወ/መ/ስ/ስ/ ህግ አንቀፅ 63 (1) መሰረት ዋስትና መነፈግ እንዳለበት የተወሰነበት፣ ዋስትና በመርህ ደረጃ ውል እንደሆነ የተወሰነበት እና የተሸሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርአትና የማስረጃ አዋጅ ቁጥር 437/97 ዋስትና ላይ ያለው መርህ አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በአጠቃላይ **ሰልጣኞች አጠቃላይ ቅሬታዎቹ፣ ብይኖቹ፣ ውሳኔዎቹ እና የሂደቱ ትክክለኛት ውይይት እንዲያደርጉበት ይደረጋል፡፡ ቅሬታዎቹ፣ ብይኖቹ፣ ውሳኔዎቹ ከፅሁፉ መጨረሻ ክፍል ጋር ተያይዟል፡፡**

5.8 በዋስትና ጥያቄ የዐቃቤ ሕግና ፍርድ ቤቶች ሚና

የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 66 ማንኛውም ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄ ሲቀርብለት ዐቃቤ ሕግ ወይም ዐቃቤ ሕጉ የሌለ ከሆነ ፖ/ሊስ ትችት መስጠት እንዳለበት ይናገራል፡፡ ሕጉ ዐቃቤ ሕግ ትችት መስጠት እንዳለበት እንጂ የትችቱ ይዘት ምን መሆን እንዳለበትና በምን ነጥቦች ላይ የተመሰረተ መሆን እንደሚገባው አይገልጽም፡፡ ሆኖም መስጠት ያለበት ትችት ዋስትና ጠያቂው የጠየቀው የዋስትና ጥያቄ ሊፈቀድለት ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ላይ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 63 (1) ተከትሎ ለሚቀርብ የዋስትና ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ የሚሰጠው አስተያየት ሁለት መልክ አለው፡፡ አመልካቹ ያቀረበውን የዋስትና ጥያቄ ባለመቃወም በቂ ዋስ ጠርቶ እንዲለቀቅ የሚል ወይም የተፈፀመው ወንጀል በሞት ቅጣት፣

በዕድሜ ልክ እስራት የሚያስቀጣና ተበዳዩም የሞተ ወይም የሚሞት ስለሆነ የቀረበውን ጥያቄ እቃወማለሁ ወይም የዋስትና ጥያቄ አቅራቢው የዋስትና ግዴታውን ስለማያከብር ወይም ሌላ ወንጀል ሊፈጽም ስለሚችል ወይም ቢለቀቅ ማስረጃ ሊያጠፋ ስለሚችል የዋስትና ጥያቄውን እቃወማለሁ የሚል ሊሆን ይችላል፡፡

ሀ. የወንጀሉ ዓይነት

ለ. የተጎጂው ሁኔታ

ሐ. ምርመራው ያለበት ደረጃ

መ. የተከሳሹ ባሕርይ (ሁኔታ)

ሠ. ሊወሰንበት የሚችል የቅጣት ክብደት ግምት ናቸው፡፡

ሀ. አንድ የተፈጸመን ወንጀል በምን የሕግ አንቀጽ እንደሚያስከስስ በትክክል ለመለየት የምርመራው መጠናቀቅና የማስረጃ መሰማት ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህም መርማሪው ፖሊስ፣ ፍርድ ቤትና ዐቃቤ ሕግ የሚጫወቱት የየራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ ሆኖም በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 38 (ሀ) መሰረት ወንጀሉን ለይቶ ክስ የማቅረብ ከፍተኛ ድርሻ የተሰጠው ለዐቃቤ ሕጉ ነው፡፡ በቀረበው የፖሊስ ራፖር መሰረት ወንጀሉ የሚያስከስስ ወንጀል ነው? ካስከሰስ ሥልጣኑ የየትኛው ፍርድ ቤት ነው? የሚለው የሚወሰነው በአብዛኛው በዐቃቤ ሕጉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀጽ 63 (1) መሰረት የሚቀርበውን የዋስትና ጥያቄ ለመወሰን ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡

ለ. በዋስትና ጊዜ የተጎጂው ሁኔታ ግምት ውስጥ የሚገባው በሰው አካል ወይም ሕይወት ወይም ከሌላ ወንጀል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሰው ሕይወት ወይም አካል ጉዳት ላይ ደርሶ ከሆነ ነው፡፡ ተጎጂው በደረሰበት ጉዳት ሕይወቱ አልፎ ወይም ሊያልፍ የተቃረበ መሆኑን የሚያሳየው የምርመራ መዝገቡ ላይ የተያያዘው ማስረጃ ሲሆን፣ የዋስትና ጥያቄውን ለመወሰን ሁኔታው በዐቃቤ ሕጉ ወይም በፍርድ ቤቱ ጠያቂነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለሕይወት አስጊ ያልሆኑ የአካል ጉዳቶች ግን ከሌላ ሁኔታ ጋር ካልተያያዙ ዋስትናን አያስከለክሉም፡፡

ሐ. ሕጉ እንደደነገገው ሞትን ወይም 15 ዓመት እና ከዚያም በላይ የሚያስቀጣ፣ የሰው ሕይወት ያለፈበት ወይም ሊያልፍበት የሚችል ወንጀል ከሆነ ሕጉ ዋስትናን የሚያስከለክል ስለሆነ ዐቃቤ ሕግ እነዚህ ሁኔታዎች በተሟሉበት ለዋስትና የሚቀርብ ጥያቄን ይቃወማል፡፡ እዚህ ላይ የሕጉ ችግርና አነጋጋሪው ጉዳይ በአንቀጹ የብዙ ሁኔታዎች በአንድነት መያያዝና በዚህ አንቀጽ ስር የዋስትና ያለመፍቀድ ሁኔታ ከተጎጂው መሞት ጋር ብቻ የተያያዙ መምሰላቸው ነው፡፡ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ አንቀፅ 63 (1) ላይ የተደነገገው ተሟልቶ ከተገኘ ዐቃቤ ሕጉ ተቃወመም አልተቃወም ፍርድ ቤቱ በወንጀሉ የሕይወት ጉዳት ደርሶ ከሆነ ወይም ይደርሳል ተብሎ ከተገመተ ዋስትናን ለመፍቀድ ሥልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡

መ. የተከሳሹ ሁኔታ ዋስትናን ለማስከልከል ምክንያት የሚሆነው ተከሳሹ በዋስትና ሲለቀቅ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. አንቀፅ 67 ስር የተደነገገውን ይፈጽማል ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲገምት ነው፡፡ በመሰረቱ ፍርድ ቤቱን ወደዚህ ግምት ሊያደርሰው የሚገባው የተፈፀመ የወንጀል ዓይነትና የዋስትና ጠያቂው ቀደምት ባሕርያት ናቸው፡፡ ለዚህ እሳቤ መነሻ መሆን የሚገባው ዐቃቤ ሕጉ በዋስትና ጥያቄው ላይ የሚሰጠው አስተያየት ነው፡፡ ዐቃቤ ሕጉ ለዚህ አስተያየት መነሻው የተፈፀመው ወንጀል ባሕርይ እና አፈፃፀሙ ሲሆኑ፣ በጉዳዩም የተጠናቀሩት ማስረጃዎች ለዚህ አጋጣሚ ናቸው፡፡ የዋስትና ጠያቂው ቀደምት ባህርያትም ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ በመሆኑም በዋስትና ጉዳይ ዓቃቤህግና ፍርድ ቤት ያላቸው ሚና የማይተካ ነው፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የዋስትና ጥያቄ ቢያቀርብ በዋስትና እንዲለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አያከብርም ብሎ ለመገመት መነሻዎቹ ምንድናቸው?

2. የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ .75 ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዳይጠይቅ ይከለክላል ወይ?

3. የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 63 ላይ የተጠቀሰውና ዋስትና የሚያስከለክለው ወንጀል መነሻ ቅጣቱ 15 ዓመት የሆነው ነው ወይንስ መነሻ ቅጣቱ ዝቅተኛም ቢሆን ቅጣቱ 15 ዓመት የሚደርሰው ሁሉ?

4. በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 63 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች በአንድ ላየ መሙዋላት አለባቸው ወይስ በተናጠል(cumulative or alternative requirements)?

5. ዋስትናን ለማስተናገድ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 64/2 መሰረት የግድ ጥያቄው በጽኑፍ መቅረብ የለበትም ወይ?

6. በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 63/2 መሰረት በማንኛውም ጊዜ እራሱ ተከሳሹ ከሚያቀርበው ዋስትና በተጨማሪ ለራሱ የዋስትና ግዴታ ሁል ጊዜ መፈረም አለበት ወይ?

ምዕራፍ ስድስት

ክስ ማቅረብ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ፡-

- ክስ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ መልኩ የክስ አፃፃፍ፣ አቀራረብ፣ ክስ ሰለ ሚሻሻልበትና የሚቋረጥበት ሁኔታ ይገነዘባሉ፡፡
- ክስ ከማቅረብ በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሰብአዊ መብት ለማረጋገጥ ያለውን ሚና ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡
- በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ክስ ተመስርቶበት ችሎት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነ ስርዓቶችን አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፡፡

በመሆኑም ክስ ከማቅረብ ጋር ስለሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

6.1 ክስ ስለ ማቅረብ

በመሠረቱ ከደንብ መተላለፍ ወንጀል በስተቀር ማንኛውም ሰው በሕጉ መሠረት የወንጀል ክስ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ሳይቀርብበት ከፍ/ቤት ሊቀርብና ሊፈረድበት እንደማይችል በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ. አንቀጽ 108 በመርህነት ተደንግጓል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ አንቀፅ 38/ሀ እና 40 መሠረት ክስ ለማቅረብ የወሰነ እንደሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ አንቀፅ ከ108-122 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ክሱን አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ማንኛውም የወንጀል ክስ የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ አለበት፡፡

ሀ. የተከሳሽ ሙሉ ስም፣አድራሻና ዕድሜ

ለ. ተከሣሹ የተከሰሰበት ወንጀል ድርጊቱንና የተጣሰውን ሕግ በሚያመላክት ሁኔታ፣

ሐ. ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታና ቀን፣

መ. በወንጀሉ ተጠቂ የሆነውን ሰው ወይም ንብረት እንደ አግባብነቱ

ሠ. ወንጀሉ የሚያስቀጣበትን የሕግ ድንጋጌ፣

ረ. ቀን፣ ቁጥር፣ የዓቃብ ህጉ ስም ፊርማና ማህተም ናቸው፡፡

እያንዳንዱ የወንጀል ክስ ተከሳሹ ለመከላከል በሚችልበት ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ባካተተ መልኩ ስለወንጀሉ ድርጊት አፈጻጸም ሁኔታ ብቁ ማብራሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡ ክሱ ተዘጋጅቶ ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ተከሳሹ ተጠርቶ ክሱ መስማት ከመጀመሩ በፊት የክስ ማመልከቻው የደረሰው ፍ/ቤት ክሱን የማየት ሥልጣን እንዳለው ማረጋገጥ አለበት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የወንጀል ሥልጣን በሕገ-መንግሥቱ፣ በአዋጅ ቁጥር 25/88 ከነማሻሻያዎቹ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት የሚታይ ሲሆን የክልል ፍ/ቤቶች የወንጀል ሥልጣንም በሕገ መንግሥቱ፣ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ እና በክልል ሕግጋት መሠረት የሚታይ ይሆናል፡፡የወንጀል ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣኑ የሌለው ፍ/ቤት ክሱ ከቀረበለት መቀበል የለበትም፡፡ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበን ጉዳይ መመለስ የማይቻለው ወንጀሉ በወ/ሕ/ አንቀፅ 665 ሥር የሚወድቀውን ስርቆትን የተመለከተ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥመው ከፍተኛው ፍ/ቤት ዝም ብሎ ጉዳዩን ማስተናገድ አለበት፡፡

ከሥልጣን ጋር ተያይዞ የሚያጋጥመው ሌላው ችግር የተወሰኑ ወንጀሎች በአንዱ ፍ/ቤት ሥልጣን ክልል ሥር ሌሎቹ ደግሞ በሌላ ፍ/ቤት ሥልጣን ክልል ስር የሚወድቁ ሲሆን በምን ዓይነት ሁኔታ መስተናገድ አለባቸው የሚለው ነው። ለምሣሌ በወ/ሕ/ አንቀፅ 665 ስር በስርቆት የተከሰሰ ሰው በተጨማሪ በደንብ መተላለፍ በወ/ሕ/ አንቀፅ 809 መሠረት የሚያስጠ ይቀውን ስለት ነገር ወይም በወ/ሕ/ አንቀፅ 854 ስር የሚያስጠይቀውን አጠራጣሪ ነገር ይዞ ቢገኝ ክሶቹ የት መቅረብ አለባቸው የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን የመመልከት ሥልጣን የተሰጠው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው። የከተማው ፍ/ቤት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበታች ሊባል የሚችል አይደለም። ከከተማው ፍ/ቤት ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በይግባኝ የሚቀርብ ጉዳይ የለም። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ አንቀፅ 109/3 መሠረት የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ወንጀሎቹን ጠቅልሎ ለማየት ሥልጣን ያለው የበላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንዲመለከት ነው የሚደነግገው። በክልልም ቢሆን የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በወረዳ ፍ/ቤቶችና የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ካላቸው በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት መሀከል ሊከሰት ይችላል። አሁን ያለው ሕግ ሕግ ለዚህ ግልፅ ምላሽ የላቸውም። የሆነ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ከደረሰው በኋላ በ15 ቀን ውስጥ ክሱን አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት።

መልመጃ

1. እርሰዎ በሚያስችሉበት ችሎት ሲታይ የቆየዉ የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ ምርመራ በማለቁ ጊዜ ቀጠሮ አልተጠየቀም። ይልቁንም ወንጀሉ የነፍስ ግድያ በመሆኑ ዐቃቤህግ ክስ እስኪመሰርት ተጠርጣሪዉ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ይታዘዝልኝ የሚል ጥያቄ ከመርማሪዉ ቀረበ። ተጠርጣሪዉም ይህ የዐቃቤህግ ዉሳኔ በተገቢዉ ፍጥነት እንዲከናወን ይታዘዝልኝ በማለት አመለከተ። በዚህ ክርክር ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉት።
2. ትዕዛዝዎ ተጠርጣሪዉ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የሚያስግድድ እንደሆነ ይገመታል። በዚህ መሰረት ተጠርጣሪዉን ወደማፊሪያ ቤት ሲልኩት መብቶቹን ለማስጠበቅ ሲባል የሚሰጡት ተጨማሪ ትዕዛዝ ካለ ይህንኑ ይግለጹ።
3. የሰጡት ትዕዛዝ የትኛዉም ይሁን ዐቃቤህግ ክስ ሳያቀርብ ከሦስት ሳምንት በላይ በመቆየቱ በማረፊያ ቤት ያለዉ ተጠርጣሪ በተገቢዉ ፍጥነት ክስ ስላልቀረበብኝ

መፍትሄ ይሰጠኝ በተለይም በዋስ ልለቀቅ የሚል ማመልከቻ ካለበት ከማረፊያ ቤት ሆኖ አቀረበ፡፡ ምን ዒሳኔ ይሰጣሉ? ይጻፉት፡፡

4. ከላይ የሰጧቸዉን ዒሳኔዎች ለመወሰን የተከተሏቸዉን የሂደት ደረጃዎች ይዘርዝሩ፡፡

የክሱ ይዘት ሕጉ ያስቀመጠውን ድንጋጌና ፎርም መከተል አለበት፡፡ የክሱ ይዘት ሕጉ ያስቀመጠውን ድንጋጌና ፎርም መከተል አለበት፡፡ ከይዘቱ ጋር ተያይዞ የሚነሣው አንዱ ችግር ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/አንቀፅ 111/1/ሐ ሥር የተጠቀሰው ጊዜ የሚለው ቃል ነው፡፡ አንዳንዶች ጊዜ ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመትን የሚያጠቃልል ነው፡፡ እነዚህ የጊዜ ክፍፍሎች እያንዳንዳቸው በክሱ ላይ ካልተዘረዘሩ ክሱ ተቀባይነት ለኖረው አይገባም፡፡ የተከሣሹን የመከላከል መብት ያጣብባል፡፡ ፍ/ቤት ውድቅ ሊያደርገው ይገባል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡

በሌላ በኩል የሚነሣው ክርክር ሕጉ የሚለው 'ጊዜ' ነው፤ ጊዜ ደግሞ በተለያየ መልክ ሊገለፅ ይችላል፤ እያንዳንዱን የጊዜ ክፍልፋይ የሚቻል ሆኖ ማስቀመጥ ከተቻለ ጥሩ ነው፤ ነገር ግን ሰዓትና ቀን አልተጠቀሰም ብሎ ከወዲሁ ክሱን ውድቅ ማድረግ ተገቢ አይደለም፤ ጊዜ ተሟልቶ ባለመጠቀሱ ብቻ ክሱ ከወዲሁ በዚህ ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊሆን አይገባም፤ እያንዳንዱ ጉዳይ ክሱን ለማስረዳት ከቀረበው ማስረጃ አንፃር መታየት አለበት፡፡ ለምሳሌ አንድ በእምነት በባለ አደራነት ንብረት እያስቀመጥክ ጊዜው ይክደኛል የምትልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም የሚል ክርክር ነዉ፡፡

መልመጃ

1. በተከሳሹ ላይ የቀረበዉ ክስ ጊዜዉን የሚጠቅሰዉ 'በትክክል ተለይቶ ባልታወቀ ቀንና ሰዓት' በማለትነዉ፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ በወንጀሉ ቦታ አልነበረምና ይህን መከላከያ ለማንሳት ቢፈልግም ክርክሩ አስቸጋሪ እንደሚሆንበት ስለተገነዘበ አስቀድሞ የክሱን ፎርምና ይዘት አስመልክቶ መቃወሚያ አነሳ፤ ይህም ጊዜዉ በበቂ ሁኔታ አልተገለጸም፣ በበቂ ዝርዝር እንዲገለጽ ተደርጎ ክሱ ሊሻሻል ይገባል በማለት፡፡ ምን ብለዉ ይወስናሉ?
2. በሌላ በኩል ክሱ ወርና ቀን የሚጠቅስ ቢሆንም ከቀኑ የትኛዉ ክፍል እንደሆነና ሰዓት አይገልጽም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ተከሳሽ በወንጀሉ ጊዜና ቦታ ስላልነበረ

በዚሁ መከላከል የሚፈልግ ቢሆንም ክሱ ሰዓት ስለማይገልጽ ይህን መከላከያ ከመከራከሩ በፊት ክሱ ሰዓት በሚገልጽ ሁኔታ እንዲስተካከል መቃወሚያ አነሳ፡፡ የሚሰጡት ዉሳኔ ከላይኛዉ የተለየ ይሆናል?

3. *"ዐቃቤ ሕግ ክሱ ላይ በፖሊስምርመራ ጊዜ ሊታወቅ ያልቻለን ጊዜ ሊጠቅስ አይችልም፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ሰዓቱ ቀኑና ወሩም ባለመጠቀሱ ብቻ የተከሣሹ መብት ይጣበባል ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ በዐ/ህግ ወንጀል መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሣሹ ሕፃኗን በአግባቡ ይዞ ይንከባከብ እንደነበረ ማስረዳት አለበት፡፡ በደሉ በሌላ ሰው ደረሰ የሚልም ከሆነ ይህንን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ኃላፊነቱ የራሱ ነው፡፡ የጊዜው ክፍልፋይ አልታወቀም በሚል ምክንያት ብቻ ክሱ ውድቅ ሊሆን ፈፅሞ አይገባም፡፡ እንደነገሩ ሁኔታ የቀረበውን ክስ ከሕጉና ከማስረጃው አንፃር መመዘን አለበት፡፡"* የሚለዉን ክርክር ምን ያህል ይቀበሉታል?

ለምሳሌ፡-

አንድ አባት የሦስት ዓመት ህፃን ልጁን ለማሣደግ ከባለቤቱ ጋር በፍ/ቤት ሲፋታ ተረክቦ እቤቱ ከወሰዳት በኋላ በመደብደብ አካሏ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርስና ከወራት ቆይታ በኋላ ጉዳዩ ተደርሶበት ሲከሰስ ተበዳይዋ ህፃን ሰዓቱን፣ ቀንና ወሩን አስታውሣ መግለፅ ተቸገረች፡፡ ተበዳይዋ ህፃን በደሉን ያደረሰባት አባቷ መሆኑን ካስረዳችና ጊዜውን ግን ካላስታወሰች በዚህ ምክንያት ብቻ ውድቅ ማድረግ ምን ያህል ፍትሃዊ ወይም ኢፍትሃዊ ይሆናል?

በወ/ሕ/አ 23 መሠረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሶስት መሠረታዊ መስፈርቶች በክሱ ላይ ተገልፀው መመልከት እንዳለባቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ አንቀፅ 111 ስር ተደንግጓል፡፡ ይህንን ለይቶ አብራርቶ ማስቀመጥ እንደቀላል የሚታይ ነገር አይደለም፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክስ ከማቅረቡ በፊት ተጣሰ የተባለ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መኖሩን እና የወንጀሉን ማቋቋሚያ መስፈርቶች የአዕምሮ ሁኔታና ግዙፋዊ ተግባራትን መለየት አለበት፡፡ በዚህ መልኩ በጥንቃቄ ክስ አዘጋጅቶ ማቅረብ ሁልጊዜ ቀላል አይደለም፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ሌላውን በጥፊ ቢመታውና በአካሉ ላይ ፊቱ ከመቅላቱ ውጪ ምንም ጉዳት ባይደርስ ክሱ መቅረብ ያለበት በወ/ሕ/ አንቀፅ 560/1 መሠረት በእጅ ዕልፈት ነው ወይስ በወ/ሕ/ አንቀፅ 840 መሠረት በደንብ መተላለፍ በሚል ሊያጠያይቅ ይችላል፡፡

በተመሣሣይ በወ/ሕ/ አንቀፅ 665 ሥር መውደቅ ያለበት የስርቆት ተግባርና በወ/ሕ/ አንቀፅ 852 መሸፈን ያለበት ቀላል ስርቆት ልዩነት በተጨባጭ አንዳንድ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለመለየት አስቸጋሪ ነው። እንደ ነገሩ ሁኔታ በአግባቡ እየታየ ክስ መቅረብ አለበት።

ሌላዉ የክስን ፎርምና ይዘት የተመለከተ ጉዳይ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ አንቀፅ 112 ስር የተደነገገዉ ነዉ። ዐቃቤህግ ክስ የሚያቀርብ ከሆነ ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታዉን በዝርዝር የሚገልጽ መሆን አለበት። ይህም ዝርዝር ክስ የቀረበበትን ተግባር ወንጀል ነዉ ብሎ ከሚደነግገዉ ህግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን አለበት።

ይህ ሁሉ ዝርዝር ዉስጥ ስህተት ሊኖረዉ ወይም ዝርዝሩ ሳይጠቀስ ሊቀር ይችላል። ሆኖም እነዚህ ስህተቶች መከሰታቸዉ ብቻ ክሱን ዋጋ አያሳጣዉም። ነገር ግን ስህተቱ መሠረታዊ ከሆነ ወይም ተከሣሹን ሊያሳስት የሚችል መሆኑ ከታመነበት ወይም ቢዚህምክንያት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የማይቻል ከሆነ ክሱን ዋጋ ያሳጣዋል። ስለዚህ ክሱ ካልተሻሻለ በቀር ክሱ ባለበት ሁኔታ ሊሰማ የሚችል አይሆንም ማለት ነዉ። በመሆኑም ክሱ እንዲሻሻል መደረግ አለበት። ይህም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 118 እና 119 ይመራል።

መልመጃ

1. በተራ ነፍስ ግድያ የቀረበን ክስ የሚያሰማ ዐቃቤህግ ለክሱ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች ሲመረምር ፊጽሞ የተራ ነፍስ ግድያ ሳይሆን ከባድ ነፍስ ግድያ ተደርጎ ክሱ ሊቀርብ እንሚገባዉ ተገነዘበ። በዚህ ጊዜ ክሱን በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 119/1/ መሰረት ለማሻሻል ፍርድቤቱን ጠየቀ። ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ ጥያቄ ላይምን ይወስናሉ?
2. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 119/3/ መሰረት ጥያቄዉ ቢቀርብ ዉሳኔዎ የተለየ ይሆናል?
3. በአጻጻፍ የተፈጠሩ ስህተቶችን ለማረም ክስ ሊሻሻል ማለትም ቀጠሮ ተወስዶ ሊለወጥ ተገቢ ነዉ ይላሉ?

ክሱ በተስተካከለ ወይም በተጨመረበት፣ ወይም አዲስ ክስ በተመሰረተ ቁጥር ለተከሣሹ ተነቦለት እንዲረዳው መደረግ አለበት። የተለየ መቃወሚያ ካለ ወይም መታመኑና መካዱ በድጋሚ መረጋገጥ አለበት። ምክንያቱም በክሱ ላይ የተደረጉትን ለውጦች ተከትሎ ተከሣሹ የተለየ መቃወሚያ ወይም ክርክር ሊያቀርብ ይችላል።

ከዐቃቤ ሕግ ክስ አቀራረብ ጋር ተያይዞ ሣይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሌላው ነጥብ ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚጠቀሰዉ ሕግ ጉዳይ ነው። ይህም በተለያ ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። በመጀመሪያ ህግ በግልጽ ወንጀሉን የሚያከብድባቸዉ ድንጋጌዎች ሱኖሩ ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ ተከሳሹ ቀደም ሲል በፈጸማቸዉ ወንጀሎች ምክንያት ጥፋቱ የሚከብድበት ሁኔታ ነዉ። ለምሳሌ በወ/ህ/ አንቀፅ 407/2/ እንደተመለከተዉ በዚሁ ህግ ንኡስ ቁ 1 የተመለከተዉን ወንጀል የሚያከብድ ድንግጌ ነዉ። ከዚህ ዉጪ ተከሳሹ ከዚህ በፊት በፈጸመዉ ወንጀል ቅጣት ሊከብድበት እንደሚችል በወ/ህ/ አንቀፅ 184 እና ተከታዮቹ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን እነዚህም ተደራራቢ ወንጀሎችና ተደጋጋሚ ወንጀሎችን የሚመለከት ነዉ።

መልመጃ

1. ተከሳሹ በወ/ህ/ቁ 407/1/ የተመለከተዉን የሙስና ወንጀል ለመፈጸሙ በወንጀል ምርመራ ተረጋግጧል። በዚህ ላይ ተመስርቶ ዐቃቤህግ ክስ እንዲያቀርብ ይጠበቃል። በወንጀል አፈጻጸሙ ረገድ በህጉ በንዑስ ቁ. 2 የተመለከቱት ማክበጃ ሁኔታዎች መኖራቸዉን ማስረጃዉ ያረጋግጣል። ዐቃቤህጉ እርስዎ እንደሆኑ ያስቡ። በዚህ መሰረት ትክክለኛ የሚሉትን የክስ አጻጻፍ ዘዴ ተከትለዉ ክሱን ያዘጋጁ። የወንጀሉን ዝርዝሮች እንደሚመችዎ ይገምቱ።
2. ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙ ታምኖ ምርመራ ተከናዉኖበት ክስ ሊመሰረትበት ታስቧል። ሆኖም በዚሁ ጊዜ ተከሳሹ ከዚህ ቀደም ፈጽሞት በነበረዉ ወንጀል ከሁለት ቀናት በፊት የጥፋተኛነት ፍርድ ተወስኖበት ቅጣቱንም ተቀብሏል። ለዚህ የሚሆን ማስረጃ ከሚቆሙበት ችሎት አግኝተዋል። በአዲሱ ጉዳይ ክሱን እንዴት ይመሰርቱበታል? ዝርዝሩን በራስዎ መገመት ይችላሉ።
3. በሌላ ሁኔታ ሊከሰሱት የተዘጋጁት ተጠርጣሪ ቀደም ሲል በፈጸመዉ ወንጀል ተቀጥቶ ካበቃ ከወራት በኋላ ወንጀል የፈጸመና ምርመራ የተጣራበት ነዉ። በዚህ ምክንያት ጥፋቱ ሊከብድ ይችላል። ይህን ተጠርጣሪ ክስ የሚመሰርቱበት እንዴት ነዉ? ዝርዝሩን በራስዎ ይገምቱ።
4. ከላይ የተመለከቱትን ክሶች ለማቅረብ ሲወስኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 114 የሚደነግገዉን ይመርምሩ።

በክሱ ላይ የማስረጃ አጠቃቀስን በተመለከተ የተለያየ አሠራር አለ። ምስክሮች፣ ሠነዶችና ሌሎች ማስረጃዎች ምን እንደሚያስረዱ በማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ላይ በግልፅ ማስቀመጥ በጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ የተለመደ አሠራር ነው። በሙስና ወንጀሎች የክስ ሂደት ደግሞ ይህን ሂደት ለመምራት በወጣዉ ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ ህግ /አዋጅ ቁጥር 434/1997/ እንደተደነገገዉ ቅድመክስ በተባለዉ ሂደት ዉስጥ ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸዉ እና ሰነዶቻቸዉ የሚያስረዱትን ነገር ዘርዝሮ ማቅረብ ግዴታ ነዉ። ይህ በችሎት ሂደት ምስክሩ በቀጥታ ወንጀሉን ሲፈጽም ያየ የዓይን ምስክር ነው ወይስ በተዘዋዋሪ መንገድ ያወቀ የሚለውን ለይቶ ቢያስቀምጥ እራሱ ዐቃቤ ሕግ የችሎቱን ሂደት በቀላሉ ለመምራትና አላስፈላጊ የተደጋገመ የምስክርነት ቃልን ለመለየት ስለሚረዳ ጠቀሜታው የጐላ በመሆኑ ሊተገበር ይገባል። በአብዛኛው ግን የማስረጃ ዝርዝር ስር ማስረጃዎችን በቻ በመጥቀስ በግልፅ የሚያስረዱትን ሳይገልጹ ማቅረብ የተለመደ ነው።

ሲጠቃለል ዐቃቤ ሕግ ክስን ማቅረብ የመጨረሻ አማራጭ አድርጐ መውሰድ አለበት። ከክስ በፊት ጉዳዩ ዕልባት ማግኘት ካለበት ይህንን አረጋግጦ መዝገቡ መዘጋት አለበት። ክስ ለማቅረብ ከወሰነም አዘገጃጀቱ ሕጉን ተከትሎ ፍትሐዊ ውሣኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ግልፅ የሆነ ክስ መቅረብ አለበት።

6.2 ክስን ስለ ማሻሻል

ከላይ እንደ ተገለፀው ኣንድ ክስ ፍርድ /ውሳኔ/ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ፍ/ቤቱ በራሱ ኣስተያየት ወይም በባለጉዳዩች ማመልከቻ በቀረበለት ጊዜ ክስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/አንቀፅ 119 ተደንግጎ ይገኛል። ይህ የሕግ አንቀፅ እንደሚያመለክተው በተከሳሽ ላይ በቀረበው ክስ ዋና ስህተት የተገኘ ሲሆን ወይም ያልተጠቀሰ ነገር ሲገኝና ይኸውም ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ በመሰለ ጊዜ እንደ ነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ ወይም እንዲጨመር ወይም ኣዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ፍ/ቤቱ ማዘዝ እንደሚችል ነው። ስለዚህ የክስ ማሻሻል ውጤት በክሱ ላይ ለውጥ ማድረግ ወይም መጨመር ወይም ኣዲስ ክስ ማዘጋጀት ነው።

በዚህ የሕግ አንቀፅ ዙርያ ሲያከራክር የነበረና አሁንም እያከራከረ ያለው ነጥብ ክስን የማሻሻል ዓላማ በሚመለከት ነው፡፡ ክስን የማሻሻል ዓላማ ተከሳሹን ሊያሳስትና ሊጎዳ የሚችል ስሕተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ (ለተከሳሹ ጥቅም ሲባል የሚደረግ) ነው የሚሉ እንዳሉ ሁሉ፤ ለተከሳሹ ጥቅም ብቻ ተብሎ ሳይሆን ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የማያስችል ስህተት ሲገኝም ክስ መሻሻል አለበት ብለው የሚከራከሩ አሉ፡፡ የመጀመርያው ሓሳብ የሚደግፉ ሰዎች ለክርክራቸው መሰረት አድርገው የሚወስዱት ዓንቀፅ 119 ብቻ ሲሆን፤ ሁለተኛው አመራጭ የሚደግፉ ደግሞ አንቀፅ 119 ከአንቀፅ 118 በማጣመር ሊታይ ይገባል ይላሉ፡፡ አንቀፅ 118 እንደሚያመለክተው “... ስህተቱ ወይም ሳይጠቀስ የቀረው አስፈላጊ ነገር ካልሆነ ወይም ስህተቱ ወይም ሳይጠቀስ የቀረው ተከሳሹን ያሳሰተው ካልሆነ ወይም በዚህ ምክንያት <u>ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የማይቻል ካልሆነ በቀር</u> እንዲህ ያለ ስህተት ወይም ሳይጠቀስ የቀረው ነገር ክሱን ዋጋ አያሳጣውም፡፡” ይላል /ሰረዝ የተጨመረበት/፡፡ ስለዚህ ከሁለቱ አንቀፆች አገላላፅ ክስን የማሻሻል ዓላማ በአንድ በኩል ተከሳሹን እንዳያሳስትና እንዳይጎዳ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ውጤቱ ተከሳሽን የሚጎዳ ባይሆንም ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት ክሱን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም ሊሻሻል እንደሚገባ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

በተግባር እንደሚታየውም ሁለቱ የአተረጓጎም መንገዶች እየተሰራባቸው ይገኛል፡፡ ስለዚህ የወንጀል ፍትሕ ስርዓት ዓላማ የመንግስትና የህዝብ ጥቅም ፤ በወንጀሉ የተጎዳ ሰውን እና የተከሳሹን መብት ለማስጠበቅ በመሆኑ በክስ ማሻሻል ሂደትም የተከሳሹን መብት ለማስጠበቅ /ለመጠበቅ/ ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ የፍትሕ ስርዓቱ ለማሳካት ሲባልም ሊደረግና ግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው ነው፡፡

ሌላ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ክስን የማሻሻል ጥያቄ መቅረብ ያለበት”...ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ...” መሆኑን ቁጥር 119 ያመለክታል፡፡ ይህ ድንጋጌ የተፋጠነ ፍትሕ እንዳይሰጥ ሂደቱ የተጓተተ እንዲሆን ምክንያት አይሆንም ወይ? የሚል ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ኣንድ የወንጀል ጉዳይ የተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ እስከተሰማበት ጊዜ ኣንድ ዓመት ፈጅቷል እንበል፡፡ ከዚያ በኃላ የክስ መሻሻል ጥያቄ ቢቀርብና ቢፈቀድ የክርክሩ ሂደት ኣንድ ብሎ ስለሚጀምር ተጨማሪ ኣንድ ዓመት ሊወስድበት ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የመከላከል መብትንም ሊጎዳ የሚችልበት አጋጣሚ አለዉ፡፡ ማስረጃዉ ተሰምቶ ካበቃ በኋላ ሊባክን ይችላል፡፡ ክሱ እጅግ ዘግይቶ እንዲለወጥ ሲደረግ የዚህን ማስረጃ እንደገና መቅረብ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ካልተገኘ መከላከያ እንዲያጣ ተደረገ ማለት ነዉ፡፡

ክስን የማሻሻል ውጤት ምን እንደሆነ ወይም ክስ እንዲሻሻል ከተፈቀደ በኃላ መደረግ ያለበት ነገር ምን እንደሆነ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ኣንቀፅ 120 እና 121 ተደንግገዋል፡፡ ኣንቀጾቹ እንደሚያመለክቱት፤ ኣንዱ ውጤት፡ ዓ/ሕግ ያቀረበውን የተሻሻለ ክስ ግልባጭ ለተከሳሹ እንዲደርሰው ይደረግና የክስ መሰማቱ ሂደት እንደ ኣዲስ ይጀምራል፡፡ ቀጥሎ፡ ዓቃቤ ሕግ ማስረጃውን ያሰማል፤ ተከሳሽም የመከላከያ ማስረጃ ካለው ያቀርባል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስነ ስርዓት ሳይፈፀም የሚቀርበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡

ከክስ ማሻሻል ጋር የተያያዘ ኣንድ የፍ/ቤት ውሳኔ እንመለከት የከፍተኛ ፍ/ቤት ኮ/መ/ቁ/ 20464 እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የይ/መ/ቁ/ 26293፣ 36932፣ 48189

ይግባኝ ባይ..... የፌደራሉ ከፍተኛ ዓ/ሕግ

መልስ ሰጭ.....ሰማኸኝ በለው

የጉዳዩን ኣጀማመር የፌደራሉ ከፍተኛ ዓቃቤ ህግ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በጠቅላዩ ፍርድ ቤት ደግሞ መልስ ሰጪ በነበረው ሰው የ1949 ዓ.ም የወነወጀለኛ መቅጫ ህግ ኣንቀፅ 526/1/ በመተላለፍ ሃምሌ 7 1994 ዓ.ም ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት .....የግል ተበዳይ ግሩም ተስፋዮን በቸልተኝነት በመኪና ገድሎታል የሚል ክስ አቀረበ፡፡

ጉዳዩን ይከታተል የነበረው የፌደራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት 8ኛ ወንጀል ችሎት ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ አንቀፅ 141 መሰረት በነፃ አሰናበተው፡፡ የፌደራሉ ከፍተኛ ዓቃቤ ህግ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማለቱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የይ/መ/ቁ/ 36932 ጉዳዩን አይቶ በተከሰሰበት አንቀፅ ይከላከል ሲል ብይን ሰጠ፡፡ መዝገቡ ለፌደራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት 9ኛ ወንጀል ችሎት ቀረበ፡፡

ይህ ከሆነ በኃላ ዓቃቤ ህግ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ አንቀፅ 119 መሰረት ክስ እንዲያሻሽል ጠየቀ፡፡ የፌደራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት 9ኛ ወንጀል ችሎት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ በይ/መ/ቁ/ 26293 በተከሰሰበት አንቀፅ ይከላከል ሲል የሰጠውን ብይን መሰረት በማድረግ ተከሳሽ እንዲከላከል አዘዘ፡፡ ተከሳሽ መከላከያ ምስክር ባለማቅረቡ ጥፋተኛ ተብሎ 3.000 ብር ተቀጣ፡፡

የፌደራሉ ከፍተኛ ዓ/ሕግ በድጋሚ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ አንቀፅ 119 መሰረት ክስ እንዲያሻሽል ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ እና በውሳኔው ላይ በጠቅላላ ይግባኝ አቀረበ፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የይ/መ/ቁ/ 36932 ጉዳዩን አይቶ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ክሱ እንዲሻሻል አዘዘ፡፡

ሰልጣኞች አጠቃላይ ቅሬታዎቹ፣ ብይኖቹ፣ ውሳኔዎቹ እና የሂደቱ ትክክለኛት ውይይት እንዲያደርጉበት ይደረጋል፡፡ ቅሬታዎቹ፣ ብይኖቹ፣ ውሳኔዎቹ ከፅሁፉ ተያይዟል፡፡

6.3 ክስን ስለ ማንሳት

ክስን ማንሳት ሲባል በመሰማት ሂደት የነበረ ክስ በተለያዩ ምክንያቶች ሂደቱ እንዲቋረጥና መዝገቡ ለዘለቄታው ወይም ለጊዜው እንዲዘጋ የሚደረግበት ስርዓት ነው፡፡ ክስ የሚነሳበት ምክንያት /ሁኔታ/ በወ/መ /ስ/ስ /ሕጋችን በአንቀፅ 122 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የዚህ ዓንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እንደሚያመለክተው በድሮው የወ/መ/ ሕግ ቁ.522 (በአሁኑ የወ/ሕግ ዓንቀፅ 539) ወይም በድሮው የወ/መ/ሕግ ቁ.637 (በአሁኑ የወ/ሕግ ዓንቀፅ 671) መሰረት ከቀረበው ክስ በስተቀር ዓ/ሕጉ በተከሳሹ ላይ ያቀረበውን ማንኛውም ክስ በፍርድ ቤቱ ፈቃድ ከፍርድ በፊት ክሱ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ ክሱን ለማንሳት እንደሚችል ነው፡፡

ስለዚህ ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳቸው ቁምነገሮች ፤

ሀ) ከከባድ የሰው ግድያ እና ከከባድ የወንብድና ተግባር ክሶች ውጭ ሌሎች ክሶች ሊነሱ እንደሚችሉ ፣

ለ) ዓ/ሕጉ ክሱን ማንሳት የሚችለው በፍ/ቤቱ ፈቃድ መሆኑን ፣ እና

ሐ) ክሱን ማንሳት የሚቻለው ከፍርድ በፊት በማንኛም ጊዜ መሆኑን ናቸው።

የወ/መ/ስ/ስ/ ሕጋችን የሁለቱ ከባድ ወንጀሎች ክስን በተመለከተ ማንሳት የከለከለበት ምክንያት ሁለት ነገሮችን ታሳቢ በማድረግ ሊሆን ይችላል ። በአንድ በኩል እንደዚህ የመሳሰሉትን ከባድ ወንጀሎች በህዝብ ላይ ስጋት የሚፈጥሩና ሰላምን የሚነሱ በመሆናቸው በእነዚህ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች ወንጀሉን መፈፀማቸው የሚያስረዳ ማስረጃ እስከ ቀረበ ድረስ ጥፋተኛ ተደርገው ሊቀጡ እንደሚገባና የዚህ ወንጀል ሰለባ የሆኑ ሰዎችም ሕግ ከለላ የሰጣቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ተከሳሾች በተከሰሱበት ጉዳይ ቁርጣቸውን አውቀው እንዳያርፉ፤ አንዴ ክስ ተነስቶ መዝገብ እየተዘጋ ሌላ ጊዜ እየተንቀሳቀሰ እንቅልፍ እንዳያጡ ከሚል ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ግን አለ ። በእነዚህ ሁለት ወንጀሎች ዓ/ሕግ ክስ እንዲያነሳ ያልተፈቀደለት ምክንያት ከባድ ወንጀሎች ስለሆኑ ነው ያልን እንደሆነ እነደዘር ማጥፋ በሰብአዊ ፍጥረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን፤ በሕገ መንግስታዊ ስርዓትና በአገር ውስጥ ደህንነት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎችን ወዘተ የመሳሰሉት ከባድ ወንጀሎች ለምን ሳያካትት ቀረ? የሚል ነው። ስልጣኞች በቡድን ውይይት የሚያዩት ይሆናል።

ሌላው ክስ ሊነሳ የሚችልበት መንገድ በዐቃቤ ሕግ ክሱ እንዲነሣ ሲደረግ ነው። በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ውስጥ የነበሩት ክሱን ዐቃቤ ሕግ እንዲያነሣ የሚፈቅዱ ድንጋጌዎች በሙሉ በአዋጅ ቁ. 39/85 ተሽረዋል የሚል ክርክር የሚንፀባረቅና ቁርጥ ምላሽ ያልተሰጠበት ጉዳይ መሆኑ ነው። አሁን ዐ/ሕግ ክስን ለማንሣት ያለው የሕግ ድጋፍ አዋጅ ቁ. 691/2003

/እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 16/5 እና 6 ነው። በዚህ አንቀፅ ዐቃቤ ሕግ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ማድረግ ወይም በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ የማንሣት ሥልጣን ተሠጥቶታል እንጂ ይወ/መ/ህ/ስ/ስ/ አንቀፅ 122 መሰረት ተደርጎ መታየት የለበትም የሚሉ ወገኖች በርካቶች ናቸው።

መልመጃ

1. አዋጅ ቁ. 691/2003 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 16/5 እና 6 በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ የማንሣት ሥልጣን ለዓቃቤህግ መሰጠቱ ፋዳው ምንድን ነው?
2. የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት አለ የሚባለው መቼ ነው?
3. ክስ ለማንሳት የሚረዱ ተጨባጭ የህግ ድንጋጌዎች ካሉ ግለፁ?

በምርመራ ላይ ያለን የወንጀል ጉዳይ ለማስቆም ግልፅ ሥልጣን ለፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተሠጥቶታል። የሚያነጋግረው አንድ ጊዜ ክስ ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ክስ ማንሣት ይችላል ወይ? የሚለው ነው። ሕጉ የሚለው በሕጉ መሠረት ክስ ያነሣል ነው። ክስ ለማንሣት በቀጥታ አይፈቀድም። በሕግ መሠረት ስለሚል ክስን ማንሣት የተመለከቱ ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች መፈለግ አለባቸው የሚሉ ክርክሮች ይቀርባሉ። በሌላ በኩል የዐቃቤ ሕግ ክስ የማንሣት መብት ሕጉ ሠጥቶታል። ክሱን ለማንሣት በቂ ምክንያት ካለ ሊቋረጥ ይችላል የሚሉ ክርክሮችም ይንፀባረቃሉ።

የሌሎች የሕግ ስርዓቶች ተመክሮ ስናይ፤ የኮመንሎው የሕግ ስርዓት በሚከተሉ ኣገሮች ዓ/ሕግ በቂ ምክንያት ይኑሮው ኣይኑሮው በፈለገው ጊዜ ክሱን ማንሳት የሚችል ሲሆን በሲቭሉ የሕግ ስርዓት ተከታይ ኣገሮች ግን ዓ/ሕግ ክስ ካቀረበ በኃላ የማንሳት ስልጣን (መብት) የለውም።

በሶስተኛ ደረጃ ክስ የሚነሳበት ጊዜ መቼ እንደሆነ ቁ.122 (1) ኣመልክቷል። ይኸውም ክሱን ማንሳት የሚቻለው ከፍርድ በፊት በማንኛውም ጊዜ ነው ይላል። አዋጅ ቁ. 691/2003 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 16/5 እና 6 በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ የማንሣት ሥልጣን ለዓቃቤህግ ከመስጠቱ ውጭ ያለው ነገር የለም። ከፍርድ በፊት ማለት ግራና ቀኙ ተከራካሪ

ወገኖች ማስረጃቸውን ኣቅርበው ካጠናቀቁ በኃላና መዝገቡ ለውሳኔ ከተቀጠረ በኃላ የክስ ማንሳት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነም ተቀባይነት ኣለው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃው ኣቅርቦ የዓ/ሕግ ማስረጃ ካስተባበለ በኃላ ክስ እንዳነሳ ይፈቀድልኝ ብሎ ለሚያቀርበው ጥያቄ እሱ የሚጠብቀውን መልስ መስጠት ለተከሳሹ የሚጎዳ ኣይሆንም ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዓ/ሕግ ለጊዜው ብቃት ያለው ማስረጃ ባለማግኘቱ ክሱን በተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ የተስተባበለበት ቢሆንም ለወደፊቱ በበቂ ሁኔታ ሊያስረዳልኝ የሚችል ማስረጃ ላገኝ እችላለሁ ብሎ ሲያምን ክሱን እንዲያነሳ ቢፈቀድለት ወንጀለኞች እንዳያመልጡ ያግዛል የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

ከክስ ማንሳት፣ ማቋረጥና ይርጋ ጋር የተያያዘ የሚከተሉት የፍ/ቤት ውሳኔዎች እንመለከት፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የ ሰበር ይ/መ/ቁ/ 28952 በይግባኝ ባይ..... የጉምሩክ ዓቃቤ ህግና በመልስ ሰጭ..... በንቲ ተአሬ መዝገብ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ አንቀጽ 122 (2) መሰረት ዓቃቤ ህግ ክስ ካነሳ በኃላ ድጋሚ ክስ ስለማቅረቡ የተሰጠ ብይን መሰረት በማድረግ ሰልጣኞች ውይይት እንዲያደርጉበት ይደረጋል፡፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የ ሰበር ይ/መ/ቁ/ 45572 መሰረትም መደበኛው ይርጋ ለተነሱ ክሶችም እንደሚያገለግል ተመለተከተቷል፡፡ የተሰጠው ብይን መሰረት በማድረግ ሰልጣኞች ውይይት እንዲያደርጉበት ይደረጋል፡፡ **ብይኖቹና ውሳኔዎቹ ከፅሁፉ ተያይዟል፡፡**

ስለዚህ ከአንቀፅ 122 መገንዘብ የሚቻለው፡- ጥያቄዉ ይህ ህግ ተፈጻሚነት ኣለዉ ወይ የሚለዉ ነዉ፡፡ በከፊል ተሸሯል፡፡ ክስ ከተነሳ በኃላ የሚኖረዉን ዉጤት በተመለከተ ከሚደነግጉት ክፍሎቹ በቀር ሌላዉ ተሸሯል፡፡ ስለዚህ ክስ ማንሳት ያለማንም ፈቃጅ ከልካይነት በዐቃቤህግ ፈቃድ ብቻ የሚከናወን ነዉ ወደሚል መደምደሚያ ያደርስ እንደሆነ መወያያ ይሆናል፡፡

1. ክስን ማንሳት የማይቻልበት ሁኔታ እንዳለ (ከባድ የሰው ግድያ እና ከባድ የውንብድና ተግባር የሚመለከት ክስ ሲሆን) ፣
2. በዓ/ሕግ ኣመልካችነት በፍ/ቤቱ ፈቃድ (ክሱን ለማንሳት ወይም ላለማንሳት ውሳኔ በመስጠት) ክስ የሚነሳበት ሁኔታ እንዳለ ፣ እና
3. ዓ/ሕግ ክሱን እንዲያነሳ በመንግስት ሲታዘዝ ፍ/ቤት የግድ መፍቀድ እንዳለበት ነው፡፡

የመወያያ ነጥቦች

1. **ዐቃቤ ሕግ ክስ አዘጋጅቶ ከማቅረቡ በፊት ሊከተላቸው የሚገቡ ሂደቶች ምንድናቸው ?**
2. **ብቃት ያላቸውን ክሶች አዘጋጅቶ ለማቅረብ ዐቃቤ ሕግ ምን ዓይነት አሠራሮችን መከተል አለበት?**
3. **ክስ ላይ ማናቸውም ዓይነት ቀላል ስህተት በተገኘ ቁጥር ተሻሽሎ አዲስ ክስ መቅረብ አለበት ወይስ እንደነገሩ ሁኔታ እየታየ ቀላል ስህተቶች በፍ/ቤቱ እውቅና የተከሣሹ ወይም ጠበቃው አስተያየት ተሰምቶ እዚያው ክሱ ላይ ሊስተካከል ይገባል?**
4. **ክስን ከቀላል ወደ ከባድ ማሻሻል ሊከለከል ይገባል ወይ?**
5. **ቅጣት የሚያስከትዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ በምን መልኩ ክስ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት?**

ምዕራፍ ሰባት

ምስክር መፈተን

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ፡-

- **ከማስረጃ አቀራረብና ምሰክር መፈተን ጋር የተያያዙ የቅድመ ዝግጅትና ፍፃሜ አተገባበር ስርአትች ሁኔታ ይገነዘባሉ፡፡**
- **የማስረጃ አቀራረብና ምሰክር መፈተን ክህሎት በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሰብአዊ መብት ለማረጋገጥና የያዙት ጉዳይ እንዲያሸንፉ ከማስቻል ረገድ ያለውን ሚና ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡**

- በችሎት የሚፈጸሙ ስነ ስርዓቶችን አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፡፡

በመሆኑም ከማስረጃ አቀራረብና በተለይም ከምሰክር መፈተን ጋር ስለሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

7.1 ስለ ምስክር አቀራረብና መፈተን በጠቅላላ

የወንጀል የፍትሕ ሥርዓቱ የተከሣሾችን ሕገ-መንግሥታዊ መብት ባረጋገጠ ሁኔታ የወንጀል ህጉን ዓላማና ግብ የሚያስጠብቅበት ሂደት ኃላፊነትን በብቃት መወጣትን የሚጠይቅ ዓቢይ ተግባር ነው፡፡ የዚህ ክፍል ገለጻ ዓላማም በዚህ ሂደት ዙሪያ የፍትህ ባለሙያዎችን ዓቅምና ችሎታ መገንባትና ብቁ ሆነው እንዲገኙ መርዳት ነው፡፡

ምስክር መፈተን የሰው/ ቃል/ ማስረጃ አቀራረብ አንድ ክፍል ሲሆን፤ የእውቀትና ክህሎት ቅንጅት የሚጠይቅ ራሱን የቻለ የተከራካሪ ወገኖች ሞያዊ ጥበብ ነው፡፡ በማስረጃ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት የማስረጃ አስፈላጊነቱ አከራካሪ የሆነ ፍሬ ነገርን እውነትነት /ሐሰትነት ወይም መኖርና/ አለመኖር ወይም መፈጸምና/አለመፈጸም ለማረጋገጥ ነው ለክርክር ምክንያት የሆኑት ፍሬ ነገሮች ከታመኑ የሕግ ግምት የሚወሰድባቸው ወይም በዳኛ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚታወቁ ሲሆኑ እንደተረጋገጡ የሚቆጠር ሲሆን በዚህ ሁኔታ መረጋገጥ የማይችሉት ሁኔታዎች ግን በማስረጃ እንዲረጋገጡ በሕግ ግዴታ ተጥሏል፡፡

ክስ ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ አግባብነት ያለው፣ አስፈላጊ እና ተቀባይ ሊያገኝ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ለመከላከልም እንዲሁ፡፡ በቃል ማስረጃ /ምስክሮች/ የሚያቀርብ ዐቃቤ ሕግ የሥነ አመክንዮ ሕጎች ጠንቅቆ ማወቅ ይገባዋል፡፡ ዐቃቤ ሕግ የሚያቀርባቸው ምስክሮች ልዩ አዋቂዎች ወይም የፍሬ ነገር ምስክሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተከላካይ ጠበቃውም ቢሆን እንዲሁ ለመከላከል የሚያቀርበው ማስረጃ አግባብነት ያለው፣ አስፈላጊ እና ተቀባይ ሊያገኝ የሚችል መሆን አለበት፡፡ የሕግና የሥነ አመክንዮ እውቀቱ የላቀ ሊሆን ይገባል፡፡ ለአዋቂና የፍሬ ነገር ምስክሮች የሚቀርበውን ጥያቄ በጥንቃቄ ማዘጋጀት አለበት፡፡ ችሎቱን የሚመሩት ዳኞችም እንዲሁ የሚቀርበው ማስረጃ አግባብነት ያለው፣ አስፈላጊ እና ተቀባይ ሊያገኝ የሚችል መሆን፣ በዓቃቤ ህግ ወይም በተከላካይ ጠበቃው በየደረጃው የሚቀርቡ ጥያቄዎች አግባብነት፣ ከጉዳዩ ጋር የሚኖራቸው ትስስርና ግንኙነት በአጠቃላይ ምስክር የሚፈተንበት ዘዴና እውቀት ሊኖራቸው የግድ ይላል፡፡ ይህ ካልሆነ

በችሎት አመራር ሂደት ውስጥ የሚያስተላለፋቸው ትእዛዞች፣ ብይኖችና ውሳኔዎች ላይ የሚኖረው ተፅእኖ አደገኛ ሊሆን ይችላል፡፡

የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበዉ የሚሰሙ ከሆነ በምስክር ማሰማት ጊዜ የሚገጥሙ ችግሮችን ለመቋቋም አንዱና ትልቁ መርህ ዝግጅት ነዉ:: ክሱ የሚመሰረተዉ በምርመራ ጊዜ በተመዘገቡ ማስረጃዎች ስለሆነ በተለይ ምስክሮች ፍርድቤት ሲቀርቡ በርግጥ በምርመራ ጊዜ እንደተመዘገበዉ (እንደክሱ) ይናገሩ እንደሆነ ዐቃቤህግ አስቀድሞ ሊያዉቅ ያስፈልጋል:: ዝግጅት የምስክሩን ብቃት ከመገምገምና ከመወሰን በተጨማሪ ይህን ብቃት ለማጎልበትም ይረዳል:: በሃገራችን የሙግት አካሄድ በከፊል አድቨርሳሪያል እንደመሆኑ ተቃራኒ ወገን በምስክር መስማት ጊዜ መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለዉ:: ምስክር በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ እንዳይምታታበት ወይም የመስቀለኛ ጥያቄን ዓላማ የማምከን ችሎታ እንዲኖረዉ አስቀድሞ ሊዘጋጅ ይገባል:: ለዚህም ስለሚመሰክርበት ነገር ያለዉ ዕዉቀት በዝርዝር ሊመረመር ይገባል::

በቅድሚያ ዐቃቤህግ ማስረጃዉን ለማቅረብ የመክፈቻ ንግግር ያደርጋል:: ይህም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 136(1) መሰረት የቀረበዉን ክስና የሚቀርበዉን ማስረጃ ባህሪ ባጭሩ፣ በትክክል (objectively) እና ያለአድልዎ (impartially) የሚገልጽ ነዉ:: ስለዚህ የክሱን መሰማት ከመክፈት በፊት ፍርድቤት ቀርቦ የሚሰማዉ ማስረጃ ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነዉ ማለት ነዉ:: በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 136 እንደተመለከተዉ የክስ መክፈቻ ሲቀርብ በትክክል ወይም በተጨባጭ ሊሆን ይገባል:: የሚቀርበዉ ሃሳብ ተጨባጭ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚገለጸዉ ነገር በርግጥ ለመኖሩ ርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል:: ይህንም ለማድረግ ምስክሮች በርግጥ የሚናገሩትን ነገር አስቀድሞ ማወቅ ተገቢ ነዉ፡፡

ቀጥሎም ዓቃቤ ሕጉ ምስክሮቹን መጥራት አለበት ምስክሮቹ ተራ ሰዎች ወይም ልዩ እዉቀት ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርባቸው ምስክሮች ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ ብቻ ያሳወቃቸው ብቻ ነው፡፡ የነገሩ መሰማት ከተጀመረ በኋላ ክሱ የተሻሻለ ወይም አዲስ ክስ የተዘጋጀ ከሆነ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ አንቀጽ 121 በማንኛውም ጊዜ ዓቃቤ ሕጉ ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ ማንኛውንም ምስክር እንደገና አስጠርቶ እንዲሰማ የማድረግ መብት አለው፡፡

መልመጃ

1. **ትጉህ ዐቃቤህግ ስለሆኑ ምስክሮችን ችሎት አቅርበዉ ከማሰማትዎ በፊት አግኝተዉ ሊመረምሯቸዉ ፈቅደዋል፡፡ እነርሱም በክሱ እንደተነገረዉ ይመሰክራሉ ብለዉ ይጠብቃሉ፡፡ ሆኖም ምስክርነታቸዉ በፍጹም የተለየ ሆኖ አገኙት፡፡ እነዚህን ምስክሮች ምን እንዲያደርጉ ይመክሯቸዋል ወይም ያዝዟቸዋል?**
2. **ከላይ ባደረጉት ምርመራ ምስክሮቹ መርማሪዉ ፖሊስ በቃል ካነጋገራቸዉ በኋላ በወረቀት ላይ ጽፎ ያቀረበላቸዉን ነገር ሳያነብላቸዉ በአስቸኳይ ፈርመዉ እንዲሄዱ ስላደረጋቸዉ የማንበብ እድልም ሳያገኙ የምስክርነት ቃላቸዉ እንደሆነ በማመን ፈርመዉ መመለሳቸዉን እንጂ በፖሊስ ተመዘገበ የተባለዉን ምስክርነት አለመስጠታቸዉን አረጋግጠልዎ፡፡ እነዚህን ምስክሮች በተመለከተ የሚያደርጉት ምንድን ይሆናል?**
3. **ምስክርን ችሎት ከመቅረቡ በፊት መርምረዉ እንደክሱ ሊመሰክር እንደሚችል አረጋገጡ፡፡ በዚሁ ችሎት እንዲቀርብ ነግረዉ ያሰናብቱታል ወይስ ከዚህ ያለፈ ከርስዎ በኩል የሚፈጸም ነገር አለ? ከባልደረባዎ ጋር በመሆን በዚህ ረገድ አሉ የሚሏቸዉን አማራጮች ወይም አቀራረቦች መርምረዉ ያግኙ፣ ይዘርዝሯቸዉ፡፡**

ዐቃቤህግ ምስክር ስለጉዳዩ የሚያዉቀዉን እንዲነግረዉ በማድረግ ነገሩን በሚገባ ያስረዳ አያስረዳ እንደሆን ገምግሞ ይወስናል:: ሆኖም ለምስክር የሚያሳዉቀዉ ምንም ነገር የለም ግንኙነቱ ከምስክር ወደዐቃቤህግ ብቻ መረጃ የሚፈስስበት ነዉ ማለት አይደለም:: ዐቃቤህግ ከምስክር መረጃ የሚያገኘዉ በክስ መሰማት ጊዜ በዕዉን እንደሚደረገዉ አይነት የጥያቄና መልስ ሂደትን በመከተል ነዉ:: በዚህ መንገድ የተገመገመዉ ምስክር ብቁ መሆኑ ከታመነበት ምስክሩ ሊያዉቃቸዉ ስለሚገቡ ስለብዙ ነገሮች ዐቃቤህግ ሊነግረዉ እና ሊመረምር ይጠበቃል:: ምስክሩ የሚያዉቃቸዉ እና ከሚመሰክርባቸዉ ነገሮች ጋር የተያያዙ ምስጢሮች ካሉ እነዚህን መግለጽ ወንጀል መሆኑን እንዲያዉቅ ማድረግ ያስፈልጋል:: ከዚህ ጋር ተያይዞ እነዚህን ምስጢሮች እንዲገልጽ የሚያደርግ መስቀለኛ ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል በዚህ ጊዜ ምስክሩ ምስጢሩን እንዳይገልጽ በህግ የተከለከለ መሆኑን በማሳወቅ መብቱ እንዲጠበቅለት ፍርድቤቱን እንዲጠይቅ ማሳወቅ ተገቢ ነው:: በተጨማሪም ምስክሩ እንዲናገር የሚፈለገዉን ሳይሆን የሚያዉቀዉን እንዲናገር የሚጠበቅ መሆኑን ማስረዳት የግድ ይላል:: በተለይ ተቃራኒዉ ወገን በህግ ባለሙያ የሚረዳ ከሆነ

ባለሙያዉ ምስክሩን በተመለከተም ሆነ ስለሚመሰክረዉ ነገር ተዘጋጅቶ ሊቀርብና ምስክርነቱን ሊያፍረከርከዉ ስለሚችል አስቀድሞ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን ለማወቅ ምስክሩ ስለጉዳዩ የሚያዉቀዉን ሁሉ መዳሰስ ጠቃሚ ነዉ:: የምስክሩ ደካማ ጎኖች የሚያስከትሉትን ጉዳት መቀነስ ወይም ለማስቀረት የሚያስችል ዘዴ ለመፈለግ ይረዳል:: ምስክሩም በሚመሰክርበት ጊዜ የሚያዉቀዉን ስለሚናገር በመስቀለኛም ሆነ በሌላ ጥያቄ ጊዜ ነገሩን የማዘባረቅ ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማገዝ ያስችላል:: ለዚህ ሁሉ ምስክር የሚያዉቀዉን ነገር እንዲመሰክር መገፋፋት ወይም ማሳመን አንዱ የዝግጅት ስራ እንዲሆን ማድረግ ያስልጋል::

ምስክሩ ስለሚያዉቀዉ ነገር አስቀድሞ እንዲገልጽም ሆነ በምስክርነት ጊዜ የሚያጋጥሙት ነገሮች ግር እንዳይሉት የምስክርነት መስማት የሚመስል ጥያቄና መልስ ማካሄድ ስለነዚህ ማብራሪያ መስጠት (በተለይ በዋና ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ እንደማይጠየቅ ስለዚህ ነገሮችን ሁሉ በዝርዝር የሚናገረዉ ራሱ መሆኑን የዘለለዉ ነገር ሲኖር ዐቃቤህጉ ምን አይነት አጠያየቅ እንደሚከተልና ይህም የተዘለሉ ነገሮችን አስቦ ማስታወስና መመለስ እንዳለበት መጠቆሚያ መሆኑን ለምስክር ማሳወቅ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ሊያጋጥም ስለሚችለዉ ነገር ወዘተ ማስረዳት) ያስፈልጋል::

በዚህ መንገድ ታይቶ ለነገሩ ተገቢ የሆነ ምስክር በችሎት ቀርቦ ሲሰማ አዲስና የሚያደናግር ሁኔታ እንዳይገጥመዉ ሊብራሩለት የሚገቡ ሌሎች ነገሮች አለ:: የችሎቱን አቀማመጥ በተመለከተ የጉዳዩ ተዋንያን እንዴት እና የት እንደሚቀመጡ ወይም እንደሚቆሙ እነዚህ እነማን እንደሆኑ ምስክሩ ፍርድቤት ሲቀርብ ለምስክርነት ከመቀመጡ በፊት ስለሚፈጸሙ አሰራሮች (ለምሳሌ ስለመማል) ወዘተ ዐቃቤህግ ሊያስረዳዉ የሚገባዉ በዝግጅት ጊዜ ነዉ:: በተጨማሪም ምስክር ፍርድቤት ከመጣ በኋላ እስኪጠራ ድረስ የት ሊቆይ እንደሚገባዉ ዐቃቤህግ ሊገልጽለት ይገባል:: አንዳንድ ጊዜ በተግባር እንደሚታየዉ ምስክሮች በችሎት ተቀምጠዉ እያዳመጡ ተከሳሹ ተጠርቶ ወደመቆሚያ ሳጥኑ የሚገባበት ክሱ የሚነበብበት ወዘተ አጋጣሚ አለ:: ከዚህ በኋላ እነዚህ ምስክሮች ይሰማሉ:: ይህም የክሱን መስማት ሂደት ሚዛናዊነት ጥርጣሬ ዉስጥ እንዲገባ ያደርጋል:: ስለዚህ አንዳንድ ፍርድቤቶች ምስክሩ ክሱን እና የሚመሰክርበትን ነጥብ ምናልባትም የተከሳሹን ክርክር የሰማ ስለሆነ በዚህ ዕዉቀት ላይ ተመስርቶ ይሁን ወይም ስለሚያዉቀዉ ነገር በየትኛዉ

መንግድ እንደሚመሰክር አጠራጣሪ ስለሆነ ምስክሩ አይሰማም ብለዉ ይወስናሉ (ጸሃፊዉ በዳኝነት በሠራ ጊዜ ከነበረዉ ተሞክሮ)። ሌሎች ለነገሩ ክብደት ባለመስጠት ምስክርነቱን ይሰማሉ። ዞሮዞሮ ምስክርነቱ ሳይሰማ የሚቀር ከሆነ ክሱ ይጎዳል። የህዝብ ጥቅም ይጎዳል። ስለዚህ ምስክር ሲቀርብ የት ሊቆይ እንደሚገባዉ ሊያዉቅ ያስፈልጋል ይህም በዝግጅት ጊዜ የሚሆን ነዉ።

ከምስክሩ ሌላ ባለሙያው ከምስክሩ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን በተመለከተ ዝግጅት ማድረግ አለበት። ምስክሩ በኃላፊነቱ የተጻጻፋቸዉ ወይም የፈረመባቸዉ ሰነዶች ስለምስክሩ የተዘጋጁ የጉዞ ወይም የህክምና ሰነዶች (ደረሰኞችን ጨምሮ) በወንጀል ምርመራ ጊዜ የሰጣቸዉ ቃሎች ወዘተ ፍርድቤት ፊት ከሚሰጠዉ ምስክርነት ጋር የማይጣጣም ይዘት ሊኖራቸዉ እና ተቃራኒዉ ወገን ምስክሩን ለማስተባበል (ለኢምፒችመንት) ሊያዘጋጃቸዉ ይችላል። ስለዚህ እነዚህን አስቀድሞ ተመልክቶ በጉዳዩ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት በሚያመጣ መልኩ ከምስክርነቱ ጋር መቃረን አለመቃረናቸዉን መመዘንና ምስክሩን ለመጥራት ወይም ላለመጥራት መወሰን አለበት።

ምስክሩ ለጉዳዩ ገንቢ የሆኑ ነገሮችን የሚያስታዉስና አፍራሽ የሆኑ ነጥቦች ላይ አላስታዉስም የሚል ከሆነ ፍርድቤት ምስክሩን እየዋሸ ነዉ ብሎ ሊገምተዉ ስለሚችል ስለጉዳዩ በስፋት (አፍራሽ የሆነዉንም ጨምሮ) የሚያስታዉሱ ምስክሮችን መምረጥ ያስፈልጋል። የበለጠ የሚታመኑ ሰለሆነ። ምስክር ችሎት ስለሚቀርብበት ሁኔታ እንዲሁም በመሰማት ጊዜ ሊኖረዉ ስለሚገባ አቀራረብ ባለሙያው ሊያስታዉሰዉ ወይም ሊያሳዉቀዉ ይገባል።

የዓቃቤ ሕጉ ምስክሮች እንደክሱ ካስረዱ ተከሣሹ መከላከያውን እንዲያሰማ ይነገረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ መከላከያ እንዲሰማ ያዘዘበትን ምክንያት በዝርዝር መመዝገብ ሳያስፈልገው ተከሣሹ ስለተመሰከረበት መከላከያው እንዲሰማ የታዘዘ መሆኑን ብቻ በመመዝገብ ይህንኑ ለተከሣሽ ይነግራል፡፡ መከላከያ እንዲሰማ የሚደረገው የዓቃቤ ሕግ ምስክር በቂ ባይሆንም ነገሩን የበለጠ ለማጣራት ሳይሆን የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ በቂ ሲሆንና በዚህ ማስረጃ ላይ የማፍረሻ ማስረጃ ካልቀረበ ተከሣሹን ጥፋተኛ የሚያደርግ መሆኑን ፍርድ ቤቱ እርግጠኛ ሲሆን ብቻ መሆን አለበት፡፡ ተከሣሹ መከላከያ የለኝም ወይም ማቅረብ አልፈልግም ካለ

ይህንን በጽሑፍ እንዲያረጋግጥ ማስገደድ አስፈላጊ ሳይሆን ቃሉን ብቻ በመመዝገብ ውሳኔ መስጠት ይቻላል፡፡ ተከሣሹ ያለአግባብ ተከላከል ተባልኩ በማለት በዚህ ትዕዛዝ ላይ ብቻ ይግባኝ መጠየቅ አይፈቀድለትም፡፡ ሆኖም የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይህንን ነጥብ እንደቅሬታ ማንሳት ይችላል፡፡

የተከሳሹ የመከላከያ ምስክር መሰማት ሥርዓት የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራትን ያካትታል፡፡

- ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በመከላከያ ሊያስረዳ ያቀረበውን ማስረጃ በአፍጭሩ በመግለጽ መከላከያውን ይከፍታል፡፡ /አንቀጽ 142 /2/
- ቀጥሎም ምስክሮቹ ወይም በምስክርነት ቃላቸውን የሚሰጡት ልዩ አዋቂዎች እንዳሉ ቀርበው እንዲሰሙለት ያደርጋል፡፡
- ስለምስክሮቹ መሃላ መፈጸም፣ ስለ ምስክሮቹ ዝርዝርና የመሰማት ሂደት ከላይ በዓ/ሕጉ ምክሮች መሰማት ሂደት የተጠቀሱት ዋና ዋና ተግባራት እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

ተከሣሹ ከፈለገ የራሱ የመከላከያ ምስክር ሆኖ ቃሉን መስጠት ይችላል፡፡ ይህም በሆነ ጊዜ ከሌሎች ምስክሮች በፊት ቃሉን መስጠት አለበት፡፡ እውነትነቱ በፍርድ ቤት የሚመዘን ሆኖ የተከሣሹ ቀል እንደ መከላከያ ቃል ይቆጠራል፡፡

ተከሣሽ በራሱ በተሰጠው የመከላከያ ቃል ላይ የመስቀለኛ ጥያቄ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ በተከራካሪ ወገን አይፈተንም፡፡ ሆኖም ግን ፍርድ ቤቱ የማብራሪያ ጥያቄ ሊጠይቀው ይችላል፡፡ማንኛውም ምስክር ቃሉን ከመስጠቱ በፊት መማል ወይም እውነትን ለመናገር ማረጋገጥ አለበት፡፡ የመሃላ ፎርሙን ተከትሎ የፍርድ ቤት ሠራተኛ መሃላውን ያስፈጽማል፡፡ ፍርድ ቤቱ የምስክሩን ቃል ሲቀበል በመጀመሪያ ስለ ምስክሩ መለያዎችን ስሙን፣ አድራሻውን፣ ሥራውንና እድሜውን እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን ይመዘግባል፡፡ ምስክሮቹ መሃላ ከፈጸሙ በኋላ መጀመሪያ ዋና ጥያቄ፣ መስቀለኛ ጥያቄና ድጋሚ ጥያቄ ይጠየቃሉ፡፡

በዋናው ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ስለክርክሩ ፍሬ ነገር ተገቢ የሆኑትንና ምስክሩ በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ስለሚያውቃቸው ፍሬ ነገሮች ብቻ ነው፡፡ ተከሣሹ

/ጠበቃው ካልፈቀደ በቀር ዓ/ሕጉ መሪ ጥያቄ / Leading Questions/ መጠየቅ አይችልም፡፡

የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማ በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ውስጥ ያለውን የስህተት ቃል፣ የሚያጠራጥር ወይም እውነት ያልሆነውን ቃል ለፍርድ ቤቱ ለመግለጽና ለማጣራት በመሆኑ በዋና ጥያቄ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማይመራ አዲስ ነገር ማንሳት አይቻልም፡፡ ሆኖም መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡ ተከሣሹ ወይም ጠበቃው በመስቀለኛ ጥያቄ ያነሳዉን ነገር ለማጣራት ብቻ ዓ/ሕጉ ድጋሚ ጥያቄ መጠየቅ የሚችል ሲሆን በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ከተነሳው ጭዳይ ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ነገር በድጋሚ መጠየቅ አይችልም፡፡ በሕግ በግልጽ ካልተፈቀደ በስተቀር የተከሳሽ የጥፋተኝነት ታሪክ ከፍርድ በፊት ስለማይገለጽ ይህን የሚያመላክቱ ጥያቄዎች ለምስክሩ መቅረብ የለባቸውም /አንቀጽ 138/ ዓ/ሕግ ያቀረበው ምስክር ክሱን በሚጎዳ ሁኔታ ቢመሰክር ዓ/ሕጉ ይህ ቃል እንዳይመዘገብ ምስክሩም ቃሉን መስጠት እንዲያቆም ፍርድ ቤቱን መጠየቅ አይችልም፡፡ ጥያቄው ቢቀርብም ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ሳይቀበል የምስክሩን ቃል መመዝገብ አለበት፡፡ ዓ/ሕጉ ጥያቄውን ቢያቆምም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሩን መመርመር መቀጠል ይችላል፡፡ የምስክሮች ቃል ሲመዘገብ ዋና ጥያቄ፣ መስቀለኛ ጥያቄ እና ድጋሚ ጥያቄ ተብሎ መከፋፈልና እያንዳንዱ የጥያቄ ክፍል የሚጀምርበት እና የሚያልቅበት ስፍራ በመዝገቡ ውስጥ እንደለይ ተደርጎ መጻፍ አለበት፡፡ ዓ/ሕጉ ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ማፍረሻ ማስረጃ አስፈላጊ ሳይሆን ተከሣሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ እና ማስረጃው በቂ ሆኖ ሳያገኘው የቀረ እንደሆነ ተከሣሹ በነፃ እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቱ ያዛል፡፡ /ቁ.141/ ትዕዛዙ እንደመጨረሻው ፍርድ ዝርዝር የያዘ ሳይሆን ዓ፣ሕጉ እንደክሱ አላስረዳም የተባለበትን ምክንያት በአጭሩ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

መልመጃ

1. ምስክር ለማሰማት ዐቃቤህግ ከላይ በተመለከቱት መንገዶች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ የክርክር መክፈቻ መበለጫ ይሰጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ተዘዉትሮ የሚታወቀዉ የጭብጥ አሰጣጥ ´ምስክሮች እንደክሱ ያስረዳሉ´ የሚለዉ ነዉ፡፡ ይህ ምን ያህል ተገቢና በቂ ነዉ?

2. ምናልባት የዐይን ምስክር የተባሉትን በተመለከተ ይህ መግለጫ በቂ ነዉ ሊባል ይችል ይሆናል:: ከዚህ ዉጪ የተጠራዉን ምስክርና ሰነድ ሁሉ በደፊናዉ እንደክሱ ያስረዳል ብሎ መግለጫ መስጠት በተራ አስተሳሰብ እንኳ ለመቀበል የሚያስቸግር ነዉ:: ቢያንስ አንድን ነገር በተመለከተ ሁሉም ሰዎች በእኩል ጊዜና ቦታ እኩል አስተዉለዉ እኩል መረጃ ሊኖራቸዉ አይችልም:: ስለዚህ በተቻለ መጠን የክስ መክፈቻ መግለጫ ሲቀርብ በደፊናዉ ከሚሆን ዘርዘር ያለ ቢሆን ለሁሉም ወገን ጠቃሚ ነዉ:: ፍርድቤትም ዐቃቤህግ ድፍንፍን ያለ ሳይሆን ግልጽና ተጨባጭነት ያለዉ መግለጫ እንዲሰጥ መገፋፋት አለበት?

ምስክሮች ከቀረቡ በኋላ በሚሰሙበት ጊዜ የዐቃቤህግ ዋናዉ ተግባር ምስክሮችን በመጠየቅ ማስመስከር ነዉ:: ይህ ምስክርነት ክሱን እንዲያስረዳ ስለሚፈለግ የጥያቄዉ አመራርና አካሄድ ክህሎትን የሚፈልግ መሆኑ ግልጽ ነዉ:: ዐቃቤህግ ክሱን ለማስረዳት የራሱን ምስክሮች አቅርቦ ማሰማት ብቻ ሳይሆን የተከሳሽን ምስክሮች በመጠየቅም የማስመስከር ተግባር አለዉ - መስቀለኛ ጥያቄ:: ለዚህም ክህሎት ያስፈልጋል:: በዚህ ረገድ ብዙ ሊባል የሚችል ቢሆንም ከሃገራችን ህግና የአሰራር ልማድ አኳያ አግባብነት ያላቸዉን ህጎችና የምስክር አጠያየቅ ቴክኒኮችና አወቃቀር እንመለከታለን::

7.2 የምስክር አጠያየቅ ቴክኒኮችና አወቃቀር

በዚህ ክፍል የቃል ማስረጃ አቀራረብና ምሰክር መፈተን ከሃገራችን ህግና የአሰራር ልማድ አኳያ አግባብነት ያላቸዉን የምስክር አጠያየቅ ቴክኒኮችና አወቃቀር እንመለከታለን:: ዋና ጥያቄ፣ መስቀለኛ ጥያቄና ድጋሚ ጥያቄ አኳያ ምን መምሰል እንዳለበት እናያለን፡፡

7.2.1 ዋና ጥያቄና የዋና ጥያቄ ይዘት (Examination inchief)

ተከራካሪው ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚያቀርባቸው ምስክሮች ዋና ጥያቄ መጠየቅ ግዴታ አለበት፡፡

> `The **Direct Examination** or **Examination-in-Chief** is one stage in the process of adducing evidence from witnesses in a court of law. Direct examination is the questioning of a witness by the party who called him or her, in a trial. Direct examination is usually performed to elicit evidence in support of facts which will satisfy a required element of a party's claim or defense.`

የተከራካሪውን ምስክር ሊሰማ በቀረበበት ጊዜ ምስክሮቹ ስለመጡበት ጉዳይ ለፍርድ ቤቱ ያስረዱ´ የሚል (ጥያቄ ሳይሆን ትዕዛዝ የመሰለ) ሃሳብ ከዐቃቤህግ መቅረቡ የተዘወተረ ነዉ:: አንድ ምስክር ፍርድቤት የሚቀርብበትን ጉዳይ አስመልክቶ እጅግ በርካታ ነገር ሊያዉቅ ይችላል:: ከዚህ ሁሉ የቱ መቼ ለፍርድቤቱ ሊነገር እንደሚገባ ምስክሩ ሊያዉቅ አይችልም ዐቃቤህጉ ለነገሩ አግባብ ያላቸዉን ነጥቦች ተንተርሶ ጥያቄ እያነሳ ካልመራዉ በቀር:: ሌላዉ ቀርቶ ከየት እንደሚጀምርም ሊቸገር ይችላል (በርግጥ ይህ ሁሉ ለሙያ ምስክሮች ላያስቸግር ይችላል):: ስለዚህ ምስክሩ ስለሁኔታው እንዲያስረዳ ስለሚያውቀው ፍሬ ነገር በነፃነት እንዲገልጽ ዕድል ማግኘት ይገባዋል፡፡ ይሁን እንጂ ምስክሩ የሚናገራቸው ሐሳቦች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ክስ ከቀረበበት ጉዳይ ተያያዥነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ምስክር አስቀድሞ የሚያውቃቸውን ፍሬ ነገሮች በማስታወስ መግለጽ እንጂ ምስክሩ ያቀረበለትን አዎ ወይም አይደለም የሚል መልስ መስጠት የለበትም፡፡

መልመጃ

በዋና ጥያቄ ጊዜ *መሪ* ጥያቄ የተከለከለ ነዉ:: ነገር ግን ይህ ክልከላ የሚሰራዉ ሌላኛዉ ተከራካሪ ሳይፈቅድ ከቀረ ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ ቁ. 137(2)):: ስለዚህ ተከሳሹ ወይም ጠበቃዉ ካልተቃወመ ዐቃቤህግ በዋና ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል? ፍርድቤት በራሱ አስተያየት መሪ ጥያቄ መጠየቅን ሊከለክል አይችልም ማለት ነዉ?

ይህ ከሆነ ከሳሽ ወገን በምስክር አፍ ራሱ *መመስከር* ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ሲያቀባብል ወይም ጥይት ሲቶክስ አይተሃል አይደል? የሚለውን ጥያቄ “አዎ” የሚል መልስ ከተሰጠ ከሳሽ ወገን የሚፈልገውን ምስክርነት በቀላሉ ያገኛል ማለት ነው፡፡ መሪ ጥያቄ ተነስቷል ብሎ መቃወሚያ ማቅረብ በፍርድቤቶቻችን የተለመደ የክስ መስማት ሂደት አጋጣሚ ነዉ:: ዋና ከሚባሉት የማስረጃ መቃወሚያዎች አንዱ መሪ ጥያቄን የሚመለከት ነዉ:: ነገር ግን ማስረጃን መቃወም የፍርድቤትን ዉሳኔ የሚጠይቅ በመሆኑ ዋናዉ ክርክር እየተቋረጠ የሚቆይበትን ጊዜ ያበዛል:: ስለዚህ የማስረጃ ተቃዉሞ ሲነሳ ይህ ነገር ከግምት ሊገባ የግድ ነዉ:: ተከራካሪውም በሌላዉ ወገን የሚነሳዉ ጥያቄ በርግጥ መሪ ነዉ አይደለም የሚለዉን በፍጥነት የመለየት ብቃት ሊኖረዉ የሚችለዉ ይህን ልዩነት ጠንቅቆ ሲያዉቅ ነዉ::

የአንድ ምስክር ታማኝነት በምስክሩ የህይወት ታሪክ፣ የምስክርነት ቃል ይዘትና የምስክርነት ቃሉን እንዴት እንደሰጠ የሚወስን ይሆናል፡፡ በበርካታ አገሮች ምስክሩ ጥሩ ስምና ዝና ያለው ከወንጀል ተግባር የፀዳ መሆኑ ከታወቀ የሚሰጠው ምስክርነት ታማኝ ይሆናል፡፡ ምስክሩ የሚሰጠው ቃል ከሳሽ ወገን በሚጠይቃቸው ነጥቦች የተመሰረተ በመሆኑ ለምስክር የሚያቀርበው ዋና ጥያቄ በጭብጥ ለተያዘው ጉዳይ የሚያስረዳ መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል፡፡

መልመጃ

1. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.137(1) ...በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ምስክሩ ስለሚያዉቃቸዉ ፍሬ ነገሮች... በሚል የተመለከተዉ ዐቃቤህግ ምስክሩን የስሚስሚ ምስክርነት ሁልጊዜ እንዲጠይቅ ለመፍቀድ ነዉ ወይስ በተለየ ሁኔታ የሚፈቀዱ የስሚስሚ ምስክርነት ሁኔታዎችን በህጉ ዉስጥ ለማካተት የታሰበ ነዉ?
2. በተለምዶ የግምት (ኦፒኒየን) ምስክርነት የምንለዉን በተመለከተም እንዲሁ ሰዉ ግምቱን እንዲመሰክር አይፈቀድም የሚያዉቃቸዉን ፍሬነገሮች እንጂ:: ምናልባት የሙያ ምስክሮችን በተመለከተ ይህ አይሰራ ይሆናል?
3. ባለሙያ ያልሆኑ ምስክሮች በቀረቡበት ጊዜ ሁሉ ግምትን የሚመለከት ማስረጃ እንዲሰጡ መጠየቅ አይቻልም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ ይቻላል? ለምን? ፍጥነትን ርቀትን መጠንን ወዘተ በተመለከተ ለማወቅ ወይም ለማስመስከር ብንፈልግ በግምት እንዲነገር ከመጠየቅ ልንከለከል ይገባል?

በጥያቄ አቀራረብ ዘዴነት የዋና ነጥቦችን (ጭብጦችን) ምስክርነት እንዳይበታተን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ዋና ጥያቄ ሲካሄድ ተከራካሪው ወደዋናዉ ጉዳይ ከመግባቱ በፊት ዙሪያዉምዉም መሄድ የለበትም:: የመግቢያና መሸጋገሪያ ጥያቄዎች ለምስክሩ የፍርድ ቤት ሁኔታዎች በሚገባ እንዲያገናዝብ ያግዘዋል፡፡ የመግቢያ ጥያቄው የሚፈለገውን መልስ ለመስጠት እንደመንደርደሪያ የሚያገለግልና ፍርድ ቤትም ምን እንደሚጠብቅ ፍንጭ የሚሰጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል የመሸጋገርያ ጥያቄዎች ከአንድ ምዕራፍ ወደ ሌላ ምዕራፍ ስትሸጋገር የምስክሩ ቃል ተቆርጦ እንዳይቀር እንደድልድይ የሚያገለግል ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ የተለያዩ ምስክሮች የሚያቀርብ ከሆነ ለምሣሌ የዓይን፣ አካባቢ፣ ስለኤግዚቪት የሚገልጽ አንዱ ከሌላው እንዴት እንደሚገናኝ ማሳየት አለበት፡፡

ምስክሩ የኋላ ታሪኩ ምን እንደሚመስል በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ተሳትፎ፣ ቅንነት፣ ታማኝነት ማሣየት ለሚሰጠው ቃል ተቀባይነት ወሣኝ ነው፣ በክሱ የተጠቀሰውን ጉዳይ መቼ፣ የትና እንዴት እንደተፈፀመ ለፍርድ ቤት በሚያስረዳ መልኩ መቅረብ አለበት፣ ፍርድ ቤቱ ምን እንደተፈፀመ በሚሰማበት ጊዜ ጉዳዩ አሁኑኑ እንደተፈፀመ በስሜት እንዲከታተለው አንኳር ነጥቦች ማሳየት፣ የተረጋጋ አነጋገር፣ ሥርዓት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም፣ አሁን ጉዳዩን እንደተፈፀመ በሚመስል መልኩ እንዲገልፀው መደረግ አለበት፣ የዐቃቤ ሕግ/ የተከሳሽ ምስክር በዋናው ጥያቄ የመምራት ጥያቄ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ምስክሩ ራሱ የሚያውቃቸው ፍሬ ነገሮች ከመመስከር ይልቅ ከሳሽ ወገን የሚፈልገውን መልስ እንዲመልስ የሚያስገድደው በመሆኑ ነው፡፡ የምስክሩ ታማኝነትና የማስረዳት አቅም ጥያቄ ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ ይገባል፡፡ ዐቃቤ ሕግ የምስክሩን ታማኝነትና ብቃት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ገደብ የሌለው ጥያቄ መጠየቅ የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ እንደመግቢያ የሚያገለግሉ፣በህፃናት ላይ የሚነሱ፣ ለአስጠቂ ምስክር በሚመለከት መሪ ጥያቄ/ይፈቀዳል፡፡

የመግቢያ ጥያቄዎች ከተነሱ በኋላ ወደዋናዉ ጉዳይ ገብቶ ለነገሩ አንኳር የሆኑትን ጥያቄዎች መጀመር አለበት:: የዋና ጥያቄ ዓላማ የቀረበዉን ክስ ማስረዳት የሚችሉትን ነገሮች ማቅረብ በመሆኑ የጉዳዩ አንኳር ሃሳቦች ወደኋላ የሚቆዩበት ምክንያት አይኖርም:: ዋናዋና ነጥቦች በሚመሰከሩበት ጊዜ ዝርዝር ነገሮችን ወይም ማብራሪያዎችን ፍለጋ ጣልቃ በመግባት ጥያቄ ማንሳት የምስክርነቱን ፍሰት ያስተጓጉላል ክብደቱንም ይቀንሳል:: ስለዚህ ማብራሪያዎችን ወደኋላ በማቆየት መጠየቅ የሚቻል ሆኖ ዋና ነጥቦች ላይ የሚቀርበዉን ምስክርነት ሳይቆራረጥ ለማቅረብ ደጋግሞ ጣልቃ እየገቡ ማብራሪያዎችን አለመጠየቅ ይመረጣል::

በተመሳሳይ ሁኔታ የአካባቢ ማስረጃ በአንድ ላይ ሳይበታተን ሲቀርብ የበለጠ ክብደት ስለሚኖረዉ እና ይዘቱንም ለመረዳት ስለሚያመች በነዚህ ማስረጃዎች መሃል ሌላ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ ጣልቃ ሳይገባ ምስክርነቱ እንዲሰማ ማድረግ ያስፈልጋል:: አጫጭር ጥያቄዎችና ምስክርነትን ስለመደጋገም፡- በዋና ጥያቄ ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎች ምስክሩ ነገሩን የማስረዳት ሰፊ ዕድል የሚሰጡ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ምክንያቱም ነገሩን የሚያስረዳዉ ምስክሩ እንጂ ባለጉዳዩ ወይም ጠያቂዉ አይደለም:: ስለዚህ ጥያቄዎቹ አጫጭር ቢሆኑ ይመረጣል::

አንዳንድ ጊዜ ለክርክሩ ጠቃሚ የሆኑ ፍሬነገሮች ላይ ትኩረት እንዲደረግ መፈለግ አይቀርም:: ስለዚህ የፍርድቤቱን አትኩሮት ወደነዚህ ነጥቦች ለመሰብሰብ እነዚህ ነጥቦች ተደጋግመዉ እንዲነገሩ ማድረግ ተገቢ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ይህን ስናደርግ ጥያቄዎቻችን ሊደጋገሙ አይገባም:: ተቃዉሞ ሊነሳበት ወይም ችሎቱን ሊያሰለች ይችላል:: ስለዚህ ተፈላጊዉን ነጥብ የሚመለከቱ ሌሎች ጥያቄዎችን በማንሳት በተለያየ መንገድ ተደጋግሞ እንዲመለስ ማድረግ ይመከራል::

ብዙዉን ጊዜ ምስክር የሚሆኑ ሰዎች የህግ ሙያ ወይም መሰረታዊ የህግ ዕዉቀት የላቸዉም:: ስለዚህ ጥያቄዎቻችን በተራ የዕለት-ተዕለት መግባቢያ ቋንቋ ሊቀርብ ይገባል:: የህግ ሙያ ቋንቋ በጥያቄዎች ዉስጥ ሊካተት አይገባም:: ምስክሩን ግራ ያጋባል:: በአንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ መጠየቅ ጠቃሚ ነዉ:: ምስክሩ በርካታ ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ከተጠየቀ መልሱ ላይ ከፊሉን ሊዘነጋ ይችላል:: ስለዚህ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ከተፈለገ በየተራ ሊጠየቁ ይገባል እንጂ ተነባብረዉ መሆን የለበትም::

በአጠቃላይ ዋናው ጥያቄ አጭርና ግልጽ መሆን አለበት ምስክሩ ወደ ዋናው ጉዳይ በቀጥታ እንዲገባ የሚያስችል ዘዴ መከተል ይገባል፡፡ በዋናው ጥያቄ መካተት ያለባቸው ነጥቦች ከተገለጹ በኋላ ወዲያውኑ ማቆም ይገባል፡፡ ዋናውን ጥያቄ በሥርዓት ማደራጀት ለምስክሩ የሚጠየቁ ፍሬ ነገሮች በቅደም ተከተልና ምክንያታዊ በሆነ አቀራረብ ማዘጋጀት ይገባል፡፡ የትኛው ጉዳይ ከየትኛው ፍሬ ነገር በኋላ መቅረብ እንዳለበት መወሰን ምስክርነቱ የጉዳዩን አፈፃፀም ወለል አድርጐ ያሳያል፡፡ በዚህ መሠረት የምስክሩ የህይወት ታሪክ/ምስክሩ ማን እንደሆነ/፣ ምን እንደተፈፀመ፣ እንዴት እንደተፈፀመ፣ ኤግዚቪቶችና የደረሰውን ጉዳት ምን እንደሆነ በሚያሣይ መልኩ መደራጀት አለበት፡፡ ዋናው ጥያቄ በቅድመ ሙግት ጊዜ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ምስክሩ ቃሉን ሲሰጥ ሁኔታውን እንዲያስረዳ ዕድል መስጠትና ግልጽ ያልሆኑ፣ ትንተና የሚጠይቁ ዐረፍተ ነገሮች ከመጠየቅ መቆጠብ አለብን፣ ምስክሩ ጉዳዩን ሲያስረዳ ኤግዚቪቶችን፣ ፎቶግራፎች፣ ዲያግራሞች፣ ጠበንጃ እና ሌሎችም በማንሳት ከሁኔታው ያላቸው ግንኙነት እንዲያስረዳ ዕድል ሊሰጠው ይገባል፣ ፍርድ ቤት ውስጥ የፍርሃት ድባብ ሊሰማው ስለሚችል ስለፍርድ ቤት አጠቃላይ ገፅታ፣ ያለፍርሃትና ድንጋጤ ነፃ ሆኖ ቃሉን እንዲሰጥ ማበረታታት ይገባል፡፡ በፖሊስ ጣቢያ ምስክርነት የሰጠበትና ፍርድ ቤት የቀረበበት ጊዜ ረጅም ከሆነ የማስታወስ አቅሙ ሊቀንስ ስለሚችል የማንበብ ዕድል ሊሰጠው ይገባል፡፡ ምስክሩን

የማዘጋጀት ሥራ በመጀመሪያ መሠራት ያለበት ወሣኝ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ምስክሩ ማስጠናት ፍትሕ ሊያዛባ ይችላል። በመሆኑም በጥንቃቄ መሠራት አለበት።

7.2.2 መስቀለያ ጥያቄ (cross-examination)

መስቀለያ ጥያቄ መጠየቅ መብት ነው።

> "**cross-examination** is the interrogation of a witness called by one's opponent. It is preceded by direct examination and may be followed by a redirect.``

ብዙዎች እንደሚስማሙበት የአንድ ማስረጃ እውነተኛና ትክክለኛ መሆን ዋነኛ መመዘኛ በማስቀለያ ጥያቄ የተፈተነ እንደሆነ ብቻ ነው። በእሳት ያልተፈተነ ወርቅና በመስቀለያ ጥያቄ ያልተፈተሸ ምስክርነት ተቀባይነት እንደማይኖረው ብዙዎች ይስማሙበታል። መስቀለያ ጥያቄ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው መብት ስለሆነ ፍርድ ቤቶች በዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ ገደብ ሊጣሉ አይገባም። መስቀለያ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ይህንን መብት የሚገድብ ተግባር መፈፀም የለባቸውም።

መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ጉዳትም ጥቅምም ስላለው በጥንቃቄ መመርመርና መዘጋጀትን ይጠይቃል፣ መስቀለያ ጥያቄ እንደ ቼዝ ጨዋታ ይታያል። ዐቃቤ ሕግ መስቀለያ ጥያቄ ሲያቀርብ መልሱ ምን እንደሚሆን ማወቅ ይጠበቅበታል። መልሱ የማይታወቅ መስቀለያ ጥያቄ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። መስቀለያ ጥያቄ በቅድመ ሙግት ጊዜ በጥንቃቄ መመረጥ እንዳለበት ይታመናል። ይሁን እንጂ ምስክሩ ዋናው ጥያቄ ሲጠይቅ የሰጠውን ምስክርነት መመዘን ደግሞ ሌላ ወሣኝ ሥራ ነው። ስለዚህ መስቀለያ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወስ ይገባል።

ሁሉም ምስክሮች ጉዳዩን ማስተባበል ስለማይችሉ የተሰጠውን የምስክርነት ይዘት በጥልቀት መፈተሽ ይገባል፣ ምስክሩ አስፈላጊና ከፍተኛ ጫና የፈጠረ ከሆነ መስቀለኛ ጥያቄ አስፈላጊ ነው፣ ምስክሩ የሰጠው ቃል ታማኝና መሠረታዊ ካልሆነ ወይም ከሌሎች ምስክሮች የሚቃረን ቃል የሰጠ እንደሆነ መስቀለኛ ጥያቄ ከመጠየቅ መቆጠብ ይገባል፣ በተከሳሽ ወይም በጠበቃውን ስሕተት ምስክሩ አንኳር ነጥቦች የዘለለ እንደሆነ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ አይገባም። ምክንያቱም ምስክሩ የፈፀመውን ስሕተት በማረም ሊመሰክር ስለሚችል ሁለተኛ ዕድል መስጠት የለብንም፣ ወይም በተመረጡ ጉዳዮች ብቻ መሪ ጥያቄ

በማቅረብ መሞከር ይሻላል፣ ክሱ ደካማ ከሆነ መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ የበለጠ ፍሬያማ ውጤት የሚገኝ መሆኑና አለመሆኑን በሚገባ መመርመር ከአንድ ተከራካሪ ወገን የሚጠበቅ ምስክር የመፈተኛ አቅም ነው፡፡

የመስቀለያ ጥያቄ አደገኛ ሰይፍ ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ሊጠቀምም ሊጐዳም ይችላል፡፡ ስለዚህ ዓላማ የሌለው መስቀለኛ ጥያቄ ውጤቱ መጥፎ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሁኑም በዋና ጥያቄ የተሰጠውን ቃል አንተን በሚጠቅም መልኩ ግንዛቤ እንዲወሰድበት፣ የተከራካሪ ወገን ክስና ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው ማድረግ፣ ምስክሩ ታማኝ አለመሆኑን ማሣየት፣ ምስክሮች የሰጡት ቃል አንዱ ከአንዱ የሚጋጭ መሆኑን ማሳየት፣ ምስክሩ ጠያቂውን በሚጠቅም መልኩ አዲስ ሐሳብ እንዲገልጽ ሁኔታዎች መፍጠርን የመሳሰሉትን መሰረታዊ ጥበቦች በጥንቃቄ ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡
ዐቃቤ ሕግ መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቅ በመጀመሪያ ምስክሩ ለራሱ ጥቅም የሚቀይርበት ዘዴ መፍጠር አለበት፡፡ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ዐቃቤህግ የሚፋጠጠዉ ከተከሳሹ መከላከያ ምስክሮች ጋር ነዉ:: በዚህ ጊዜ በቀጥታ ከመዋሸት አንስቶ ለዐቃቤህግ ክስ ገንቢ የሆኑ ወይም የተከሳሹን ክርክር የሚያፈርሱ ፍሬነገሮችን አላስታዉሰም እስከማለት የሚደፍሩ ምስክሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ዋናዉ የዐቃቤህግ ግብ ይህን ድፍረት ማዳከምና በህግና በሥነምግባር ደንቦች በታወቁ መንገዶች ሃቆችን ማፍረጥረጥ ይሆናል:: ይህም የተባለዉን ሃቅ ከምስክሩ ማግኘትን የሚመለከት ነዉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታወስ የሚገባዉ ነገር እንደየተመልካቹ አንድ ሃቅ በተለያየ አቅጣጫ ሊተነተን የሚችል መሆኑ ነዉ:: ከጊዜ ማለፍ ለነገሩ ከሚኖር የተዛባ አመለካከት ወይም ከጥቅም ጋር ከተያያዘ አቀራረብ የሰዎች አተያይ በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ምስክሩ ታማኝ አለመሆኑን ለመግለጽ የምንጠቀምበት አገላለጽ ምስክሩ ሊያስቆጣው ስለሚችል በጥንቃቄ ማካሄድ አለበት፡፡ ምስክሩን ስንጠይቀው ሰብአዊ ክብሩ በመጠበቅ በፍሬ ነገሮች ላይ በማትኮር ብቻ መሆን አለበት፡፡መስቀለያ ጥያቄ በጣም አጭርና ጥቂት መሆን አለባቸው፡፡ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች መዳሰስ የሚችሉ ከ3-4 የማይበልጡ ጥያቄዎች ብቻ በማዘጋጀት መጠየቅ፣ ጠንካራና አስተማማኝ የምትለውን ጥያቄ በመጀመሪያና ማጠቃለያ አድርገው የመጀመሪያና የመጨረሻ ጥያቄዎች የማያወላዱ ከሆነ የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፣ መልስ የሚሰጠው ምስክር የመጨረሻው ውጤት መገመት የለበትም፡፡ ጥያቄዎች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ከቀረቡ ምስክሩ

የጥያቄው ዓላማ ሊገባው ስለሚችል የሚፈለገውን ውጤት ላያገኝ ይችላል፣ የመስቀለያ ጥያቄ አስፈላጊነት፣ ስልት መመሪያዎችና ሌሎች ጠቃሚ ሐሳቦች በዕለት ተዕለት ሥራችን ተግባራዊ ካደረግነው ሙግት የማሸነፍ ብቃት ይኖረናል፡፡ የመስቀለያ ጥያቄ የማዘጋጀት ክህሎት በሚገባ ካልዳበረ ሙግት የማሸነፍ አቅማችን ደካማ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጉዳይ ከማንኛውም ነገር በላይ ትኩረት መስጠት ያሻል፡፡ በተለያየ መንገድ ተደልለውና ተገዝተው የሚመጡ ምስክሮች ለማስተባበል ሁነኛው መሣሪያ መስቀለያ ጥያቄ ነው፡፡ የመስቀለያ ጥያቄ በሚታሰብበት ጊዜ የሚከተሉት ነጥቦች በተጨሪም መዳሰስ ይገባል፡፡ የመስቀለያ ጥያቄ እውነት ለማውጣት ወሣኝ መሣሪያ መሆኑን ማመን፣ መስቀለያ ጥያቄ የተቃራኒ ወገን ምስክሮች ታማኝነት የሌላቸው መሆኑ አድልዎ የሚንፀባረቅባቸው መሆኑን በማሣየት ውድቅ እንዲደረግ የሚያስችል መሆኑ፣ መስቀለያ ጥያቄ አስፈላጊ በሆኑ የመከራከሪያ ነጥቦች ማተኮር አለበት፡፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በጭብጥ ከተያዘው ጉዳይ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማሣየት፣ የመስቀለያ ጥያቄ አግባብነትና ዓላማ ዐቃቤ ሕግ/ተከሳሽ እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡ ዓላማውና አግባብነቱ አስቀድሞ ከታወቀ መቃወሚያ እንዲነሳበትና ውድቅ እንዲሆን ስለሚደረግ ዓላማውን ይስታል፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቶች የምትጠይቀው ነገር ዓላማው ምንድነው? ብለው በመጠየቅ ማጨናገፍ አይገባቸውም፡፡ የመስቀለያ ጥያቄ ዋነኛ ስልት የጥያቄው ዓላማ ሚስጥር እንደሆነ እስከ ፍፃሜው ድረስ መጠበቅ ይገባል፡፡ ዐቃቤ ሕግ የሚናገራት እያንዳንዷ ቃል ሚስጥር ያረገዘች በጥልቅ እውቀትና የሕግ ትንተና ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ ፍርድ ቤቶች ምክንያት እየፈጠሩ መስቀለያ ጥያቄ መገደብ እንደሌለባቸው እንደ መርህ ወስደን ከሙያው አንፃር ሲታይ ምንም ግንኙነት የሌላቸውን ጥያቄዎች ግን የመቆጣጠር ሥልጣን አላቸው፣ መስቀለያ ጥያቄ በቂ ዕውቀትና ተከታታይነት ያለው ልምምድ ያደረገ ባለሙያ ሁነኛ መሣሪያ ነው፡፡ ሐሰተኛ ምስክሮችን ለመለየት የመስቀለያ ጥያቄ በሚጠየቅበት ጊዜ ምስክሩን ትኩር ብሎ መመልከት ይገባል፡፡ ይህ ከሰውየውና ከአእምሮው ግንኙነት ለመፍጠር አመቺ ዕድል ነው፡፡ ሰውየውን ትኩር ብሎ በማየት እውነተኛ መሆኑን አለመሆኑን፣ ጥላቻ ያለው መሆኑና አለመሆኑን መለየት ይቻላል፡፡ ስለዚህ እንደምስክሩ ባህሪ የተረጋጋ ምስክር ከሆነ ረጋ ማለት፣ ተንኮለኛ ከሆነ የበለጠ ብልጥ መሆን፣ ታማኝ ከሆነ ቅንነት ማሳየት፣ ኃይለኛና ውሸታም ከሆነ ደግሞ ነጎድጓድ መሆን ይገባዋል፣ ጥያቄዎች የሚያሻሙ ከሆኑ የሚሰጠው መልስም የሚያሻማ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የሚጠየቁ

ጥያቄዎች ግልጽ፣ አጭርና የማያሻሙ መሆን አለባቸው፣ የመስቀለያ ጥያቄ እንደ ቼዝ ጨዋታ መታየት አለበት፡፡ የቼዝ ተጫዋች ውጤቱ ምን እንደሆነ ያውቃል፡፡

ለዚህም ቀደም ሲል እንደተመለከትነዉ ዝግጅት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ችግሩ አሁን ባለዉ የአሰራር ልማድ ስለሌላዉ ወገን ምስክር ቃል መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነዉ፡፡ ስለዚህ የተቃራኒ ወገን ምስክር በተለይም የተከሳሽ ምስክር በፍርድቤት ሲቀርብ ምን እንደሚመሰክር አስቀድሞ ማወቅ አይቻልም፡፡ እንዲያዉም በመደበኛዉ አሰራር የተከሳሽ ማስረጃ ምንነት የሚታወቀዉ ክርክሩ ወደፊት ገፍቶ የዐቃቤህግ ማስረጃ ታይቶና ተሰምቶ ካበቃ በኋላ ነዉ፡፡

መልመጃ

1. *በአንድ ችሎት የቀረበዉ የወንጀል ክስ ተሰምቶ ሲያበቃ ተከሳሹ ወንጀሉን አልፈጸምኩም አለ፡፡ ፍርድቤቱም ተከሳሹን ወንጀሉን አልፈጸምኩም ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እንዲያብራራ ጠየቀዉ፡፡ እንዲህ አድርጎ ለማጣራት ያስገደደዉ ወንጀል አልፈጸምኩም የሚባልበት ብዙ ምክንያት ስላለ እዉነት ከሆነ የትኛዉ ምክንያት እንደሆነ ለመለየት ነዉ፡፡ በዚህ ማጣራት መሰረት ተከሳሹ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ያለዉ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በወንጀሉ ቦታ ሳይሆን በሌላ ቦታ ስለነበረ መሆኑን ገለጸ፡፡ ይህን የፍርድቤቱን አቀራረብ እንዴት ይገመግሙታል? ተገቢ አይደለም ይላሉ? ለምን?*

2. *በሌላ በኩል ተከሳሹ ከላይ ያቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ፍርድቤቱ ዐቃቤህግን ምን እንደሚያመለክት ሲጠይቀዉ ተከሳሽ ለዚህ ክርክሩ የሚያቀርበዉን የማስረጃ አይነትና ይዘት ለፍርድቤቱ ያስመዝግብልኝ ብሎ አመለከተ፡፡ ይህ የዐቃቤህግ አካሄድ ምን ያህል ተገቢ ነዉ? ከባልደረባዎ ጋር ይወያዩበት፡፡*

ፍርድቤቶች የዐቃቤህግ ምስክሮችን ምስክርነትም ሆነ የተከሳሽን ምስክሮች ምስክርነት ይዘት የሚገልጽ ማመልከቻዎች ግራ ቀኙን አያለዋዉጡም፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የሙስና ጉዳዮችን በሚያዩ ችሎቶች ያለዉን አሰራር ስንመለከት በተለዩ የሥነሥርዓት ድንጋጌዎች መሰረት ዐቃቤህግ የምስክሮችን ቃል ይዘት በመግለጫ ለተከሳሽ እንዲያደርስ ይደረጋል፡፡

በተመሳሳይ ተከሳሽም ስለማስረጃዉ ቢያንስ ዝርዝር እንዲያቀርብ ይደረጋል:: ይህ ሁሉ የክሱን ዋና ጉዳይ ማየት ከመጀመር በፊት የሚከናወን ነዉ:: ስለዚህ ይህ ማስረጃን የተመለከተ የመግለጫ መለዋወጥ ለህጋችን እንግዳ አይደለም::

ያም ሆኖ በመደበኛዉ አሰራር የዐቃቤህግ ማስረጃ በክፊል (የጽሁፍ) ለተከሳሽ አስቀድሞ የሚደርሰዉ ቢሆንም ስለተከሳሽ ማስረጃ ምንም የሚደረግ ነገር ባለመኖሩ ዐቃቤህግ የተከሳሽ ማስረጃ ይዘቱ ይቅርና ስለመኖር አለመኖሩ እንኳ የራሱ ክርክር ከማለቁ በፊት ሳያዉቅ ቆይቶ የተከሳሹ ክርክር መቅረብ ሲጀምር ስለሚያገኘዉ ያለበቂ ዝግጅት ቀርቦ የመስቀለኛ ጥያቄ ሂደትን ያከናዉናል:: ከዚህ የተነሳ አንዳንዴ በችሎት የሚስተዋሉ አጋጣሚዎች ይህን ማስረጃ የመግላለጽ ነገር አስቀድሞ ማድረግ አይቻልም ወይ የሚል ጥያቄ የሚጋብዙ ናቸዉ::

የጽሁፉ አዘጋጅ በተለያዩ አጋጣሚዎች ችሎት ላይ የሚከናወኑ ሂደቶችን እንዳስተዋለዉ የመከላከያ ማስረጃ ሲቀርብ የሚከተለዉ ይከናወናል፡፡ *ተከሳሽ የመከላከያ ክርክሩን በወንጀሉ ቦታ አልነበረኩም፣ በሌላ ቦታ ነበርኩ፣ ለዚህም የሚያዉቁ ምስክሮች (በተወሰነ ቀንና ሰዓት በአንድ ተለይቶ በተመለከተ ቦታ እንደነበርኩ) ያሰረዳሉ* በሚል ያስመዘግባል፡፡ ከዚህ በኋላ ዐቃቤ ህግ ቋሚጉን በተመለከተ ዝርዝር ነገሮችን ከተከሳሽ ለማግኘት ተከሳሹን ወይም ጠበቃዉን ለረጅም ጊዜ እንዲጠይቅ ይደረጋል::

ይህ አይነቱ አካሄድ የፍርድ ቤቱን ጊዜ የሚያባክን ነዉ:: ፍርድቤቶች ይህን አሰራር በዚህ ደረጃ የሚፈቅዱ ከሆነ ተከሳሹ መጀመሪያዉኑ ክሱን ሰምቶ ወንጀሉን ሲክድ ራሱን ለመከላከል ስለሚያቀርበዉ ማስረጃ መግለጫ እንዲሰጥ ቢያደርጉ ልዩነት ይኖረዋል ወይ? ዐቃቤህግስ እንዲህ እንዲደረግ በዚህ ደረጃ ሊጠይቅ አይገባም?

በወንጀሉ ጊዜና ቦታ አልነበርኩም የሚለዉ መከላከያና መስቀለኛ ጥያቄ፡- በርግጥ ዘወትር የሚቀርብ የተከሳሾች መከላከያ ክርክር በወንጀሉ ጊዜ በወንጀሉ ቦታ አልነበርኩም የሚል ከመሆኑ አኳያ ይህን መከላከያ አስመልክቶ የዐቃቤህግን የመስቀለኛ ጥያቄ ክህሎት በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን አንስቶ መመርመር ተገቢ ነዉ:: ከላይ እንደተመለከተዉ

ዐቃቤህግ ይህን መከላከያ አስመልክቶ ያለዉ ፍላጎት የፍሬነገር ዝርዝር ላይ በማተኮር መከላከያ ምስክሮች በፍሬነገር ዝርዝሩ ላይ የሚለያዩበትን አጋጣሚ በመፍጠር እንዳይታመኑ ማድረግ ነዉ። ነገር ግን የዚህ ክርክር የተለየ ባህሪ ዕዉነትን ተመርኩዞ ሊቀርብና በቀላሉ ሊዋሸበት የሚችል መሆኑ ነዉ። በዚህ መከላከያ ማስረጃ የሚነገረዉ ነገር ሙሉ በሙሉ የተከሰተ ዕዉነተኛ ታሪክ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ምስክሮች በፍሬነገር ዝርዝር ላይ ተመሳሳይ ሊመስክሩ ይችላሉ። ችግሩ የሚኖረዉ ይህ ታሪክ በርግጥ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ የተከሰተ ታሪክ ነዉ ወይ የሚለዉ ዉስጥ ነዉ። ምስክሮች በሌላ ጊዜ የተከሰተን ዕዉነተኛ ታሪክ በወንጀሉ ጊዜ እንደተፈጸመ አድርገዉ ለማቅረብ ተዘጋጅተዉ ቢቀርቡ ትልቁ ድካማቸዉ ጊዜዉን መቀየር ላይ ብቻ ነዉ። ይህም ቀላል ነዉ። ስለዚህ ዐቃቤህግ መስቀለኛ ጥያቄዉን ምን ላይ እንዲያተኩር ሊያደርግ ይገባል? በታሪኩ ላይ ወይስ ስለጊዜ በተነገረዉ ምስክርነት ላይ? እንዲህ ከሆነስ የተከሳሹ መከላከያ ክርክር (ሙቡጥ) በሚቀርብበት ጊዜ የፍሬነገር ዝርዝር ፍለጋ የፍርድቤቱን ጊዜ በሚያባክን ሁኔታ ተከሳሹንና ጠበቃዉን በጥያቄና መልስ (ኢንተሮጌሽን ሊባል እስከሚችል) ማፋጠጥ ያስፈልጋል ወይ? ፍርድቤቶችስ የመከላከያ ክርክር አስቀድሞ እንዲገለጽ ማድረግ የለባቸዉም? ዐቃቤህግስ ይህን አስቀድሞ ሊጠይቅ አይችልም?

የመስቀለኛ ጥያቄ መርሆችና ቴክኒኮች፡- ዐቃቤህግ በመደበኛ የወንጀል ክስ ለመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ሲቀርብ ስለጉዳዩ በተለይም ስለምስክርነቱ አስቀድሞ ሳይዘጋጅ ማለትም ዕዉቀት ሳይኖረዉ ነዉ። መስቀለኛ ጥያቄ ሂደት እንኳንስ ያለቅድመዝግጅት ዝግጅትም ተደርጎ አስቸጋሪ ሥራ ነዉ። የመከላከያ ምስክሮች ከመዋሸት እስከ ሆን ብሎ አለማስታወስ ድረስ መሰናክል ሊፈጥሩ ይችላሉ። በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደቱ ለዐቃቤህግ ተባባሪ ላይሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ዐቃቤህግ በዚህ ሂደት ለማግኘት የሚፈልገዉን ምናልባትም ሊያገኝ የሚገባዉን ያለማግኘት ችግር ሊያጋጥመዉ ይችላል። እንዲያዉም የራሱን ክስ ሊጎዳ የሚችል አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄን ለማካሄድ ወይም ላለማካሄድ በከፍተኛ ጥንቃቄ መምረጥ አና ማካሄድ የግድ ነዉ። ለዚህ ደግሞ አንዳንድ መርሆችንና ቴክኒኮችን ማወቅ ተገቢ ነዉ። እነዚህ መርሆችና ቴክኒኮች በአሰራር ልማድ የምንፈጥራቸዉን ችግሮች ለማረም እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸዉ። እነዚህን ቆየት ብለን የምናያቸዉ ሆኖ ከዚያ በፊት ስለመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ወሰን እና መጠን አንዳንድ ነገሮች እንይ።

በቅድሚያ ከላይ እንደተገለጸዉ መስቀለኛ ጥያቄ አስቸጋሪ ሂደት ነዉ። አደጋዎቹ አሉት። ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄ ማከሄድ ተመራጭ ላይሆን ይችላል። መስቀለኛ ጥያቄ አለማካሄድ ምን ዉጤት አለዉ? በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 140 እንደተመለከተዉ መስቀለኛ ጥያቄ አለመጠየቅ በሌላዉ ወገን የተነገረዉን እንደማመን አያስቆጥርም። ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄ ብዙም ባይደፈር ይመረጣል። በተለይም የመስቀለኛ ጥያቄ ግብ ከሆኑት (የተቃራኒን ምስክርነት የማይታመን መሆኑን ማሳየት በክሱ ላይ የደረሰዉን ጉዳት ማስተካከል ወዘተ) አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ለማሳካት የምንችል ወይም ተገቢ ካልሆነ በቀር ወይም ምስክሩ ለጉዳያችን የምንፈልገዉ መረጃ ብቸኛ ምንጭ ካልሆነ በቀር መስቀለኛ ጥያቄ ማካሄድ የሚመከር አይደለም።

ሆኖም ዘወትር እንደሚስተዋለዉ አንዳንድ ምስክሮች ባህሪያቸዉ ምንም ሳይጠየቁ መሄድ የለባቸዉም የሚያስብል ይሆናል። በዚህ ጊዜ መስቀለኛ ጥያቄ ማንሳት የግድ ከሆነ ከላይ ሲባል እንደነበረዉ አደጋዉ የበዛ በመሆኑ መጠኑን ማሳነስ ይመከራል።

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 137(3) ስር መስቀለኛ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ጊዜ በተመለሱ ነገሮች ዉስጥ ያለዉን ስህተት አጠራጣሪ ወይም የማይታመን ቃል ለፍርድ ቤቱ ለመግለጽ ወይም ለማስተባበል የሚደረግ መሆኑ ተደንግጓል። ስለዚህ ከዚህ የወጣ ጥያቄ ሲነሳ ተቃዉሞ ሊገጥም ይችላል። ሆኖም በዋና ጥያቄ ከተፈጠረዉ ድንበር ወጥቶ መጠየቅ የሚቻልባቸዉ የተለዩ አጋጣሚዎች ይኖራሉ። ለምሳሌ የምስክሩን ተዓማኒነት የሚመለከቱ ጥያቄዎች በዋና ጥያቄ ጊዜ ባይነሱም በጠቅላላዉ ምስክሩ የተናገረዉን ነገር ተዓማኒነት የሚመለከት ስለሚሆን ተቀባይነት ያለዉ አካሄድ ነዉ። ለምሳሌ የተለመደዉ የተከሳሽ መከላከያ ክርክር (በወንጀሉ ጊዜ በወንጀሉ ቦታ አልነበርኩም) ሲቀርብ የሚነገረዉ ታሪክ የተፈጸመበትን ጊዜ ከወንጀሉ ጊዜ ጋር እንዲገጥም የማድረግ ነገር ስለሚኖር ምስክሩ ጊዜን በመለየት ረገድ ስላለዉ ችሎታ ለማረጋገጥ በዚህ ዙሪያ ጥያቄ ቢነሳ ሊከለከል አይገባም። ምስክሩ ተዓማኒነቱ ምን ያህል እንደሆነ ለማሳየት የሚረዳ በመሆኑ ተገቢ ነዉ።

መልመጃ

በወንጀሉ ጊዜና ቦታ አልነበርኩም በሚለዉ ክርክር ዉስጥ ዐቃቤህግ ስለምስክሩ ጊዜን የመለየት ችሎታ ረዘም ያለ የመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ለመምራት በመፈለግ በዚሁ ነጥብ

ላይ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ሲያነሳ ተከሳሽ ከጭብጥ ዉጪ ነዉ የሚል ተቃዉሞ ቢያነሳና ፍርድቤት ለዚህ የዐቃቤህግ አቀራረብ ማብራሪያ ቢጠይቅ ዐቃቤህግ ምን ብሎ ሊያሰረዳ ይችላል?

ከተዓማኒነት ጋር በተያያዘ ምስክሩ በነገሩ ዉስጥ ያለዉ ጥቅም ወይም ፍላጎት ሊታለፍ የማይገባዉ ነጥብ ነዉ:: ምስክሩ የሚሰጠዉ ምስክርነት ከነገሩ ዉስጥ ካለዉ ጥቅም ወይም ፍላጎት የተነሳ ከዕዉነት የራቀ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ በነገሩ ዉስጥ ጥቅም እንዳለዉ ማሳየት በሰጠዉ ምስክርነት ላይ ዕምነት እንዲታጣ ሊያደርግ ስለሚችል በዋና ጥያቄ አልተነሳም ተብሎ ቀሪ ሊደረግ አይገባም:: አንዳንዴ ምስክሩ ራሱ ለመስቀለኛ ጥያቄ በሚመልስበት ጊዜ በዋና ጥያቄ ጊዜ ላልተነሱ ሀሳቦች መንገድ ሊከፍት ይችላል:: በዚህ ጊዜ ምስክሩ ራሱ ባነሳዉ ነገር ላይ ሌላ መስቀለኛ ጥያቄ የማይጠየቅበት ምክንያት አይኖርም:: ስለዚህ ዐቃቤህግ እነዚህን አጋጣሚዎች በንቃት መጠባበቅ ይገባዋል፣ ለዚህም ምስክርነቱን በሚገባ ማዳመጥ ይኖርበታል፡፡

ከጭብጥ ከመዉጣት ሌላ በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት የማይፈቀድ ነገር ምስክርን ማስፈራራት እና ማንጓጠጥ ነዉ:: ምስክሩ ዐቃቤህግ የሚፈልገዉን እንዲል መገደድ የለበትም:: ይህን ማድረግ የሚቻለዉ ክህሎት በተሞላዉ የአጠያየቅ ዘዴ መሆን አለበት:: አዘዉትሮ በፍርድቤቶች በሚደረግ ክርክር ጊዜ የሚስተዋል በህግ ባለሙያዎች (ዐቃብያነህግ ጠበቆች ዳኞች) የሚባል አንድ ነገር አለ:: ምስክሩ እነዚህ ባለሙያዎች እንደፈለጉት ወይም ዕዉነት ነዉ ብለዉ እንደሚያስቡት ሳይናገር በቀረ ጊዜ በሃሰት መመስከር በወንጀል እንደሚያስቀጣ ይነግሩታል:: ይህ ነገር ማስፈራራት ከመሆኑ በተረፈ ነገሩ ተሰምቶ ሳያልቅ እና ምስክሩ የተናገረዉ ሃሰት ይሁን ዕዉነት ሳይረጋገጥ በጉዳዩም ላይ በምስክሩም ላይ ፍርድ የመስጠት ያህል ይሆናል:: ከዐቃቤህግ የህግ ጠባቂነት ሚና አኳያም የሰዉን መብት የሚደነግጉ ህጎችን የመጣስ ዉጤት ይኖረዋል::

መሪ ጥያቄ በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ዉስጥ በህግ የተፈቀደ ቢሆንም ዐቃቤህግ (ሌሎች ባለሙያዎችም) ሲጠቀሙበት አይስተዋልም:: በርግጥ ይህ የጥያቄ አይነት ስለሚያስከትለዉ መልስ ማወቅን ስለሚጠይቅና ዐቃቤህግ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸዉ ያለቅድመዝግጅት ስለሚቀርብ ይህን የጥያቄ አይነት ለመጠቀም አይደፋፈርም:: ሆኖም ዋና ጥያቄ የሚመስል ሂደት በማካሄድ ነገሮችን እንዲደገሙ ከማድረግና በዚህም ችሎትን ከማሰላቸት ግፋ ሲልም የዐቃቤህግን ክስ የሚያፈርስ አጋጣሚ ከመፍጠር በዚያዉ በችሎት

በተደረገች ዝግጅትም ቢሆን መሪ ጥያቄ በመጠየቅ ምስክሩን እንዳሻዉ እንዳይናገር መቆጣጠር ይመከራል:: በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ዋናዉ ግብ ምስክሩን መቆጣጠር የሚመሰክረዉን ነገር መወሰን በዚህም ለመዋሸት ያለዉን ዝንባሌ ወዘተ ማስቀረት ነዉ:: በዋና ጥያቄ ጊዜ ሊነሱ የሚገባቸዉ ዝግ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት ምስክሩ የሚናገረዉን ነገር ልቅ ማድረግ ሂደቱን ዐቃቤህጉ ሳይሆን ምስክሩ እንዲቆጣጠረዉ ማድረግ ይሆናል::

የተከሳሽን ምስክር በመስቀለኛ ጥያቄ መቆጣጠር የሚቻልበት መንገድ ጥያቄዉን መሪ ጥያቄ በማድረግ ብቻ አይደለም:: ጥያቄዉን አጭር ማድረግም እንዲሁ በምስክሩ ላይ የበላይነትን ያስገኛል:: ጥያቄዉ ከአንድ በላይ ሃሳብ ከሌለዉ እና ርዝመቱም አጭር ከሆነ ምስክሩ ለዚሁ ብቻ መልስ እንዲሰጥ ሰለሚገደድ ብዙም መፈናፈኛ አይኖረዉም:: በተለይ ከአንድ በላይ ሃሳብ አለመያዙ ምስክሩ መርጦ የመመለስ ስራ እንዳይሰራ ያደርገዋል የመልሱ ወሰን የታጠረ ይሆናል::

ከዚህ በተያያዘ ከአንድ በላይ የሆኑ ጥያቄዎችን አነባብሮ በአንድ ጊዜ መጠየቅ የሚገኘዉን መልስ ግልጽ እንዳይሆን ያደርገዋል:: አንድ መልስ ቢሰጥ ለየትኛዉ ጥያቄ እንደተመለሰ ማወቅ አይቻልም:: ስለዚህ እንደዋና ጥያቄ ጊዜ በአንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ ብቻ ማንሳት ተገቢ ይሆናል::

የመስቀለኛ ጥያቄ መልሱ የሚታወቅ ወይም ማስረጃ ሊቀርብበት የሚችል መሆን ይኖርበታል:: ግን ቀደም ሲል እንደተገለጸዉ ትልቁ ችግር ስለመከላከያ ምስክርነትም ሆነ ስለምስክሩ አስቀድሞ የሚሰበሰብ ማስረጃ የለም:: ስለዚህ የዐቃቤህግ መስቀለኛ ጥያቄዎች በዕድል ባወጣ ያዉጣዉ ወዘተ ላይ ተመስርተዉ የሚጠየቁ ናቸዉ:: ሆኖም ማስረጃ በተሰበሰበባቸዉ አጋጣሚዎች ለምስክሩ የሚቀርብ መስቀለኛ ጥያቄ ሊመለስ የሚገባዉን መልስ የሚጠቁም ሊሆን ይገባል:: ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠዉ መልስ ምንም ይሁን ምን በቂ ስለሚሆን የሚገኘዉ መልስ ምንነት ስጋት አይፈጥርም:: የሚፈለገዉን መልስ ምስክሩ አመነም አላመነም ዉጤቱን አይቀይረዉም:: ምክንያቱም ቢያምን ዐቃቤህግ እንደሚፈልገዉ ሆነለት ማለት ሲሆን ከካደ ደግሞ ማስረጃ ስላለ ምስክርነቱን ማስተባበልና በዚህም ምስክሩ ተዓማኒነት የሌለዉ መሆኑን ማሳየት ይቻላል::

ዉጤታማ መስቀለኛ ጥያቄ በጥያቄዎች አይነት ብቻ የሚወሰን አይደለም:: የጥያቄዎቹ ቅደም ተከተልም (ቅንብር) የራሱ አስተወጽየ ይኖረዋል:: በተለይ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ምስክሩን በሚገባ መቆጣጠር እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ አኳያ የጥያቄዎቻችን አወቃቀር ይህን የመቆጣጠር ችሎታ የሚያሳጣ መሆን የለበትም:: ስለዚህ የተቃራኒ ወገንን ምስክር የምንጠይቅ እንደመሆኑ በቀላሉ የምንፈልገዉን ነገር ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆን የጥያቄዎቻችን አወቃቀር የምስክሩን ወዳጅነት የሚያስገኝ እንዲሆን የግድ ነዉ::

ዐቃቤህግ መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠይቅ ከወሰነ በዚህ ጥያቄ ሊያሳካ የፈለገዉን ነገር በሂደቱ መጀመሪያ ላይ መግለጽ የለበትም:: ይህ ግብ በምስክሩ ከታወቀ የተቃራኒ ወገን ምስክር እንደመሆኑ የመስቀለኛ ጥያቄዉ ሂደት ወደዚህ ግብ እንዲደርስ መፍቀዱ አጠራጣሪ ነዉ:: ስለዚህ ይህን ግብ የሚደብቅ የጥያቄዎች ቅደምተከተል መኖር አለበት::

ከዚህ የተነሳ በመነሻዉ ላይ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ከምስክሩ ጋር ፍጥጫን የማያስነሱ ምስክሩ በቀላሉ ሊያምናቸዉ ወይም ሊስማማባቸዉ የሚችሉ ፍሬነገሮችን የሚመለከቱ መሆን ይገባቸዋል:: ይህን ማድረግ በዐቃቤህጉና በተከሳሽ ምስክር መካከል ሰላማዊ ሁኔታ ይፈጥራል:: ስለዚህ ከምስክሩ የሚፈለገዉን ለማግኘት ቀላል ይሆናል ቢያንስ ምስክሩ መሰናክሎችን ከመፍጠር ይታቀባል::

ይህ ማለት ደግሞ ዐቃቤህግ ለክሱ እጅግ አስፈላጊ የሚላቸዉን ነጥቦች መጀመሪያ ላይ ማንሳት የለበትም ማለት ነዉ:: እነዚህን ጉዳዮች ከመነሻዉ ከገለጸ ምስክሩ የመስቀለኛ ጥያቄዉን ዓላማ በቀላሉ ማወቅ ስለሚችል እና ይህም ምስክሩ በዋና ጥያቄ ጊዜ ከተናገረዉ ሊቃረን ስለሚችል ምስክሩ ይህን የተፈለገ ነገር ለመስጠት አይፈቅድም:: በሚችለዉ መንገድ ራሱን ከመቃረን ለማዳን የማስተካከያ መረጃዎችን ከመግለጽ ያለፈ ነገር ለመፈጸም ፈቃደኛ እንዳይሆን ያደርገዋል:: ስለዚህ ዐቃቤህግ መነሻዉ ላይ ከዋና ጥያቄ ሂደት በተቃራኒ ዋና ነጥቦችን ሳይሆን ዝርዝር ጉዳዮችን (በተቻለ መጠን ምስክሩ የማይክዳቸዉን) እንዲያነሳ ይመከራል::

ከዚህ ሌላ ዐቃቤህግ የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማዉን ለመደበቅ በጥያቄና መልሱ ሂደት ጊዜ ከአንድ የጥያቄ ሃሳብ ወደሌላዉ በመዝለል ምስክሩ የነገሩን አቅጣጫ እንዳይገነዘብ ማድረግ ይችላል:: ለዚህም ጥያቄዎቹ በተለያየ ርዕስ ስር እንዲደራጁ ሊያደርግ ይገባል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የአካባቢ ማስረጃን አስመልክቶ ከዋና ጥያቄ ጋር በማያያዝ ያነሳነዉ ሃሳብ ለመስቀለኛ ጥያቄም አግባብነት ይኖረዋል:: በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ዓላማዉ ምስክሩ የዐቃቤህግን የክርክር አቅጣጫ እንዳይገነዘብ ማደረግ በመሆኑ የአካባቢ ማስረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎች እነዚህን ማስረጃዎቹ በአንድ ላይ የማሰባሰብ ባህሪ እንዳይኖራቸዉ ማድረግ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ከተሰባሰቡ ትርጉማቸዉ ግልጽ ስለሚሆን ምስክሩ የክርክሩን አቅጣጫ በቀላሉ እንዲረዳዉ በማድረግ መሰናክል እንዲፈጥር ይገፋፋዋል:: ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄዎች የአካባቢ ማስረጃዎች እንዲበታተኑ የማድረግ ችሎታ ሊኖራቸዉ ይገባል:: ለዚህም ከላይ እንደተመከለተዉ የጥያቄዎችን ቅድም ተከተለ በማዘባረቅ ከርዕስ ወደርዕስ መዟዟር አስፈለጊ ነዉ::

ከጥያቄዎች ቅደም ተከተል ጋር በተያያዘ አዘዉትሮ የሚታይ ስህተት አለ:: በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ምስክሩ ሊክዳቸዉ የማይችሉ ፍሬነገሮችን መሰረት በማድረግ ዐቃቤህግ ለሚያቀርባቸዉ ጥያቄዎች በሚገኙ መልሶች የሚገነባ ታሪክ ሊኖር ይችላል:: ከዚህ በኋላ የዚህን ሁሉ ጥያቄና መልስ እንድምታ (ድምዳሜ) ምስክሩ እንዲናገር ከተጠየቀ መልሱ የተከሳሹን ክርክር የሚጎዳ ከመሰለዉ ወይም ከሆነ ምስክሩ የጥያቄዉ አቅጣጫ ሰለሚገባዉ ቀደም ሲል የሰጣቸዉን መልሶች የሚያስተካክል መልስ ሊሰጥ ስለዚህ ለክሱ የሚረዳዉን ነገር የመደበቅ ተግባር ሊፈጽም ይችላል:: ይህም እንኳ ባይሆን ተከሳሹ ወይም ጠበቃዉ በክርክሩ ላይ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ የደረሰዉን ጉዳት በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ የማስተካከል ስራ እንዲሰራ የማባነን ዉጤት ይኖረዋል:: ይህም ካልሆነ ፍርድቤቱ ራሱ በማጣሪያ ጥያቄ ጊዜ ነገሩን እንዲያነሳ ምስክሩም በዚህ አጋጣሚ ነገሩን የሚያድበሰብስ ወይም የሚያርም ተግባር እንዲፈጽም የማስታወስ ዉጤት ይኖረዋል:: በተግባር ሲደረግ የሚስተዋለዉም እንዲህ ያለ ዉጤትን የሚያመጣ አጠያየቅ ነዉ:: ስለዚህ ይህን የነገሩን ማሰሪያ ጥያቄ ዐቃቤህግ መጠየቅ የለበትም:: ቀላልና ተራ በሚመስሉ ጥያቄዎች የተገነባዉ ታሪክ እንድምታ ለፍርድቤቱ የሚተዉ ነዉ:: ምናልባት ለፍርድቤቱ ግልጽ የማይሆን ቢሆን

በመስቀለኛ ጥያቄ የተሰጡ መልሶች የሚጠቁሙት ድምዳሜ ምን እንደሆነ በክርክር ማቆሚያ ንግግር ጊዜ መግለጽ ይቻላል::

ነገር ግን አሁን ባለዉ አሰራር ይህ ከላይ የተመለከተዉ የአሰራር አቅጣጫ ምን ያህል ያስኬዳል? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነዉ:: ምክንያቱም የክርክር መዝጊያ ንግግር ወይም በተለምዶ አጠራሩ የመፋረጃ ሃሳብ እንዲቀርብ የሚያደፋፍሩ ፍርድቤቶች ጥቂት ከመሆናቸዉም በላይ እንዲቀርብ የሚያደርጉትም ቢሆኑ በአብዛኛዉ በጽሁፍ እንዲቀርብ የሚያደርጉ ሰለሆነ እንዲሁም የቀረበዉን ሃሳብ የሚጠቀሙበት ማለትም በዉሳኔ ጊዜ ከግምት የሚያስገቡት ፍርድቤቶች በእጃቸዉ ጥቂት በመሆናቸዉ ዐቃቤህግ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ያስመሰከራቸዉ ፍሬነገሮች ድምር ዉጤት ምን እንደሆነ በክርክሩ ጊዜ (በመስቀለኛ ጥያቄ ማጠናቀቂያ ጊዜ) ካልጠቆመ እንዲህ የሚያደርግበት መድረክ አያገኝም:: ከዚህ የተነሳ ዐቃቤህግ ከተከሳሽ ምስክር ጋር በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ዉስጥ ወይም ማሳረጊያ ላይ የምስክርነቱን እንድምታ እመን አትመን እሰጥ አገባ ዉስጥ ሲገባ ይታያል:: ስለዚህ ፍርድቤቶች የክርክር ማቆሚያ ንግግርን አሰራር እንዲያከብሩ ዐቃቤህግ መወትወት ዳኞችም ይህን አሰራር ባህል እንዲያደርጉት የግድ ነዉ::

በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ቅድመዝግጅት ካለ ጥያቄዎችን በጽሁፍ አዘጋጅቶ የመቅረብ ነገር ሊኖር ይችላል:: ነገር ግን እንዲህ አይነቱ አቀራረብ መልካም አይደለም:: ጥያቄዎቹ በጽሁፍ ከተዘጋጁ ወይ እያነበቡ ለመጠየቅ ነዉ አለያም ሸምድዶ ከሃሳብ እያስታወሱ ለመጠየቅ ነዉ:: ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸዉ:: ወረቀት ላይ የምናተኩር ከሆነ ወይም በአዕምሯችን ስለምናስታዉሰዉ ነገር የምናስብ ከሆነ ምስክሩን ዓይንለዓይን አንገናኝም ማለት ነዉ:: በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ከምስክሩ ጋር የዓይንላይን ግንኙነት መኖር ምስክሩን ለመቆጣጠር ይረዳል:: ከዚህም ሌላ ያልተጠበቁ ለክሱ የሚጠቅሙ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም በጥያቄና መልሱ ሂደት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል:: ጥያቄን ከወረቀት ላይ ወይም ከአዕምሮ ዉስጥ ማንበብ ይህን አትኩሮት ስለሚነፍግ በዚህም ረገድ ዐቃቤህግ ብሎም ክሱ ተጎጂ ይሆናሉ:: በተለይ ጥያቄዉ በርከት ያለ ከሆነ አንዱ ጥያቄ ተመልሶ ሌላ ለመጠየቅ በዝርዝሩ ዉስጥ የሚቀጥለዉ ጥያቄ ቦታ እንዳይጠፋ በማሰብ አትኩሮትን ወደዚሁ ጽሁፍ ለማድረግ መገደድ ይኖራል::

ከዚህ የተሻለዉ አማራጭ ጥያቄዉን በዝርዝር አለመጻፍ ነዉ:: ዝግጅቱ የግድ በጽሁፍ መሆን ካለበት የጥያቄዎቹን ሃሳቦች የያዙ ርዕሶችን ዝርዝር (አዉትላይን) አዘጋጅቶ

መቅረብ ይመረጣል:: ርዕሶቹን ብቻ ከወረቀቱ ላይ በመመልከት ጥያቄዎቹን ከራስ ማመንጨት ይገባል::

አትኩሮትን ወደጥያቄና መልሱ ሂደት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ከፍ ብሎ ተጠቅሷል:: ከዚህ በተያያዘ ለመሰቀለኛ ጥያቄ የሚሰጡ መልሶችን ዐቃቤህግ ማድመጥ ይኖርበታል:: ለክሱ ገንቢ የሆኑ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም የሚረዳ ከመሆኑም በላይ ምስክሩ ጥያቄዉን እየሸሸ የሚመልስ ከሆነ ይህን አስተዉሎ ጥያቄዉ እንዲመለስ ለማስገደድ (ምስክሩን ለመቆጣጠር) የሚያስችል ነዉ:: ከዚህ ከማድመጥ የሚያሰናክለዉ አንዱ ከላይ እንደተመለከትነዉ ጥያቄን በዝርዝር ጽፎ ቀርቦ በንባብ መጠየቅ ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ ምስክርነቱን በዝርዝር መጻፍ ነዉ:: ሰለዚህ እነዚህን የአሰራር ዘዴዎች ወይም ባህሪዎች ዐቃቤህግ ሊያስወግድ ይገባል::

አንዳንድ ጊዜ የተቃራኒ ወገን ምስክር ሳያስበዉ ወይም ከዐቃቤህግ የአጠያየቅ ብቃት የተነሳ ለክሱ ጠቃሚ ምስክርነት ሊሰጥ ይችላል:: በሌሎች አጋጣሚዎች ደግሞ ክሱን የሚጎዳ ነገር ሊመሰክር ይችላል:: በዚህ ጊዜ ዐቃቤህግ እንደተሰጠዉ ምስክርነት ጠቃሚነት ወይም ጎጂነት ስሜቱ የሚለዋወጥ ከሆነ ምስክሩ በሰጠዉ ምስክርነት እያደረሰ ያለዉን ዉጤት በሚገባ እንዲገነዘብ ስለሚያደርገዉ የተከሳሹን ክርክር የሚጎዳዉን ምስክርነት ያስተካክላል የዐቃቤህግን ክስ የጎዳበትን ምስክርነት በማጠናከር የበላይነቱን ይዞ የክርክሩን ሂደት የመቆጣጠሩን ሚና ከዐቃቤህግ ይነጥቃል::

የተከሳሽ ምስክር ለዐቃቤህግ ክስ ገንቢ የሆነ ምስክርነት ከሚሰጥባቸዉ አጋጣሚዎች አንዱ መዋሸት ነዉ:: መዋሸቱን የምናዉቅ ከሆነ ከምስክርነቱ በተቃራኒ የሆነዉን ዕዉነተኛዉን ታሪክ የሚያሳይ ማስረጃ አለን ማለት ነዉ:: ስለዚህ ምስክሩ ሲዋሽ ካገኘነዉ በዚሁ ዉሸቱ እንዲቀጥልበት የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ማንሳት እንጂ መዋሸቱን ያወቅንበት መሆኑን የሚገልጽ ምንም ነገር ማድረግ የለብንም:: ምክንያቱም ይህን ከገለጽን የዋሸበትን ሁኔታ ያስተካክላል ስለዚህ ዐቃቤህግ ምስክሩ የማይታመን ወይም የሚዋሽ መሆኑን የሚያስረዳበትን አጋጣሚ ያጣል ማለት ነዉ::

በብዙ አጋጣሚዎች አላዋቂ መስሎ ላለመታየት በሚደረግ ጥረት ክርክርን መጉዳት ሊከተል ይችላል። ስለዚህ በማያዉቁት ጉዳይ ጥያቄ ከመጠየቅ አለመቦዘን ተገቢ ነዉ። ለምሳሌ በባለሙያ ምስክርነት ጊዜ ለባለሙያዉ ወይም ስለጉዳዩ ዕዉቀት ላላቸዉ ሰዎች ተራ የሆነ ነገር ሁሉ ለዐቃቤህግ ግልጽ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ አላዋቂ ላለመምሰል የባለሙያ ምስክርነት በሚነገርበት ጊዜ ነገሩ እንደገባዉ ሰዉ ዝም ብሎ ማዳመጥ ጉዳቱን ማወቅ የሚቻለዉ ነገሩ ካለቀ በኋላ ሰለሚሆን ጥንቃቄ ይፈልጋል። በዚህ ረገድ ግልጽ ያልሆነን ነገር ማብራሪያ እንዲሰጥበት መጠየቅ ሊያሳፍር አይገባም ምንም ያህል ተራ ነገር ቢሆን ወይም ቢመስል።

ቀደም ሲል ለማየት እንደተሞከረዉ መስቀለኛ ጥያቄ አደጋ ያለዉ ሂደት ነዉ እንደተገኘ የሚገባበት አይደለም። ጥንቃቄ ያሻዋል። ተመራጭ ሆኖ ወይም አማራጭ የሌለዉ ሆኖ ጥያቄዉ መካሄድ ያለበት ከሆነ የተመጠነ ሊሆን ይገባዋል። በዚህ ጊዜ ምስክሩን ለመቆጣጠር መቻል ያስፈልጋል። ለዚህም የማያጨቃጭቁ ጥያቄዎችን ማንሳት አንዱ ከምስክሩ ጋር ያለመፋጠጥ ሁኔታ መፍጠሪያ መንገድ ሲሆን ሌላዉ የጥያቄዉን ሂደት ዓላማ መደበቅ መቻል ነዉ። ይህ ማለት ግን ምስክሩን ማፋጠጥ ወይም ማስጨነቅ በማንኛዉም አጋጣሚ ተገቢ አይደለም ማለት አይደለም። ተቃራኒ ምስክር እንደመሆኑ የምንፈልገዉን ነገር በቀላሉ ሊሰጠን አይችልም ወይም አይፈቅድም። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ፍጥጫ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ትልቁ ጥያቄ ግን መቼ የሚለዉ ነዉ። ይህን ነገር መቼ ማድረግና አለማድረግ እንዳለብን የምናዉቅባቸዉን አንዳንድ ሁኔታዎች መለየት ያስፍልጋል።

ምስክርን ማስጨነቅ ወይም ማፋጠጥ ተገቢ የሚሆንበት ጊዜ ምልክቶች - የምስክሩ መረጋጋት አለመቻል ከጠበቃዉ ርዳታን መጠበቅ መናደድ ወይም ማድበስበስ መጀመር የጠበቃዉ ማደናገሪያ ወይም አቅጣጫ ማስቀየሪያ ተቃዉሞዎች መበራከት - እነዚህና መሰል ሁኔታዎች ምስክሩ ለማፋጠጥ የተጋለጠ መሆኑን ጠቋሚ ናቸዉ። በዚህ ጊዜ ምስክሩ የደበቀዉን ለማዉጣት ወይም ነገሮችን ማሳሳት ወይም ማዘባረቅ ጀምሮ ከሆነ የበለጠ ነገር የሚያበላሽበት ሁኔታ ዉስጥ መሆኑን መረዳትና ማፋጠጡን ማጠንከር ያስፈልጋል።

በዚህ ሁኔታ የተጀመረ ማፋጠጥ ቢኖርም ምስክሩ እየጠነከረ ከመጣና በቀላሉ የሚፈታ ሰዉ ካልሆነ ማፈግፈግ - መተዉ ተመራጭ ነዉ::

ምስክሩን ማፋጠጥ ተገቢ የማይሆንባቸዉ አጋጣሚዎች ሲኖሩ በቀጥታ ማጥቃትን ማስቀረት ተገቢ ነዉ:: ይህ ተገቢ የሚሆንባቸዉ ሁኔታዎች ባብዛኛዉ ሃዘኔታን ወይም አክብሮትን የሚያገኙ ሰዎች ምስክር የሆኑባቸዉ አጋጣሚዎች ናቸዉ:: እነዚህም - ህጻናት አዛዉንት የሃይማኖት ሰዎች ወይም አባቶች ወዘተ ናቸዉ:: በነዚህ አጋጣሚዎች በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ካልኖረ በቀር እንደዚህ አይነት ሰዎችን ማፋጠጥና ማስጨነቅ በዳኞችና ሂደቱን በሚከታለዉ ህጎብረተሰብ ፊት የሚያስጸይፍ ሊሆን ስለሚችል ዉጤቱ አፍራሽ ይሆናልና ይህ አይነቱን አቀራረብ መተዉ ተገቢ ነዉ::

ከመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ጋር የማይነጣጠለዉ ይህ ምስክርን የማስተባበል ነገር በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 145 የተፈቀደ ነዉ:: ይህ ህግ ተከሳሽ የዐቃቤህግን ምስክር የሚያስተባብልበትን ሥነሥርዓት ብቻ የሚደነግግ ይመስላል:: ሆኖም በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠ ምስክርነት ጽሁፍ ለምስክርነት ማስተባበያ ይሆን ዘንድ ከመፈቀዱ በፊት ለፍርድቤት የሚቀርበዉ በተከሳሽ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በዐቃቤህግም ጭምር ነዉ:: ከዚህ በኋላ ፍርድቤት ጽሁፉን ለማስተባበያነት እንዲሰጠዉ የሚያደርገዉ ለተከሳሹ ነዉ::

መልመጃ

1. *በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 145 በተቋቋመዉ ድንጋጌ መሰረት ዐቃቤህግ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ በፖሊስ ጣቢያ በተሰጠ የምስክርነት ጽሁፍ አማካኝነት የተከሳሽን ምስክር ማስተባበል አልተፈቀደለትም ማለት ይቻላል?*
2. *ምናልባት በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጽሁፉ ለተከሳሹ ይደርሰዋል ሲል ዐቃቤህግን ያለመጥቀሱ ይህ ጽሁፍ ለማንም ከመድረሱ በፊት ከምርመራ መዝገቡ ጋር የሚደርሰዉ ለዐቃቤህግ ስለሆነ እንዲደርሰዉ ማድረግ ትርጉም አልባ ስለሚሆን ይሆን?*

ያም ሆነ ይህ በተለመደዉ አሰራር መሰረት ዐቃቤህግ የራሱን ምስክር በተመለከተ ቃሉን እየለወጠ መሆኑን ለማስረዳት በፖሊስ ጣቢያ የሰጠዉን ቃል ጽሁፍ ለምስክሩ አሳይቶ

ፊርማዉን እንዲያረጋግጥ ካደረገ በኋላ ለፍርድቤት በማቅረብ ሲያስወስን ይታያል። በተመሳሳይ ሁኔታ የተከሳሹ ምስክር በፖሊስ ምርመራ ጊዜ የሰጠዉን ቃል ጽሁፍ ለማስተባበያነት እንዲታይለት ቢጠይቅ ምን ስህተት አለዉ? የተከሳሽ ምስክር በፖሊስ ጣቢያ የምስክርነት ቃል ሊያስመዘግብ ይችላል? የተከሳሽ ምስክር በወንጀል ምርመራ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ቃሉን በምስክርነት ከሰጠ በኋላ ዐቃቤህግ ማስረጃ አድርጎ ሳይቆጥረዉ ቢቀርና ተከሳሽ ምስክሩ ቢያደርገዉ ለፖሊስ ምስክርነቱን የሰጠ ምስክር ሊባል አይችልም?

በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የሚደረገዉ ማስተባበል ቀድሞ በተሰጠ ቃል ላይ የተመረኮዘ ነዉ። ሆኖም የማስትባበል ስራ ቀደም ሲል በምስክሩ በተደረገ ሌላ ተግባርም ሊከናወን ይችላል። እንዲሁም የምስክሩን ባህሪ (ምናልባትም የመዋሸት) እና በጉዳዩ ዉጤት ምስክሩ የሚኖረዉን ጥቅም በማሳየት ምስክሩን ማስተባበል ይቻላል።

ከወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 145 ዉጪ ያሉ ምስክር ማስተባበያ ዘዴዎች፡- የቀድሞ የምስክር ቃልንም በተመለከተ ህጉ በፖሊስ ጣቢያ የተመዘገበን ቃል ብቻ ይገልጻል። ቀደም ሲል በፍርድቤት በማንኛዉም ጉዳይ የተመዘገበ ቃልስ ምስክሩን ለማስተባበል አይዉልም? የቀዳሚ ምርመራ ፍርድቤት የመዘገበዉ ምስክርነት ለዚህ አገልግሎት ማዋል አይቻልም? በክስ መስማት ጊዜ በፍርድቤት ከሚደረግ የቃል ምዝገባ ሌላ ቃልን ለመመዝገብ ብቻ በሚሰራ ፍርድቤት ቃል ሊመዘገብ አይችልም (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 35)? ምስክሩ ባለዉ የሥራ ኃላፊነት መሰረት የጻፋቸዉ ጽሁፎች ወይም ደብዳቤዎች ምስክሩን ለማስተባበል አያገለግሉም?

በነዚህ በሁሉም ሆነ በፖሊስ ጣቢያ ቃል ምስክርን ለማስተባበል አስቀድሞ ይህን ቃል ወይም መጻጻፍ እና ይዘቱን ማወቅ እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም። ለዚህ ደግሞ ከዚህ በፊት እንደተገለጸዉ ዝግጅት ማድረግ የማይታለፍ ይሆናል። ለዚህም አስቀድሞ ስለተከሳሹ ምስክር እንዲሁም ስለመከላከያ ክርክሩ ማወቅ ያስፈልጋል። ሆኖም ይህ ክርክር እንዲገለጽለት ዐቃቤህግ ፍርድቤትን መጠየቅ ይችላል ወይ የሚለዉ የዘወትር ጥያቄ ነዉ?

7.2.3 ድጋሚ ጥያቄ (Re-examination)

የድጋሚ ጥያቄ ዓላማ በመስቀለያ ጥያቄ የተፈጠረውን ክፍተት ማጥበብና በዋናው ጥያቄ የተነሱ ጉዳዮች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ማግኘት ነው፡፡ ድጋሚ ጥያቄ መጠየቅ የሚቻለው መስቀለያ ጥያቄ የተጠየቀ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ የድጋሚ ጥያቄ ወሰን የመስቀለያ ጥያቄ ወሰን ነው፡፡ በመስቀለያ ጥያቄ ያልተነሱ ጉዳዮች በድጋሚ ጥያቄ ማንሣት አይቻልም፡፡ ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ በመጠየቅ ሦስት ነገሮች ማሳካት ይችላል፡- ታማኝነቱ ጥያቄ ውስጥ የገባውን ቃል እንደገና የመቋቋም ሥራ ይሠራል፣ መስቀለያ ጥያቄ ሲጠየቅ ፍርድ ቤት በስሕተት ግንዛቤ የወሰደባቸውን ነጥቦች ማስተካከል፣ በመስቀለያ ጥያቄ የተነሱ ነጥቦችን መሠረት በማድረግ አዳዲስና ጠቃሚ ፍሬ ነገሮች መገንባት ይቻላል፣

7.3 *መቃወም* (Objection)

በፍርድ ቤት ሙግት የተከራካሪ ወገን ጥቅሞች የሚጎዳ በተለይ ደግሞ መሪ ጥያቄ ሲቀርብ መቃወም አስፈላጊ ነው፡፡ መቃወም እንደመብት በመውሰድ ፋንታ በማይሰጥ መልኩ ፍርድ ቤት ማስቸገር ደግሞ ሌላ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡ የመቃወም ዓላማ አንድና አንድ ነው ምስክሩ ፍትሃዊ ባልሆነ መልኩ ምስክርነት እንዳይሰጥ ወይም መመስከር ያለበትን ጉዳይ ሳይመሰክር ከችሎት እንዳይነሳ ማድረግ ነው፡፡ መቃወም የሚቻለው በፈለከው ሰዓት ሳይሆን ጥያቄው ከቀረበ በኋላ መልስ ከመስጠቱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ማስረጃ ተቀባይነት ሲያጣ ወይም አግባብነትና ታማኝነት የለውም ተብሎ በሥር ፍርድ ቤት መቃወሚያ ካልቀረበበት በይግባኝ ፍርድ ቤት ማቅረብ አይቻልም፡፡

ዐቃቤ ሕግ መቃወሚያ ሲያቀርብ የሚከተሉት ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

1. በተደጋጋሚ መቃወሚያ ማቅረብ ታማኝነት ይሸረሽራል፣
2. ምስክሩ የሚሰጠውን መልስ ምን ያህል ክሱን የሚጐዳ መሆኑንና አለመሆኑን ማጤን፣
3. የምታቀርበው መቃወሚያ የሕግ መሠረት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡ መሠረታዊና የስነ ሥርዓት ሕጎች ጠንቅቆ ማወቅ ይጠይቃል፡፡ መቃወሚያ ለማቅረብ ምክንያት የሆነውን ከጥላቻና አድልዎ የተያያዙ ነገሮች ከሆኑ ጠያቂው ሳይጨርስ ጣልቃ ገብተን መቃወም እንችላለን፡፡ ለመቃወም ምክንያት የሆነው የሥነ ሥርዓት ጉድለት ወይም

መሠረታዊ ሕጎች የጣሰ መሆኑ በግልጽ ማሣየት ይጠበቅብናል፡፡ የሚቀርበው መቃወሚያ ዝርዝር ምክንያት የሚያስፈልገው ከሆነ መቃወሚያ ከቀረበ በኋላ መናገር ይቻላል፡፡ ለምሣሌ መቃወሚያው መሪ ጥያቄ ወይም የሰሚ ሰሚ ምስክርነት የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ ለምን መቃወሚያ እንዳነሳህ የምትጠየቅበት ጊዜ በዋናው ጥያቄ የመምራት ጥያቄ የማይቻል መሆኑን የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137/2 በመጥቀስ መከራከር ይቻላል፡፡

በዐቃቤ ሕግ ወይም የተከሳሽ ጠበቃ የሚያቀርቧቸው መቃወሚያዎች በጥያቄው ፎርም (Objection to form) ወይም መሠረታዊ ይዘት የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ በጥያቄው አቀራረብ/ፎርም/ የሚነሣው መቃወሚያ ለምሣሌ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሠረታዊ የማስረጃ አቀራረብ ይዘት የሚነሱ መቃወሚያዎች የሚከተሉት ጉዳዮች ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ የሚቀርበው ጥያቄ በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ ጉዳዩን ለማስረዳት የማይችል ከሆነ አግባብነት የለውም የሚል መቃወሚያ ሊነሣ ይችላል፡፡ የማስረዳት ወይም የማስተባበል ሚና የሌለው ማስረጃ መቅረብ የለበትም፣ በዋና ጥያቄ ወይም በማስቀለያ ጥያቄ የሚነሱ ነጥቦች የሚሰጥ ምላሽ ግንኙነት ከሌለው መጠየቅ ስለሌለበት የመቃወሚያ መሠረት ሊሆን ይችላል፣ ችሎታ በማጣት፣ በሕግ የተደረገ ክልከላ ካለ ለመመስከር ብቁ አይደለም የሚል መቃወሚያ ሊነሣ ይችላል፣ ማህበራዊ ጠቀሜታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በጠበቃና ደምበኛ፣ ሐኪምና በሽተኛ፣ባልና ሚስት፣ የንስሃ አባትና ምዕመናን የሚደረግ ግንኙነት የሕግ ከለላ ስላለው ሚስጥር እንዲጠብቁ ግዴታ አለባቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ወገኖች ከለላ ካልተደረገላቸው በስተቀር በነፃነት የመናገርና ሚስጥራቸውን የመግለጽ ፍላጐት አይኖራቸውም፡፡ አንድ ጠበቃ ደንበኛውን ለመወከል ይችል ዘንድ ዝርዝር ጉዳዮች ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ደንበኛው የሕግ ከለላ ከሌለው ደግሞ ሚስጥር ማካፈል አይችሉም፡፡ ስለዚህ ይህ እንደአንድ መቃወሚያ ሊነሣ ይችላል፡፡ በሕግ በልዩ ሁኔታ በሚታዩ የወንጀል ጉዳዮች ሚስጥር የመግለጽ ግዴታ ይኖራል፣ በመርህ ደረጃ ምስክሮች የዓይን ምስክሮች መሆን አለባቸው፡፡ የሰሚ ሰሚ ምስክርነት በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ መቃወሚያ ሊቀርብበት ይችላል፡፡ ምክንያቱም የሰሚ ሰሚ ምስክርነት በስሕተት፣ የማስተዋል ችግር፣ ሆን ተብሎ ለሚፈፀም ስሕተት የተጋለጠ ነው፡፡

7.4 ምስክር በመፈተን የፍርድ ቤት ሚና

በመሠረቱ የወንጀል ክስ በሚሰማበት ሂደት ማስረጃ ማቅረብና ምስክሮችን መመርመር የዓ/ሕጉና የተከሣሹ ኃላፊነት ቢሆንም ፍርድ ቤቱም የራሱ ሚናዎች አሉት፡፡ እነዚህን ሚናዎቹን ሲፈጽም ፍርድ ቤቱ ገለልተኝነቱን በማይነካ መልኩ በጥንቃቄ መሆን አለበት፡፡ የፍ/ቤቱ ዋና ዋና ሚናዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ምስክሮቹን መመርመር የባለጉዳዮቹ ሚና ቢሆንም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ የማብራሪያ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፡፡ /አንቀጽ 136/4/

- ተጨማሪ ምስክር እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

  በዚህም መሠረት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ምስክርነቱ አስፈላጊ ከመሰለው ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ምስክር /አሰቀድሞ ቃሉን የሰጠም ሆነ ያልሰጠ መጥራት ይችላል/ አንቀጽ 143 /1/ ዓ/ሕጉ ወይም ተከሣሹ በምስክር ዝርዝር ላይ ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡላቸው በጠየቁ ጊዜ ምስክሮቹ ነገሩን ለማከግየት ሳይሆን ለትክክለኛ ፍትህ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሮቹ እንዲጠሩ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል፡፡ ከእነዚህ ከተጠቀሱት ተግባራት ውጪ ዳኛው የቀረበለትን ጉዳይ በተመለከተ ማስረጃ ለመፈለግ የግሉን ምርመራና ምርምር ማድረግ የለበትም፡፡

የመወያያ ነጥቦች

1. በዋና ጥያቄ መወገድ የማይችል መሪ ጥያቄ ሊኖር ይችላል?
2. የፍርድ ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የሚቀርበው መቼ ነው?
3. ከወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ-137/1/ የምንገነዘበው ነገር ምንድን ነው?
4. የመሰቀለኛ ጥያቄ ይዘትና አደረጃጀት ምን መምሰል አለበት?
5. የድጋሚ ጥያቄ አላማ ምንድን ነው? ተግባራዊ አፈፃፀሙ እንዴት ይመለከቱታል?
6. ምስክር በመፈተንና ምሰክርነት በመቃወም ረገድ ያለው ልዩነት በአላማኝ ምክንያቶች በምሳሌ አሳዩ ?
7. ዓቃቤህግ በምስክርነት ያቀረበው ሰው ድጋሚ በመከላከያ ማስረጃነት መቅረብ ይችላልን?
8. የመቃወምያ አቀራረብ ለከተላቸው የሚገቡ ቅድመሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

9. **በ ፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኮ/መ/ቁ/** 62266 **የዓቃቤ ህግ ምስክሮች በተመሳሳይ ሞብተዋ ድጋሚ ተጠርተዋል፡፡ ጉዳዩን በመመልከት ካስገኙት ፋይዳ እና ካስከተለው ጉዳት አንፃር ተቹ?**

ዋቢ ጽሁፎች

<u>ሕጎች</u>

1. **የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አዋጅ** 1.1/1987
2. **የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አዋጅ ቁ**.414/1996
3. **የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ**.25/88
4. **የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁ**.652/2001
5. **አደገኛ ቦዘኔ አዋጅ**
6. **ፀረ-ሙስና አዋጅ**
7. Major Human Rights Instruments ፡A Selected Collection (ICCPR 1976)

<u>ሌሎች ፅሑፎች</u>

1. **በኢትዮጵያ ወንጀልን ስለሚመለከት ስልጣን የአስተያየት መግለጫ፤ በሮበርት አለን ሴድለር /የኢትዮጵያ ሕግ መፅሄት ቅፅ**.2 **ቁ**.2/
2. Ethiopian Criminal Procedure (By Stanley Z Fisher, 1969)

3. **የተዘነጉ የወንጀል የፍትሕ ስርዓት ድንጋጌዎች /በመንበረፀሐይ ታደሰ** 1996/
4. **የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተሻሻለው የወንጀል ስነ ስርዓት ሕግ ረቂቅ /በፍትሕና ሕግ ስርዓት ምርምር ኢንስቲቱዩት የተዘጋጀ** 1993/
5. **የወንጀል ክርክር ስርዓተ ችሎት /በፍ/ቤቶች ማሻሻያ ፕሮጀክት እና በፍትሕ እካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማእከል በጋራ የተዘጋጀ ሰኔ** 1997 **ዓ/ም/**
6. **በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ያሉትን አንዳንድ የሕግ ግድፈቶችና በአፈፃፀም ሂደት የሚጋጥሙ ችግሮች /የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ ጋር በመተባበር ባዘጋጀው የዳኞች ስልጠና የቀረበ፣ በገብሩ ዘነበ** 1994 **ዓ.ም/**
7. Andrew West, Yvon Desdevises et al, *The French Legal System, an Introduction*, (London: Fourmat Publishing, 1993).
8. **ብ/ጄኔራል ታጠቅ ታደሰ፣ *የማስረጃ ሕግ መሠረተ ሃሳቦች*፤ (አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጻህፍት ማዕከል፣ 1ኛ ዕትም፣** 1996).
9. Bryan A. Garner(ed.), *Black's Law Dictionary*, (Washington: West Publishing Co., 8th ed ., 2004).
10. Jerold H. Israel, and Wayne R La Fave, *Criminal Procedure, Constitutional Limitations in anut shell*, (St. Paul: West Publishing Co., 8th ed., 2001).
11. John N. Ferdico, *Criminal Procedure*, (Stamford: Wadsworth Group, 8th ed., 2002).
12. J.W.Ceil Turner, *Kenny's Outlines of Criminal Law*, (New Delhi: Universal Law Publishing Co. Pvt. Ltd., 19thed., Second Indian Reprint, 2004).
13. Marvin Zalman and Larry Siegel, *Key Cases and Comments on Criminal Procedure*, (St. Paul: West Publishing Co., 1994 ed., 1995).
14. Stanley Z Fisher, *Ethiopian Criminal Procedure, a Sourcebook,* (Addis Ababa: the Faculty of Law Haileselassie I University and Oxford University Press, 1969).
15. **ፀሐይ ወዳ፣ *የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች፣(አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም)*.**
16. **በሪሁ ተወልደብርሃን፣ በክስ አቀራረብ የሚታዩ ግድፈቶች** 2002 **ያልታተመ**
17. **በሪሁ ተወልደብርሃን፣ የኣቃቤ ህግ ምርመራ የመምራት፣ ጉዳይ የማደራጀትና የክርክር ክህሎት** 2003 **ያልታተመ**
18. Wayne R. LaFave and Jerold H. Israel, *Criminal Procedure*, (St. Paul: West Publishing Co., 4th ed., 2004).

19. **የኢትዮጵያ ወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ማስተማሪያ ማቴሪያል፤ ቦልዩም**.2 **/በንጋቱ ተስፋዬ፤** 1983 **ዓ.ም/**
20. **የኢትዮጵያ ወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ማስተማሪያ ማቴሪያል፤ ቦልዩም**1.2 **እና** 3 **የ ፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ማእከል**
21. European Criminal Procedures
22. **የማስረጃ ምዘና /በድጋፌ ደሳለኝ/**
23. **የማስረጃ አቀራረብና ሙግት ክህሎት /ተኽሊት ይመሰል/**
24. **የፍርድ አሰጣጥና አፈፃፀም /የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ከኢትዮጵያ የእስርቤቶች ሕብረት በመተባበር ለትግራይ ዳኞች ስልጠና የተዘጋጀ፤ በብርሃነ አሰፋ፤** 2000 **ዓ.ም/**
25. **የቅጣት አወሳሰን በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ /በመስፍን ገ/ህይወት** 1993 **ዓ.ም/**